ቅናትና መዘዙ
ገጽ 10



በመንገዴ ሳይ...
ገጽ 11

አእምሮን እየገዱ ያሉ ቀሳል ልማዶች
ገጽ 12




አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 068 ኅዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# በኢትዮጵያ ከ360 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል መኖሩ በጥናት ተረጋግጧል

- ባለፈው ዓመት ከአንድ ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ተመርቷል

**አመስወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከ360 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ሀብት እንደሚገኝ በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች በተደረገው ጥናት እንደተረጋገጠ የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ። ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ 186 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ማምረት መቻሉን ተጠቁሟል፡፡

የማዕድን ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቴዎስ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ባደረገው ጥናት መሠረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ360 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ይገኛል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ አንድ ነጥብ 186 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል መመረቱን አስረድተው፤ የሀገሪቱ ዓመታዊ የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ከአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ቶን በላይ እንደሆነ በ2015 ዓ.ም የተደረገ ጥናት ያሳያል ብለዋል።

በአሁን ወቅት በሀገሪቱ የሚገኙ በርካታ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በኢትዮጵያን የሚመረተው የድንጋይ ከሰል


**በኢትዮጵያ ከ360 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል**




## በምክክሩ

የራስ ሀሳብን ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን ሌሳውንም ወገን ማድመጥ ያስፈልጋል

ገጽ 9



ፎቶ: ገበበ ገብሬ

ታደሰ ኩማ (ዶ/ር)

## የዋጋ ግሽበቱን ለማርገብ በሀገር ደረጃ የገበያ ሥርዓቱን መፈተሽ ያስፈልጋል

**ምሕረት ሞገስ**

አዲስ አበባ፡- የዋጋ ግሽበት ለማርገብ አንዱ አባባሽ ምክንያት የሆነውን የገበያ ሥርዓት መፈተሽ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና ማዘመንና የገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል አስተባባሪ ታደሰ ኩማ (ዶ/ር) ገለፁ፡፡

አስተባባሪው ታደሰ ኩማ (ዶ/ር) ከአዲስ ዘመን

**የዋጋ ግሽበቱን ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል**

## ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የደረሰ ሰብል ተሰብስቧል

- እስካሁን 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- በመኸር እርሻ ከተዘራው 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የደረሰ ሰብል መሰብሰቡን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ እስካሁን 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ማግኘት እንደተቻለም ተጠቁሟል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የመኸር የምርት ዘመን ላይ 14 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር በዘር ለመሸፈን ታቅዶ 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት መሸፈን ተችሏል፡፡ ይህም ከዕቅድ በላይ መሠራቱን ያሳያል፡፡ እስካሁን ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የደረሰ ሰብል የተሰበሰበ ሲሆን፤ 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ማግኘት ተችሏል፡፡

መሬት ላይ ያለውን ሰብል ወቅቱን ካልጠበቀ ዝናብና ከተለያዩ ጉዳቶች ለመጠበቅ የመሰብሰብ ሥራ እየተከናወነ

**ከሁለት ነጥብ ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል**






# አምራች ኢንዱስትሪዎች በሦስት ወራት ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ወስደዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዳማ:- በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አምራች ኢንዱስትሪዎች ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ ብድር መውሰዳቸውን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። በሩብ ዓመቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች የብድር ምጣኔ ዝቅተኛ መሆኑ ተመላክቷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ2016 በጀት ዓመት የሦስት ወር አፈጻጸም ትናንት ሲገመገም በሚኒስቴሩ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጥላሁን ዓባይ እንደገለፁት፤ በሦስት ወራት ውስጥ በተለያየ ዘርፍ ለሚሠሩ ኢንዱስትሪዎች ከ13 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን በላይ ብር ብድርና ሊዝ ፋይናንስ ለማቅረብ ታቅዶ ሲሠራ ቆይቷል። በዚህም አምራች ኢንዱስትሪዎች በሦስት ወራት ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ወስደዋል፡፡

እንደ አቶ ጥላሁን ገለፃ፤ ብድሩ የተመቻቸው በልማት ባንክና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ነው፡፡ የሩብ ዓመቱን በአብዛኛው የብድር አቅርቦቱ ተጠቃሚ የሆኑት ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ናቸው።

ከዚህም ባለፈ ብድሩ እንዲቀርብ ታቅዶ ሲሠራ የቆየው ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ሥራ ማስኬጃና ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት መሆኑን ገልጸው፤ በተጨማሪም በቆዳና ቆዳ ውጤቶች እና በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ዘርፍን ለመደገፍ ብድሮች ተዘጋጅተው ሲሠራ እንደነበር አብራርተዋል።

ለከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ብቻ 12 ቢሊዮን ብር ለማቅረብ ታቅዶ ሲሠራ መቆየቱን ያነሱት ኃላፊው፤ በሦስት ወራት ውስጥ ከ10 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ለከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማቅረብ ተችሏል ሲሉ ገልፀዋል።




በሌላ በኩል ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ገደማ ለማቅረብ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በሦስት ወራት አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ለሥራ ማስኬጃና የሊዝ ፋይናንስ ብድር ለዘርፉ ማቅረብ መቻሉን አስረድተዋል።

በከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች እና በአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የቀረበው ብድር ስኬታማ እንደነበር የጠቀሱት የስትራቴጂክ ጉዳዮች አስፈፃሚው፤ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች እና በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የቀረበው ብድር አፈፃፀም በመጠኑ ዝቅ ያለ ነው ብለዋል።

ከቀረበው 600 ሚሊዮን ብር ብድር የዘርፉ ተዋናዮች ሊጠቀሙ የቻሉት 400 ሚሊዮን ብር ያህሉን ብቻ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በተለይ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተወሰደው ብድር ዝቅ ያለ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች መኖራቸውን አብራርተዋል።

በቆዳ ዘርፉ አብዛኛው ኢንዱስትሪዎች የብድር ሁኔታ የተበላሸ መሆን አንዱ ተግዳሮት መሆኑን አንስተዋል።

በተጨማሪም ወደ ቆዳ ዘርፍ የገቡ ኢንቨስትመንቶች አለመኖር የታቀደው የዘርፉ የብድር መጠን አፈፃፀም ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል ብለዋል።

# ማዕከሉ ከ250 በላይ የልብ ቀዶ ሕክምናዎችን መስጠት የሚያስችል ድጋፍ ተደረገለት

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ልማት ባንክ፣ ለኢትዮጵያ ልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል ከ250 በላይ የልብ ቀዶ ሕክምናዎችን መስጠት የሚያስችል የ31 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ፡፡

ድጋፉ በተደረገበት በትናንትናው ዕለት ንግግር ያደረጉት ኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዳይሬክተር ዮሐንስ አያሌው (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ባንኩ ብቸኛው የኢትዮጵያ የፖሊሲ ባንክ እንደመሆኑ የሀገራዊ ልማቶች ሁሉ መሠረት ሰዋዊ ልማት እንደሆነ ያምናል፡፡

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጠንካራ የኮርፖሬት ማኅበራዊ አገልግሎት ዕቅድ በማውጣት ማኅበረሰብ ተኮር በሆኑ ሰብዓዊ ተግባራት ላይ በመሳተፍ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ብለዋል፡፡

ባንኩ በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ቀውሶች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ እና በተለያዩ ችግሮች ላይ የሚገኙ ዜጎችን በማቋቋም ለችግራቸው እየደረሰ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ የማኅበረሰብ ልማትና ሰብዓዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመመደብ በመሥራት ላይ ይገኛል ብለዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ባንኩ የተሳተፈባቸው ሌሎች ሰው ተኮር ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዳሉ ገልጸው፤ ለማዕከሉ ያደረገውን ሳይጨምር ከ29 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

የማዕከሉ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ ሰላዲን ከሊፋ በበኩላቸው፤ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የተገኘው የ31 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ከ250 በላይ የልብ ቀዶ ሕክምናዎች ለመስጠት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

በልብ ሕመም የሚሰቃዩ እንዲሁም ወረፋ




የሚጠብቁ በርካታ ሕጻናት ታካሚዎችን እንግልት የሚቀንስ እና እፎይታ የሚሰጥ ይሆናል ሲሉም አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የኢትዮጵያ የልብ ሕክምና ሕጻናት መርጃ ማዕከል ብራንድ አምባሳደር አርቲስት መሠረት መብራቴ እንደገለጸችው፤ የባንኩ ከፍተኛ አመራሮች ማዕከሉ በጎበኙበት ወቅት የገቡትን ቃል በመተግበራቸው ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ማዕከሉ የመሥራት አቅም ያላቸው ባለሙያዎች ያሉት ቢሆንም የግብዓት እጥረት ግን ትልቅ እንቅፋት ሆኖበታል ያለችው አርቲስት መሠረት፤ ድጋፉም የብዙ ወላጆችንና ሕጻናትን እንባ የሚያብስ እና እፎይታ የሚሰጥ ነው ብላለች ፡፡

የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ላደረገለት ድጋፍ በልብ ሕሙማን ሕጻናት ስም ምስጋና አቅርቦ የባንኩ እና የሌሎች አካላት ድጋፍ እና ትብብር እንዲቀጥል ጠይቋል።



ሙሉቀን ንጋቱ (ዶ/ር)

# የኅብረተሰቡን ችግሮች ለመፍታት የፈጠራ ሥራዎችን ማበራከት ይጠይቃል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ ፡- የኅብረተሰብ ችግሮችን ለመፍታት ሳይንሳዊ የፈጠራ ሥራን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ የትምህርት ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

ስምንተኛው ዓለም አቀፍ የሒሳብና የሳይንስ ቀንን ምክንያት በማድረግ ሀገር አቀፍ የመምህራንና የተማሪዎች የሳይንስ ፈጠራ ሥራዎች ውድድር ሰሞኑን ተካሂዷል፡፡

በወቅቱ በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሙሉቀን ንጋቱ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ በሳይንስ የተደገፉ የፈጠራ ሥራዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለማቃለል አይነተኛ መንገድ ናቸው።

የዓለም ሀገራት ከድህነት ተላቀው ወደ ዕድገት የተሸጋገሩት ለሳይንስ ትምህርትና ፈጠራ ሥራዎች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው በመሥራታቸው መሆኑን ገልጸው፤ ተቋማትና ግለሰቦች የምርምርና ፈጠራ ሥራዎችን በተለያየ መንገድ በመደገፍ መሥራት እንደሚገባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ በሳይንስ ብቁ ተማሪዎችን ለማፍራት ሁሉን አቀፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ሚኒስቴሩም ተማሪዎች በሳይንስ ትምህርት የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ በትኩረት እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በየዓመቱ የሳይንስ ቀን መከበሩ የፈጠራና የምርምር ሥራዎች ለኅብረተሰቡና ለተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ዶክተር ሙሉቀን አስረድተዋል፡፡

የኅብረተሰቡን ችግሮች ለመፍታት ሳይንሳዊ እውቀት አስፈላጊ መሆኑን ያነሱት ዶክተር ሙሉቀን፤ ቀኑን አስመልክቶ የሳይንስ ውድድር መዘጋጀቱ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ለሌሎች ለማካፈል እንደሚረዳ አመልክተዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የሒሳብ ሳይንስና ሥነ-ጥበብ ዴስክ ኃላፊ አቶ ታደሰ ተሬሳ በበኩላቸው ትምህርት ሚኒስቴር የተማሪዎችን ችግር ፈች የፈጠራ ሥራዎች ለማሳደግ የመምህራን ብቃት ማደግ ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ አቅም ግንባታ ሥራው በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በሀገር አቀፍ የፈጠራ ሥራዎች ውድድር 211 ችግር ፈች የፈጠራ ሥራዎች እንደቀረቡ ገልጸው፤ የተማሪዎች የፈጠራ ሥራ ውድድር በዘርፉ ያለውን የክህሎት አቅም ለማዳበር አይነተኛ መንገድ መሆኑን አስረድተዋል።

በሀገር አቀፍ የመምህራንና የተማሪዎች የሳይንስ ፈጠራ ሥራዎች ውድድሩ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እና የክልል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ከ200 በላይ መምህራንና ተማሪዎች የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ይዘው ቀርበዋል። በውድድሩ 211 የፈጠራ ሥራዎች ቀርበዋል።

የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ይዘው የቀረቡት መምህራንና ተማሪዎች በበኩላቸው፤ ለሳይንስና ፈጠራ ሥራዎቻቸው ተገቢው ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጥሪ አቅርበዋል።

የፈጠራ ሥራዎች ለውድድር ቀርበው ለአሸናፊዎች ሽልማት እንደተበረከተ ታውቋል፡፡



ወይዘሮ ሠላማዊት ዳዊት

# በሦስት ወራት 69 ሺህ በላይ ፓስፖርት ተደራሽ ተደርጓል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ ፤ ባለፉት ሦስት ወራት 69 ሺህ 659 ፓስፖርት መሰራጨቱን የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሠላማዊት ዳዊት የተቋሙን የሦስት ወር አፈጻጸም መግለጫ በሠጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ አገልግሎቱ ባለፉት ሦስት ወራት 531 ሺህ 800 ፖስፖርት አሳትሞ ወደ ሀገር አስገብቷል። ከእዚህ ውስጥ 69 ሺህ በላይ ፓስፖርት ተደራሽ ተደርጓል፡፡

45 ሺ 366 ፓስፖርት ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የተላለፈ ቢሆንም 15 ሺ 924 መልዕክት ቢደርሳቸውም እስካሁን አልወሠዱም ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ይህ አካሄድ ፓስፖርቱን ለአስቸኳይ በሚፈልጉ ሰዎች ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ በቀጣይ መስተካከል እንደሚኖርበትም ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ ሠላማዊት ገለጻ፤ 8 ሺህ 500 ከዛሬ ጀምሮ በክልል ለሚገኙ መሠራጨት ጀምሯል። በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ስር ሥልጠና ወስደው ወደ ውጭ ለሥራ የሚሄዱ በክልል ለሚገኙ ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል። 15 ሺ 793 የአስቸኳይ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውንም ማዳረስ ተችሏል።

በውጭ ሀገራት ለሚኖሩ ዜጎችም እስካሁን በዲ. ኤች. ኤል በኩልና በኦንላይን 40 ሺህ 531 ፓስፖርት መላኩን ጠቁመው፤ በተጨማሪ የዲፕሎማት የሰርቪስ የድንገተኛና ለትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚሰጡ ጊዜያዊና ቋሚ መታወቂያ አገልግሎት መስጠታቸውንም ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ባለፉት ሦስት ወራት በቁጥጥር ስር የዋሉት ተጠርጣሪዎች በሙስና በሌብነት እንዲሁም በድለላ ኔትወርክ የተሠማሩ መሆናቸው አውስተው፤ ከፓስፖርት ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚታዩ በርካታ ችግሮች ነበሩ። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በተሠራው ሥራ ከተቋሙ 34 ወንዶችንና አራት ሴቶችን እንዲሁም 15 ከተቋሙ ውጪ ኔትወርክ በመፍጠር በድለላ የተሠማሩ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረጋቸውን ተናግረዋል።

በተጨማሪ 50 አየር በአየር የተሠሩ ፓስፖርቶችም እንዲሠረዙ መደረጋቸውን ገልጸው፤ ሕገ ወጥ ሰነዶችን ተጠቅሞ ከሀገር የመውጣትና የመግባት እንቅስቃሴዎችን ለመግታት በየብስና በአየር ማረፊያ በተደረገ ቁጥጥር ከ180 በላይ ግለሰቦች መያዛቸውንም ይፋ አድርገዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ አገላለጽ፤ 61 ኢትዮጵያውያን በሕገ ወጥ መንገድ ሰዎችን በሚያዘዋውሩ ግለሰቦች ተታለው በድንበር ከሀገር ሊወጡ ሲሉ ተይዘው እንዲመለሱ ተደርጓል። ይህ ብልሹ አሠራርን ለማስቆም የሚደረግ እንቅስቃሴ ከሕዝብና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

ተቋሙ አሁን እየሰጠ ያለው አገልግሎት ከፍተኛ ክፍተት ያለበት በመሆኑ ይህንን ለማስተካከል የሚሠሩ ሥራዎችም ይኖራሉ ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ መረጃን በአንድ ማዕከል ተደራሽ ለማድረግ፤ እንዲሁም ተገልጋዮችን ምልልስ ለመቀነስና ሰነዶችን በተመለከተ ከወረቀት ነፃ በሆነ መልኩ በቴክኖሎጂ ለማከናወን እየተሠራ ይገኛል። በተጨማሪ የትግራይ ክልልን ጨምሮ የተለያዩ ችግሮች ባሉባቸው አካባቢዎች በነበሩ የአገልግሎቱ ቢሮዎች ላይ የደረሡ ውድመቶችን በማጥናት ሥራ ለማስጀመር እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# የኢትዮጵያን የባሕር በር ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መቃኘት ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


አዲስ አበባ:- የኢትዮጵያን የባሕር በርና የወደብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በጉዳዩ ላይ ያሉ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መመልከት እንደሚገባ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካሪ አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ ገለጹ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያዘጋጀው የፍትሐዊ የወደብ አጠቃቀም ልዩ ሴሚናር "ፍትሐዊ የወደብ አጠቃቀም ለአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላምና ልማት" በሚል መሪ ሀሳብ ትናንትና ተካሂዷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካሪና የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የሦስትዮሽ ድርድር ተደራዳሪ ቡድን አባል አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ከዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ሕግ አኳያ ያለውን አንድምታ አስመልክቶ የመወያያ ጽሑፍ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ የባሕር በር የመጠቀም ጥያቄና ፍላጎት የረጅም ጊዜ የታሪክ መሠረት እንዳለው አምባሳደር ኢብራሂም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፍላጎት የባሕር በርና ወደቦችን በሰጥቶ መቀበልና የሀገራትን ሉዓላዊነትን ባከበረ መልኩ መጠቀም መሆኑን አመላክተዋል።



አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ

የሀገሪቷ ፍላጎት ዓለም አቀፍ ሕግን መሠረት ያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ እ.አ.አ በ1982 የፀደቀውን ዓለም አቀፍ የባሕር ሕግ በማሳያነት ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚ ለመሆን ከዚህ ቀደም የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት የባሕር በር ካላቸው ሀገራት ጋር በመነጋገር ተጠቃሚነታቸውን ያረጋገጡባቸውን ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መመልከት አለባት ብለዋል።

ኢትዮጵያ በጉዳዩ ላይ ሰፊ የዲፕሎማሲ ውይይቶችን ከሀገራት ጋር ማድረግ እንደሚጠበቅባትም ጠቁመዋል።

የአፍሪካ ኅብረት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የባሕር በር የሌላቸው የአፍሪካ አገራት የሚያነሷቸው የተጠቃሚነት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ የበኩሉን ሚና ሊጫወት እንደሚገባና ቀጣናዊ ተቋማት ለጉዳዩ በትኩረት መሥራት እንዳለባቸው አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎት ውይይት የሚያስፈልገው መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ አኳያም እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በጉዳዩ ላይ ውይይቶችን በማዘጋጀት ሳይንሳዊ ምክረ ሃሳቦችን ማፍለቅ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የቀጣናው ሀገራት ምሑራን ለመንግሥታት ዲፕሎማሲያዊ ውይይቶች መሠረት የሚጥሉ ተከታታይ ምክክሮችን በማድረግ የመፍትሔ አማራጮችን እንዲያመላክቱም ጠይቀዋል።

በሴሚናሩ ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር)፣ የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች፣ ምሑራንና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።



# የትግራይ ክልል የቱሪስት መዳረሻዎች በመጪው ሳምንት ክፍት ይደረጋሉ

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ላለፉት ዓመታት በፀጥታ ችግር ምክንያት ተዘግተው የነበሩት የትግራይ ክልል የቱሪስት መዳረሻዎች በቀጣይ ሳምንት ለጎብኚዎች ክፍት እንደሚደረጉ ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ እንዳስታወቁት፤ በፀጥታ ችግር ምክንያት በክልሉ የሚገኙ የቱሪስት መስሕቦች ሳይጎበኙ ብሎም ሆቴል እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከሥራ ውጪ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ከመጪው ሳምንት ጀምሮ የክልሉ ቱሪስት መዳረሻዎች ለጎብኚዎች ክፍት ይደረጋል፡፡

የአክሱም ሐውልት ጥገና እና ሌሎች የቅርስ ጥገና ሥራዎች ከሞላ ጎደል የተከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ ሆቴሎች እና አስጎብኚ ድርጅቶችም አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅተዋል፡፡ የሚሰጡት አገልግሎትም ጥራት ያለው እና ለዚህም ተመጣጣኝ ዋጋ በማስከፈል አካባቢውን ማስተዋወቅ የሚችል መሆን እንዳለበት አስታውቀዋል፡፡

ላለፉት ስድስት ወራት የዝግጅት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት አቶ ስለሺ፤ በቀጣይ ሳምንት ቱሪስቶች በክልሉ ተዘዋውረው መጎብኘት ይችላሉ፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ እና አስጎብኚዎች ቱሪስቶችን በአግባቡ ተቀብሎ በማስተናገድና ከፀጥታ ችግር ነፃ የሆነ የጉብኝት ሥርዓት እንዲኖር ማገዝ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ጎብኚዎች ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ የሽሬ አውሮፕላን ማረፊያን በመጠቀም አክሱምን በቀላሉ መጎብኘት ይችላሉ፡፡ ከመቀሌ ወደ አክሱም እንደ ነጃሺ፣ አዲግራት ያሉ መልክዓ ምድሮችን በመኪና እየጎበኙ የሚሄዱበት ዕድል እንዳለም ተናግረዋል፡፡

ቱሪስቶች በዋነኝነት የቱሪዝም ቀጠና ነው የሚመርጡት፡፡ የትግራይ ክልልም የቱሪዝም እንቅስቃሴ ከአማራ ክልል እና ከአፋር ክልል ጋር የተሳሰረ እና በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህም ከአጎራባች ክልሎች ጋር በቅንጅት በመሥራት ቱሪስቶች እየተዘዋወሩ እንዲጎበኙ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በዋና ዋና የቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ የሚገኙ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሕይወት ሕልውናቸው ቱሪዝም ዘርፍ የሆነባቸው አካባቢዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ከእነዚህም መካከልም ደባርቅ፣ አክሱም፣ላሊበላ እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡

ቱሪዝም እና ሰላም የሚለያዩ አለመሆናቸውን የገለጹት አቶ ስለሺ፤ የሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ ሲያድግ እና ሰዎች የሌላውን አካባቢ ታሪክ እና ባሕል ሲያውቁ የተሻለ ቅርበት ይፈጥራል፡፡ የውጭ ቱሪስቶችም በመሳብ ቱሪዝሙን ዘርፍ እንዲያድግ እና መጠቀም የሚገባን ጥቅም እንድናገኝ ይረዳል ብለዋል፡፡

ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅማ ለማሳደግም ቱሪዝሙን ለማዘመንና ለማሳደግ እንደሚሠራ አመልክተዋል፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የቁስጥ ገጾች



## «የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር የንግድ ሥርዓቱን በደንብ መፈተሽ ያስፈልጋል»

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና ማዘመንና የገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል አስተባባሪ ታደሰ ኩማ (ዶ/ር)

ገጽ 6



ትኩረት ያልተሰጠው የጋማ እንስሳት ጤና

ገጽ 19



ያልጠለቀች ጀንበር...

ገጽ 22

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አዲስ አበባ The Vibrant Hub of Africa

**አፍሪቃዊቷ መልኅቅ**

## ቅርስን መጠበቅ፤ ማንነትና ሀገርን መጠበቅ!

**ዳንኤል ዘነበ**

አንድ ሀገር ሃይማኖት፣ ታሪክና ቅርስ ከሌለው ማንነቱ በሌሎች ዘንድ ሊታወቅ አይችልም፡፡ ቅርሶች ያለፈውን፣ ነባሩንና ተተኪውን ትውልድ የሚያገናኙ የኀብር ትውልድ ድልድዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ ሕዝብ ቅርስ አለው ሲባል ታሪክ አለው ፤ ክብር አለው ተደማጭነት እንዲያገኝ የሚያደርግ ማስረጃ አለው ማለት ነው፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው የቅርስ ጥናትና ጥበቃ አዋጅ 209/92 አንቀጽ 3 "ቅርስ ማለት በኢትዮጵያ ቅድመ ታሪክና ታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የሥራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ፣ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትንም የሚገልጽና የሚመሰክር፣ በሳይንስ፣ በባሕል፣ በታሪክ፣ በዕደ ጥበብና በሥነ-ጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያለው ማንኛውም ግዙፍነት ያለው ግዙፉነት የሌለው ነገር ነው" ሲል ብያኔ አስቀምጠዋል።

ስለ ሀገራችን ቅርሶች ስናነሳ በዓለም በቅርስነት ተመዝግበው እየተጎበኙ የሚገኙ ቅርሶች መካከል በርካቶቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሻራ ያረፈባቸው ቅርሶች ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ ለሀገራችን ያበረከተቻቸው ታሪካዊ ቅርሶች ከታዋቂነታቸው አንጻር ከፍ ያለ ቦታና ዓለም አቀፋዊ ዋጋ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ ከሆኑ የሀገራችን ታሪካዊና ሀይማኖታዊ ቅርሶች ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የመንበረ ፀባዖት የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይጠቀሳል ።

መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አመሠራረት በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ታኅሳስ 24 ቀን 1883 ዓ.ም እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። በጊዜው ታቦቱ ዛሬ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በተሠራበት ቅጥር ግቢ ውስጥ መቃኞ ሠርተው ያስገቡ ሲሆን የቤተክርስቲያኑ የክብር ስም ደብረ ጽጌ ተብሎ ነበር።



**የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የእድሳት ግንባታ 40 በመቶ ደርሷል ፤**

በኋላም በ1885 ዓ.ም በዘመነ ማቲዎስ መካነ ሥላሴ ተብሎ ተሰየመ አሁን የሚገኘው ታላቁ ካቴድራል የመሠረት ድንጋይ የተጣለው በ1924 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴ ሲሆን ሥራው ተጀምሮ ሳለ ጣሊያን ሀገራችንን በመውረሩ ምክንያት ግንባታው ለዓመታት ተቋርጦ ከቆየ በኋላ በ1935 ዓ.ም ግንባታው ተፈጽሞ የቅዳሴ ቤቱ በዓል በ1936 ዓ.ም ተጠናቆ ተከብሯል።

በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ትልልቅ ቅርሶች አንዱ ሆኖ የተመዘገበው የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ፓትርያርኮች እና የሊቃነ ጳጳሳት በዓለ ሲመት የሚከናወንበትና በመካነ እረፍታቸው ጊዜም የማረፊያ ቦታ መሆኑ ይታወቃል። ካቴድራሉ ለሀገር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉ ግለሰቦችና መሪዎች መካነ መቃብር የሚገኝበት ሲሆን፤ በውስጡም ዘመናትን ያስቆጠሩ ቅርሶችን የያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከ90 ዓመታት በላይ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየው የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት እየተደረገለት ይገኛል፡፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለፈ የሀገር ቅርስ የሆነው ካቴድራሉ የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት ስለደረሰበት እድሳት ማድረጉ አስፈላጊ ሆኗል ።

በከተማዋ ከሚገኙ ትልልቅ ቅርሶች አንዱ በሆነው የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለፈ የሀገር ቅርስ እንደመሆኑ ይዘቱንና ቅርሱን ጠብቆ በመታደስ ላይ ነው። በካቴድራሉ የተጀመረውን የጥገና ሥራ ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ የሚያስችል የገቢ (ድጋፍ) የማሰባሰብ ሥራ ኅዳር 1 ቀን 2016 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል ተካሂዷል፡፡ የገቢ ማሰባሰብ ፕሮግራሙ የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ኃላፊዎችና ኮሚቴዎች ከአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ በጋራ በመተባበር ያዘጋጁት ሲሆን የሀገር ሽማግሌዎች፣ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶች፣ እውቅ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ ታዋቂ አርቲስቶች፣ ባለሀብቶችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

በተደረገው የድጋፍ ማሰባሰብ ፕሮግራም ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ክብርት ዶክተር ሂሩት ካሣው እንደተናገሩት፣ ቅርስ የአንድ ሀገር የመነሻነትና መድረሻነት የሚያሳይ ስለሆነ ኢትዮጵያ ሀገራችን የሰው ልጅ መገኛ፣ የሁሉም ነገር በተለይ የፈጠራ ሥራ የአስተሳሰብና የዕደ ጥበብ መነሻ መሆናችን የሚያሳየን ቅርስ መሆኑንም ገልጸዋል። ቅርስ የሰው ልጆች ሁሉ ሀብት በመሆኑ፤ ቅርሶቻችን መጠበቅ የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ኃላፊነትም እንደሆነ ጠቅሰው፤ መንበረ ፀባዖት የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅርስ መጠበቅ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገባዋል ብለዋል ።

ዶክተር ሂሩት፣ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከኪነ-ሕንጻነትና ከቅርስነት በተጨማሪ ንጉስ ካዎ ጦናን ጨምሮ የበርካታ የሀገር መሪዎቻችን፣ ጀግኖቻችንና አርቲስቶቻችን ያረፉበት ቦታ ስለሆነ ሁላችንም ልንጠብቀው ይገባል ሲሉም አብራርተዋል።

በእለቱ በካቴድራሉ የተጀመረውን የጥገና ሥራ ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ የሚያስችል የገቢ (ድጋፍ) ማሰባሰብ መርሐ-ግብሩ የተሳተፉ ባለሀብቶች የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል። ግንባታው አሁን የደረሰበት ደረጃ 40 በመቶ መሆኑንና ለቀሪው ግንባታ እስኪጠናቀቅ 172 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡ ካቴድራሉ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለፈ የሀገር ቅርስ በመሆኑም በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሕንጻው እድሳት ሥራ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቅ እንዲችል የተለመደውን ትብብርና ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ ቀርቧል።

የኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ የሆኑ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች አበርክታለች ። ከእነዚህ መካከል በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ትላልቅ ቅርሶች አንዱ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አንዱ ነው። አባቶቻችን በታላቅ ጥረትና ተጋድሎ ያስረከቡን የሃይማኖትና የማንነታችን መገለጫ የሆነው ሀገራዊ ቅርስ በተሻለ ቁመና ከትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር የጥገና ሥራ እየተሠራ መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን ጥገና ሙሉ ለሙሉ እንዲጠናቀቅ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአቅሙ ድጋፍ በማድረግ እንዲጠናቀቅ ማድረግ ያስፈልጋል ።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር የንግድ ሥርዓቱን በደንብ መፈተሽ ያስፈልጋል››

## የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና ማዘመንና የገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል አስተባባሪ ታደሰ ኩማ (ዶ/ር)

**ምሕረት ሞገስ**

የቀድሞ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት የአሁኑ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት መሥራች ተመራማሪ ናቸው፡፡ በእርሳቸው መሪነት በኢትዮጵያ ግብርና ዙሪያ 30 የሚደርሱ ምርምሮች ተካሂደዋል። ከምርምሩ ጎን ለጎን የሁለተኛ ዙር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልም ነበሩ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪቸውን በኢትዮጵያ በኢኮኖሚክስ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኮሪያ በዴቨሎፕመንት ኢኮኖሚክስ፣ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን በደቡብ አፍሪካ በግብርና ኢኮኖሚክስ ላይ አተኩረው ተምረዋል፡፡

የዛሬው የዘመን እንግዳችን እስከ ሶስተኛ ዲግሪ ተምረው ጥሩ ደረጃ ላይ ቢደርሱም፣ ውልደታቸው ከአርሶ አደር ካልተማረ ቤተሰብ ሲሆን፣ ትምህርት ለመማር ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ወላይታ ዞን በሶዶ ዙሪያ ወረዳ በ1957 ዓ.ም የተወለዱት የዛሬው የዘመን እንግዳችን ታደሰ ኩማ (ዶ/ር)፣ የልጅነት ሕይወታቸውን ያሳለፉት አረካ ከተማ አካባቢ ወይቦ በተሰኘ መንደር በአያታቸው ቤት ነበር፡፡

በእርሳቸው የልጅነት ዘመን በአካባቢው ልጅ የሚወለደው በትምህርት ራሱን ከፍ ያለ ደረጃ እንዲያደርስ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ በእርሻ ወይም ከብት በመጠበቅ ቤተሰቡን እንዲያግዝ ይፈለግ ነበር፡፡ የታደሰ (ዶ/ር) ቤተሰብ ግን፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ የነቁ በመሆናቸው ትምህርት ቤት ላኳቸው፡፡

ትምህርት እንዲጀምሩ ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት ደግሞ አክስታቸው ነበሩ፡፡ የአክስታቸው ሴት ልጅ እና እርሳቸው ቃለሕይወት የተባለ ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥረው፣ አረካ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት እንዲቀስሙ ተላኩ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን መማር ግን ቀላል አልነበረም። ከአያታቸው ቤት ተነስተው ትምህርት ቤት እስከሚደርሱ በልጅነት ጉልበታቸው በትንሹ ለአንድ ሰዓት ተኩል በእግር የመሔድ ግዴታ ነበረባቸው፡፡ ሲመለሱም በተመሳሳይ መልኩ ለአንድ ሰዓት ተኩል ተጉዘው አምሽተው ቤታቸው ይደርሱ ነበር።

አካባቢው ጫካ እና ወንዝ ያለበት በመሆኑ መንገድ ላይ ከሚያጋጥማቸው አውሬ ጋር እየፈሩ ይተላለፉ ነበር፡፡ መጋቢት እና ሚያዚያ ላይ ደግሞ እንደአሁኑ ድልድይ ባለመኖሩ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የሞላ ወንዝ እስኪጎድል በወንዝ ጫፍ ተቀምጠው እየጠበቁ፣ ተለቅ ያለ አቅም ያለው ጠንካራ፣ ሊያሻግራቸው የሚችል ሰው ሲገኝ እየለመኑ እየተሻገሩ፣ ወንዙ አልጎድል ሲላቸው ደግሞ እየመሸባቸው ለምነው ሰው ቤት እያደሩ ከበድ ያሉ ፈተናዎችን አሳለፉ፡፡

ልጅ ስለነበሩ እየሮጡም እየተራመዱም፣ በቀን ለሶስት ሰዓት በእግር በመጓዝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ከ1964 እስከ 1968 ዓ.ም ተከታተሉ፡፡ ችግሩ ግን መንገዱ ብቻ አልነበረም። በአካባቢው ስንቅ አስቋጥሮ ትምህርት ቤት የሚልክ ቤተሰብ አልነበረም፡፡ ቤት ያፈራውን፣ በእጅ በተሰፋ የአቡጀዴ ጨርቅ ቂጣም ሆነ ጥሬ ያገኙትን ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ይሔዳሉ። አንዳንዴ ቤተሰብ ምንም ላያዘጋጅ ይችላል። በዛ ጊዜ ገንዘብ ውድ በመሆኑ፣ ገዝቶ መብላት የሚታሰብ አይደለም። በእርግጥ የተራበ ሰው አንኳኩቶ ማንንም ቢጠይቅ ወተት የሚሰጥ አይጠፋም። ነገር ግን ሁልጊዜ ሰውን ማስቸገር ከባድ ነው፡፡ እንዲህ እያሉ የእግር መንገዱንም፣ ከአውሬ ጋር መተላለፉንም፣ ረሃቡንም ሆነ ደራሽ ውሃውን አሳልፈው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡

ድቦ እመቤታችን መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ሲማሩ፣ ቀደም ሲል የነበረው መከራ ተቃለለ፡፡ መንገዱ ሜዳ ከመሆኑም ባሻገር፣ ወንዝ ስላልነበረ ብዙ አልተቸገሩም፡፡ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሲሸጋገሩ እና ሶዶ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ግን፣ ሌላ ፈተና ገጠማቸው፡፡ ወይቦ አካባቢ ካለው የአያታቸው ቤት ተነስተው ሶዶ ከተማ ለመድረስ በትንሹ 35 ኪሎ ሜትር አካባቢ መጓዝ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ በእግር ይሔን ያህል መጓዝ ከባድ ነበር፡፡

እሁድ ለሰኞ አጥቢያ ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ተነስተው በእግራቸው ተጉዘው ትምህርት ቤት ይደርሱ ነበር። እስከ አርብ አጎታቸው ቤት እያደሩ ትምህርታቸውን ተከታትለው፣ አርብ ማታ ተጉዘው ቤተሰባቸው ጋር ይመለሱ ነበር፡፡ በአብዛኛው



ፎቶ ፡- ገበቦ ገብሬ

ከጓደኞቻቸው ጋር በቡድን የሚሄዱ ሲሆን፣ አንዳንዴ ደከም ብሎ ከቡድኑ የመነጠል አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ጊዜ ለብቻ ቀበሮ፣ ድብ፣ ጅብ ያጋጥማል፡፡ ይህንን ሁሉ አልፈው ብዙ ውጣ ውረዶችን ተቋቁመው አሁኑ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና ማዘመንና የገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል አስተባባሪ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙት ታደሰ ኩማ (ዶ/ር) አጠቃላይ የህይወት ውጣ ውረዶቻቸውን፣ ያጠኗቸውን ጥናቶች እና የምርምር ግኝቶቻቸውን በተመለከተ ቆይታ አድርገን እንዲህ አቅርበንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- ገጠር ተወልዶ ለከፍተኛ ደረጃ መድረስ ምን ያህል ፈታኝ ነው? እስኪ የልጅነት አጋጣሚዎን ይንገሩን?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በጣም ከባድ ነው፡፡ አንድ ጊዜ 10ኛ ክፍል ሆኜ ሰኞ ፈተና ነበረኝ፡፡ ሌሎቹ ጓደኞቼ አስቀድመው እሁድ ማታ ወደ ሶዶ ከተማ ሲሔዱ፣ እኔ ግን በለሊት ወጥቼ በመኪና እደርሳለሁ ብዬ ቀረሁ፡፡ከአያቴ ቤት ገንዘብ ለምኜ 35 ኪሎ ሜትር በመኪና ትምህርት ቤት ለመሔድ አስቤ ነበር፡፡ ነገር ግን ልቤ አላረፈም፡፡ ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል ብዬ በጨለማ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ ብዙ ብሔድም አልነጋም፡፡ ድብ አንገቱን አቀርቅሮ ጉድጓድ ሲቆፍር ግማሽ አካሉ ጉድጓድ ውስጥ በመሆኑ ድብ መሆኑን ሳላውቅ እላዩ ላይ ወጣሁ፡፡ በጣም ደነገጥኩ፣ ድቡም ደነገጠ፡፡ በድንጋጤ ተንደርድሬ ዛፍ ላይ ወጣሁ፡፡

ድቡ ደንግጦ ስለነበር አላጠቃኝም ትቶኝ ሔደ፣ ዛፍ ላይ እንዳለሁ መንጋት ሲጀምር፣ ከሰዎች ጋር ተቀላቅዬ ሔድኩ፡፡ በአጋጣሚ መኪና አግኝቼ ለፈተና ደረስኩ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት መሔድ ብቻ ሳይሆን አምሽቶ ወደ ቤት መመለስም እጅግ ከባድ ነበር፡፡ ከአውሬ ጋር መጋፈጥ ብቻ ሳይሆን፣ ድካም እና ረሃቡ ቀላል አልነበረም፡፡ በዛ ላይ ለደብተር መግዣ እና በበጋ ለሚወጣ ወጪ ክረምት ላይ እነግድ ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ የትምህርት ውጤትዎ እንዴት ነበር? ንግዱ መቼ ቆመ?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በጣም ምጡቅ ተማሪ ነኝ ብዬ ባላጋንንም፣ ጥሩ የሥራ እና ትምህርት የመማር ባህል አለኝ፡፡ ከክፍል ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ እወጣለሁ፡፡ በባህሪዬ ጭምት ነኝ፡፡ ሥራ እወዳለሁ፡፡ በ1964 ዓ.ም አንድ ቀድሞ ተምሮ አስመራ ይሠራ የነበረ የእኔ አጎት በድምፅ መቅረጫ ቀድቶኝ ነበር፡፡ ‹‹ ሥራ ሥሩ፣ ሥራ ሥሩ አገር የሚለማው በሥራ ነው፡፡›› ብዬ አዜም ነበር፡፡ ለሥራ ያለኝ ጉጉት ከዛ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡

በእርግጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ስማር አይኔን በመታመሜ ለአንድ ዓመት ትምህርቴን አቋርጬ ነበር፡፡ በተጨማሪ በ1975 ዓ.ም አባት እና እናቴ ተለያይተው፣ እናቴ እና አያቴ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ማጠቃለያ ፈተና ሲደርስ ፣ እሁድ ለስንቅ ቤት ሔጄ እናቴ በድንገት ታመመች፡፡ ሰኞ እና ማክሰኞ እናቴን ሃኪም ቤት ወስጄ አሳክሜ፣ እኔ ታመምኩኝ፡፡ ፈተናውን ታምሜ በመፈተኔ ውጤቴ ዝቅ አለ። በጣም አዝኜ ነበር፡፡ ነገር ግን በኋላ የመምህርነት መግቢያ ፈተና ተፈተንኩኝ፣ ከብዙ ሰዎች መካከል ሁለተኛ ሆኜ የሐዋሳ መምህራን ማሠልጠኛ ገባሁ፡፡

የመምህርነት ሥልጠናውን እንዳጠናቀቅኩ በመንግሥት ትምህርት ቤት ማገልገል ጀመርኩ፡፡ በሲዳሞ አካባቢ ሀገረ ሠላም ወረዳ ከስድስት ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ወደ ሚገኘው ቀጭኑ ሳምኣሎ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመደብኩ፡፡ በዛ ጊዜ ሲዳማ ከፍተኛ ጫካ ነበር፡፡ መሃል ላይ ወንዝም አለ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤቱ ሰዎች ወሰዱኝ፣ ትምህርት ቤቱ የተሠራው መሃል ሜዳ ላይ ነው፡፡ ለእኔ ማደሪያ ቤት አልነበረም፡፡ እንደምንም አርሶ አደሩን በማስተባበር ቤት አሰርቼ መኖር ጀመርኩ፡፡ ለሶስት ዓመት እዛው በመምህርነት ሠራሁ፡፡

መንገዱ የማይመች በመሆኑ ወደ ከተማ በወር አንድ ጊዜ ደሞዝ ለመውሰድ እንኳን ችግር ነበር፡፡ ነገር ግን ከአውሬ ውጪ አካባቢው ሰላም ነበር፡፡ ሕዝቡም መምህር በመንገድ ላይ ሲገኝ ያከበር ነበር፡፡ በኋላ በዝውውር ወላይታ ገባሁ፡፡ ለስድስት ዓመታት ወላይታ ሆኜ ሳስተምር ጎን ለጎን እነግድ ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ሁሉ በኋላ ትምህርቶትን የቀጠሉት እንዴት ነው?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** መጀመሪያ ግልገል ጊቤ ሶስት ያለበት ኪንዶ ኮይሻ በሚባል አካባቢ ተመደብኩ፡፡ ቦታው በረሃ ነው፡፡ ከባድ ነው፡፡ እባብ ብዙ ጊዜ ይተናኮለን ነበር። ደጋግሜ ወደ ቤተሰቦቼ እሔዳለሁ፣ እነግዳለሁ፡፡ ቤተሰቦቼ ገፋፍተውኝ በ1984 ዓ.ም ጋብቻ መሠረትኩ፡፡ ባለቤቴ ከእኔም በላይ በጣም ልጅ ነበረች። በተከታታይ ሶስት ልጆች ወለድን፡፡ ሶስቱም አሁን ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ የመጀመሪያዋ ሃኪም ናት፡፡ አሁን ስፔሻሊስት ለመሆን እያጠናች ነው፡፡ ሁለተኛ ልጄ ወንዱም ኢንጂነር ሆኖ የዩኒቨርስቲ መምህር ነው፡፡ ትዳር መስርቷል፡፡ ሶስተኛዋ ፋርማሲስት ነች፡፡

ልጆች እያሳደግኩ ርቄ ሔጄ ትምህርት ለመማር አልቻልኩም፡፡ አለመማሬ ይቆረቁረኝ ነበር፡፡ የልጆቼ ነገር ያሳስበኛል፣ ባለቤቴ ደግሞ ልጅ ነበረች፡፡ ከአካባቢው ሰው ጋር መልካም ግንኙነት ነበረኝ፡፡ ማስተማር፣ መነገድ እና ልጆች ማሳደግ ቤተሰቦቼን በእርሻ ሥራ ማገዝ እነዚህን ተደራራቢ ሃላፊነቶች መወጣቴን ቀጠልኩ፡፡

በ1986 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ግን አዲስ ዕድል ተገኘ። የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ማስተማር ሊጀምር ነበር፡፡ አዲስ አበባ ሔጄ የምፈተንበት ገንዘብ አልነበረኝም፡፡ የፓርላማ አባል ለነበሩ አጎቴ ሳማክራቸው ፈተናውን ተፈተነህ ትምህርት ካልተማርክ ፊቴን እንዳታይ አሉኝ፡፡ ‹‹ገንዘብ ከሌለህ እኔ እሰጥሃለሁ፣ አሁኑኑ ሔደህ ተፈተን›› ብለው ገንዘብ ሰጡኝ፡፡ ፈተናውን ተፈትኜ አልፌ፣ኢኮኖሚክስ ተማርኩ። ስጨርስ ደቡብ ኦሞ ፕላን እና ልማት መምሪያ የሚባል ድርጅት ተመደብኩ። ስድስት ወር ሰርቼ በአጋጣሚ ኮሪያን ዴቨሎፕመንት ኢንስቲትዩት ለጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት የትምህርት ዕድል መስጠቱን ሰማሁ፡፡ ውጤቴ ጥሩ ስለነበር፣ ፍላጎት ካለህ መፈተን ትችላለህ ተብሎ ተነገረኝ፡፡

ለሁለተኛ ዲግሪ የመግቢያ ፈተና ወሰድኩ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ኮሪያ ሔድኩኝ፡፡ ከኮሪያ ዴቨሎፕመንት ኢንስቲትዩት በኢኮኖሚ ልማት ሁለተኛ ዲግሪዬን አገኘሁ። ኢንስቲትዩቱ በዛ ጊዜ የራሳቸውን የእድገት ተሞክሮ ለብዙ አገሮች ለማስተላለፍ ያቋቋሙት ሲሆን፣ አሁን ዩኒቨርስቲ ሆኗል፡፡ በዛ ጊዜ የተላክነው ኮሪያዎች እንዴት እንዳደጉ የልማት ተሞክሯቸውን አምጡ በሚል ነበር፡፡ የእነርሱ ዕድገት አንደኛው ጥሩ የተማሩ ሰዎች ተሳትፎ ማድረጋቸው እና የአሜሪካን ዕገዛም ታክሎበት ነበር፡፡ ብዙ መፅሃፍ አምጥቼ ለመንግሥት ሠጥቻለሁ፡፡

እንደመጣሁ የሄድኩት አርባ ምንጭ ሳይሆን፣ ‹‹ኮሪያ ተምሮ ስለመጣ ይጠቅመናል እዚሁ ይሁን›› ተብሎ ጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ገባሁ፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት የኢኮኖሚ አማካሪ ቡድን ሥር ሆኜ እሠራ ጀመረ፡፡ ነገር ግን እኔ እና ሌሎች አብረውኝ ተምረው የመጡ ሁለት ልጆች ነበሩ፡፡ አንዱ ወደ ንግድ ሚኒስቴር ሲገባ እኛ ሁለታችን ጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ቀረን፡፡

በጊዜው የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት (ኢ ዲ አር አይ) መንግሥት ለመመስረት ውስጥ ለውስጥ ሲሠራ ቆይቶ ነበር፡፡ ወዲያው የኢትዮጵያ ልማት ኢንስቲትዩት ተቋቋመ፡፡ በጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ውስጥ ሆነን ከ1992 ጀምሮ እንደ መሥራች ተቆጠርን፡፡ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ የሁለተኛ ዙር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነህ ተመረጥ ተባልኩ። ብዙም የፖለቲካ ፍላጎት ባይኖረኝም እምቢ ማለት አልቻልኩም። ምንም እንኳ የምክር ቤት አባል ብሆንም፣ አብዛኛው ሥራዬ እና ዝንባሌዬ የምርምር ሥራ ላይ ነበር፡፡ ለቀረበልኝ ጥያቄ አልፈልግም ማለት ስለማልችል፣ የምክር ቤት አባል ሆንኩኝ። ለአራት ዓመት በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ተመራማሪ እና የህዝብ ተወካዮች አባል ሆኜ ቆየሁ፡፡

ሁለቱን ሥራ አብሮ ማስኬድ ከባድ ነበር፡፡ በተለይ የምክር ቤት አባል መሆኔ ፈተና ሆኖብኝ ነበር፡፡ ገጠር በመኖሬ ጥሬ ሃቅ ላይ አተኩራለሁ፡፡ የፖለቲካ ነገር እንደማይሆንልኝ አሰብኩኝ፣ ችግሮች ሲያጋጥሙ ከመውደቅ ይልቅ በብልሃት ማለፍ ይሻላል ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ለመማር ፈለግኩ፡፡ ነገር ግን ማንም አይፈቅድልኝም ብዬ ፍራቻ አደረብኝ፡፡ ምክንያቱም የምክር ቤት አባልነትን ማቋረጥ አይቻልም፡፡ የትምህርት ዕድል ማፈላለግ ጀመርኩ፣ በአጋጣሚ በአራተኛው አመት የምክር ቤት ዘመን በክረምት ወደ ተመረጡበት አካባቢ የሚኬድበት ጊዜ ላይ መጀመሪያ ስውዲን የትምህርት ዕድል መጣልኝ፣ እርሱን ለመማር ገንዘብ ያስፈልግ ነበር፡፡ ያንን መክፈል አልቻልኩም፡፡

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

በሁለተኛነት ብዙ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ሰዎች የተማሩበት በደቡብ አፍሪካ የእርሻ ኢኮኖሚክስ ማዕከል የትምህርት ዕድል አገኘሁ፡፡ ነገር ግን ከምክር ቤት አባልነት መውጣት ከባድ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ብልሃት ያስፈልጋል። በቅድሚያ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ነዋይ ገብረአብን ጠየቅኩ፡፡ ምክር ቤቱ ከለቀቀህ እኔ አስተምርሃለሁ አሉኝ፡፡ ፓርላማ ሄጄ ‹‹ተቋሜ ሊያስተምረኝ ነው፤ ሄጄ ልማር›› ብዬ ስጠይቅ፤ ከተቋምህ ደብዳቤ አምጣ ተባልኩ፡፡ እኔ ተምሬ አገር እንዳገለግል የአንድ ዓመት የምክር ቤት ዘመን ይፈቀድልኝ ስል አመለከትኩ፤ ተቋሙ መማር እንዲችል ፈቅደንለታል የሚል ደብዳቤ ሰጠኝ፡፡ ለሶስተኛ ዲግሪ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሔድኩ፡፡ ለአራት ዓመት ተምሬ በጥሩ ውጤት ተመረቅኩ፡፡

በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ ትዳር ከመሰረትኩ በኋላ የባለቤቴ ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡ አራተኛ ልጅ ወልደን፤ አነስተኛ ንግድ እየሠራች፤ ልጆቼን የማሳደግ ሙሉ ሃላፊነት ወስዳ ልጆቼን ለቁም ነገር አድርሳለች፡፡ እኔም ኮሪያም፣ ደቡብ አፍሪካም ስማር ቤተሰቦቼ ከእኔ የሚያገኙት የመንግሥት ሰራተኛ ግማሽ ደሞዝ ነበር፡ ትምህርት ጨርሶ ልጅ ወልዶ ማሳደግ እና እየተማሩ ልጅ ማሳደግ በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ የባለቤቴ ድጋፍ ባይታከል እዚህ አልደርስም ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ገጠር ተወልዶ፤ ከቲ ቲ አይ ተነስቶ ሶስተኛ ዲግሪ ድረስ ለመማሬ ቁልፉ ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** የሰው ልጅ ጠንክሮ ከሠራ እና ባለበት ደረጃ ካልረካ በየጊዜው ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር ይችላል። እኔ አንድም ጥረት አደርጋለሁ። ከፊደል ቆጠራ ጀምሬ የጥናት ጊዜዬን አስተጓጉዬ አላውቅም፡፡ መማርና ማጥናት ከሚገባኝ በላይ አነብ ነበር፡፡ ሕይወቴን ለማሻሻል በተለያየ መልኩ እጥር ነበር፡፡ ትእግስትና ጥረት ጥሩ ነው፡፡

በቤተሰብም በሥራ ባልደረባም በሌሎችም በተለያዩ ሁኔታዎች ፈተናዎች ያጋጥሙኝ ነበር፡፡ ትዕግስት ባይኖረኝ እና በብልሃት ባልንቀሳቀስ ብዙ መጓዝ አልችልም ነበር። ሌላው ስለትምህርት ማሰብ ጥሩ ነው፡፡ ከወረዳ ወጥቼ በዓለም ላይ በትንሹ ከ18 ያላነሱ አገራትን አይቻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ስለተማርኩ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡-የምርምር ሥራ እንዴት ነው? ምን ያህል ምርምር አድርገዋል? በኢትዮጵያ የምርምር ተቀባይነት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** ምርምር በጣም አስደሳች ሥራ ነው። ምርምር ድብቅ የሆኑ ነገሮችን በሳይንስ ላይ ተደግፎ ተንትኖ ግኝቶችን ማቅረብ ነው፡፡ ሂደቱ ከባድ እና የብዙ ሰው ተሳትፎን የሚጠይቅ ነው፡፡ ከትምህርት ቤት ወጥቼ ግብርና እና ገጠር ልማት ላይ ጥናት የማካሔድ ሥራ ስሰራ ነበር። በዚህ በምርምር ሥራ 30 የሚደርሱ የምርምር ሥራዎችን ለህትመት አብቅቻለሁ። አብዛኛዎቹ ግብርና ላይ ሲሆኑ፤ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ምርታማነት፣ ግብይት፣ የምግብ ዋስትና እና ሌሎችም ከግብርና ጋር የተያያዙ ናቸው።

ቀድሞም ቢሆን የመጀመሪያ ዲግሪዬንም ስማር የመሬት መጠን እና የምግብ ዋስትና ላይ ያተኮረ ነበር። የሁለተኛ ዲግሪዬንም የሰው ሃይል ብዛት እና ልማት ለይ የሚያተኩር ነበር። ኮሪያዎች አንድም አገራቸውን ያሻገሩት በትምህርታቸውም ጭምር ነው፡፡ የሶስተኛ ዲግሪዬን የግብርና ምርት ግብይት ላይ ያተኮረ ነበር። በዋናነት ቡና ላይ ያተኮርኩ ሲሆን፤ የመንግሥት ቁጥጥርን እና የገበያ ሁኔታው ላይ ተመርኩዤ ነበር፡፡

በእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ተቀባይነት ያገኙ እና በመንግስት ፖሊሲ ውስጥ የተካተቱ ነበሩ፡፡ በተለይ ገና ምርምር እንደጀመርኩ ከዓለም ባንክ እና በወቅቱ ከኢትዮጵያ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ጋር የሠራነው ቀደም ሲል በጀቱ ለክልል ሲሰጥ ክልል የራሱን ቀንሶ ለዞን፣ ዞንም የራሱን ቦጭቆ ለወረዳ፣ እታች ሲደርስ ሥራ ላይ የሚውለው ትንሽ ነበር፡፡ በጥናት ግኝቱ በመመርኮዝ ሁሉም እንደየደረጃው እንዲሰጠው ሲደረግ ወረዳ የተሻለ ሥራ ላይ የሚውል ገንዘብ ማግኘት ጀመረ፡፡

ሌላው የታክስ መጠንን መቀነስ እና የሰፋፊ እርሻዎች ውጤታማነት ላይ በእኔ መሪነት ጥናት ተጠንቶ በመንግስትም ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። በተጨማሪ የዓየር ንብረት ለውጥ እና የቤተሰብ የመቋቋም አቅም ላይ ጥናት አካሒደናል። አየሩ እየተለወጠ፤ የማይታወቁ በሽታዎች እየተስፋፉ በመሆኑ እነዚህን ችግሮች እንዴት መቋቋም ይቻላል? የሚል ጥናት በእኔ መሪነት እያጠናን ነው፡፡ አራት አመት ሆኖናል። ሌላው አሁን ማንም እንደሚያውቀው የዋጋ ግሽበት አለ፡፡ የዋጋ ግሸት መንስኤው ምንድን ነው? ምን መሠራት አለበት በሚለው ላይም ጥናት አጥንተን ለመንግሥት አቅርበናል። ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የፖለቲካ ለውጡ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ላይ ያስከተለው ጫና ላይ በማተኮር ሠርተን መሠራት ያለበትን ለመንግሥት አቅርበናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በምርምር ሥራ ውስጥ ያለው ፈተና ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በዚህ ሁሉ ውስጥ ያለው ፈተና ጥናት ወዲያውኑ ተቀባይነት ይኖረዋል ብሎ መናገር ከባድ ነው። ዓለም አሁን ላለችበት ደረጃ የደረሰችው ዕውቀት ተይዛ ነው። ዕውቀትን ማዕከል አድርጎ መሔድ ለሀገር እና ለሕዝብ ይጠቅማል፡፡ ምርምር ብዙ ፈተና አለው፤ ተቀባይነቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ነው፡፡

ሰዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው አንደኛው ነው፡፡ ለምሳሌ አሁን ላይ የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ላይ የሚካሔድ ጥናት አለ፡፡ በዓለም ባንክ እና በግብርና ሚኒስቴር የሚሠራ ሲሆን፤ በየዓመቱ ምን ውጤት መጣ በሚል ሥራው ይሠራል፡፡ ነገር ግን መረጃ ለመሰብሰብ ስንሔድ አርሶ አደሩ እና ተጠቃሚው ፈቃደኛ ሆኖ መረጃ ካልሠጠ በጣም አስቸጋሪ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሕዝብ ጥናት ለማካሔድ የሚረዳ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለም። መንግሥት ደግሞ ጥናትን በመቀበል በኩል ውስንነት አለበት ማለት ነው? ስለዚህ ከላይም ከታችም ችግር ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በጥናት ላይ በርከት ያለ ችግር አለ። ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች መኖራቸውን መካድ አይቻልም፡፡ በመንግስት በኩል በዚህ ላይ ጥናት አካሒዱ፤ ይህንን አድርገናል ምን ውጤት መጣ? አጥኑልን የሚሉ ጥያቄዎች ይቀርባሉ። ከየመንግስት መስሪያቤቶችም ጥናት አጥኑልን ይባላል፡፡ አሁን ያለው ፍላጎት እና ትኩረት ከአስር ዓመት በፊት ከነበረው ጋር ይለያያል፡፡ ነገር ግን አሁንም ትልቁ ፈተና ምርምር ብዙ መረጃዎች መሰብሰብን ይፈልጋል፤ መረጃ ማግኘት በጣም ችግር ነው፡፡

አንዳንድ ተቋማት መረጃ አይሰጡም፡፡ ጤና ጥበቃ ወይም ግብርና ሚኒስቴር የሰበሰበው መረጃ ቢኖር ለሌሎች አካላት የሰበሰበውን መረጃ አያጋራም። ይሄ ትልቅ ችግር ነው። ብዙዎች ተመራማሪዎችን በጣም ያመላልሳሉ፡፡ ለምሳሌ ግጭቱ እና ያስከተለው ጉዳትን በተመለከተ ጥናት ስናካሔድ በተቋም ደብዳቤ ፅፈን ብንመላለስም የመንግስት ተቋማት እና የሃይማኖት ተቋማት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ይሔ የመረጃ ውስንነት ይፈጥራል፡፡ ሲያያዝ አንዳንድ ጊዜ ጥናቱ ላይ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ሌላው ጥናት ለመስራት ሁሉንም ኮርነሮችን ማየትን ይጠይቃል፡፡ አንድ ሰው ጥናቱ እስከሚያስፈልግበት ጫፍ ድረስ መሔድን ይጠይቃል፡፡ ለእዚህ ምቹ የፀጥታ ሁኔታ የለም። ይህ በጥናታችን ላይ ከፍተኛ እንቅፋት ፈጥሯል። ደህንነት በማይጠበቅበት ሁኔታ መረጃ ሰብሳቢ ባለሙያ መላክ ከባድ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሚካሔዱ ጥናቶች ሳለመተግበራቸው አንደኛው ምክንያት የጥናት ጥራት ችግር መሆኑ ይነገራል፡፡ አንዳንድ ምርምሮች ለመመረቅ ብቻ ወይም ሥራ ተብሎ እንጀራ ስለሚበላባቸው ብቻ እንደሚካሔዱ ይታሰባል፡፡ በእርግጥ በእርሶ እምነት በኢትዮጵያ ምርምር በትክክል ችግር ለመፍታት ወይም አዲስ ነገር ለማግኘት እየተካሔደ ነው?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በእርግጥ የጥናት ጥራት በጣም ወሳኝ ነው። አንድ ሰው ያጋጠመውን በሽታ ለማወቅ በተደጋጋሚ ምርመራ ሳይካሔድ እና በሽታው ሳይለይ በግምት ሕክምና ከተጀመረ ውጤቱ በሽተኛውን ከማዳን ይልቅ መግደል ይሆናል፡፡ ጥናትም ተመሳሳይ ነው። በግምት በሽታ ማዳን አይቻልም፡፡ በቂ መረጃ እና ዕውቀት ሳይኖር በተካሔደ ምርምር ምክረ ሃሳብ መስጠት በሽተኛውን አድናለሁ ብሎ እንደመግደል ነው።

ምርምር ዓይነት ብዙ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሯቸው ብዙ ምርምሮች አሉ፡፡ የዩኒቨርሲቲዎች ጥናት የዕውቀት ፍላጎትን ለማሟላት ነው፡፡ ይህኛው ግን የፖሊሲ ምርምር ነው፡፡ ይህኛው ምርምር ሁልጊዜ የሚመነጨው ከፍላጎት ነው፡፤ ስለዚህ ሁልጊዜም ጥናት ከማድረጋችን በፊት የመንግሥት ተቋማትንና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን እንጠይቃለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከመንግሥት ከራሱም አጥኑልን የሚል ጥያቄ ይቀርባል፡፡ ለምሳሌ የነዋሪዎች የኢኮኖሚ ለውጥ ምን ይመስላል ዳሰሳ አድርጉልን የሚል ጥያቄ ይቀርባል። ሌላው በተመራማሪዎች በኩልም ሃሳብ ይነሳል፡፡ ነገር ግን በዋናነት እንደተጠቀሰው ከሁሉም በፊት ጥራት ይቀድማል፡፡

መጀመሪያ የተሰበሰበው መረጃ በቂ ነው ወይ? ሽፋኑ ትክክል ነው ወይ? ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ምን ያህል ተሳትፈዋል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይፈልጋሉ። ይህ ተቋም ፌዴራል ነው፡፡ የሚሰበሰበው መረጃም ፌዴራልን የሚወክል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ስለግብርና ሲጠና የአንድ ክልልን ብቻ ወስዶ በሀገር ደረጃ እንደተሰራ መታሰብ የለበትም፡፡ ከሀገር አንፃር ከታየ ጥልቅ መሆን አለበት፡፡

በሌላ በኩል የጥራት ጉዳይ ሲነሳ የወጪ ጉዳይም መታሰብ አለበት፡፡ በጥራት ለመስራት ሽፋንን ማስፋት ያስፈልጋል። በጉዳዩ ላይ ብዙ የሚመለከታቸውን ሰዎች መጋበዝ እና ማሳተፍ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ ወጪ አለው። ስለዚህ ብዙ ጊዜ የምናካሂዳቸው ጥናቶች ናሙናን በመውሰድ ነው፡፡ ናሙናው ወካይ መሆን መቻሉ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ከሚፈለገው ሕዝብ ውስጥ ወካይ የሆነ ሰው መምረጥ የግድ ነው፡፡ ለአምስት ሺህ ሰው አንድ ሰው እንጠይቃለን፡፡ አምስት ሺውንም ሰው ብንጠይቅ ተመሳሳይ ሃሳብ እናገኛለን ብለን የምንሠራቸው ጥናቶች አሉ፡፡

እዚህ ተቋም ላይ ከጥናት ጋር በተያያዘ መጀመሪያ ከእኛ በፊት የተጠኑ ጥናቶችን በደንብ እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ የጥናቱ አስፈላጊነት እና የሚጠናበት መንገድ ምን ያህል ያስኬዳል የሚለው በቅድሚያ በባለሞያዎች ታይቶ ይተቻል፡፡ መስክም ተሔዶ ይታያል፡፡ በዚህ ዓይነት ተገምግሞ ወደ ውጪ ይሔዳል። ስለዚህ ጥራቱን በደንብ እናየዋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡-የዋጋ ግሽበት ላይ ጥናት አካሂዳችኋል። በትክክል ተጨባጭ መንስኤው ምንድን ነው? መፍትሔ ብላችሁ ያስቀመጣችሁትስ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** የዋጋ ግሽበት መኖሩን መካድ አይቻልም። የዋጋ ግሽበት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ብለን ከተነሳን በሁለት መልኩ መታየት አለበት፡፡ አንደኛው መሠረታዊ ምክንያት ሲሆን፤ ሌሎች አባባሽ ምክንያቶችም አሉ፡፡ መሠረታዊው ጉዳይ በዚህች ሀገር የፍላጎት መጠን ከአቅርቦት መጠን ፈጥኖ አድጓል። ፀጥታ እና ሠላም ቢኖርም የምርት ፍላጎት እና አቅርቦት ካልተመጣጠነ የዋጋ ግሽበት መከሰቱ የማይቀር ነው፡፡

ከተሞች እጅግ በጣም ተስፋፍተዋል፡፤ በስፋት ፋብሪካዎች አሉ፡፡ ምርት ቢመረትም በሚፈለገው መጠን አላደገም፡፡ ስለዚህ የዋጋ ግሽበት ቁልፉ ከጀርባው ካሉት አባባሾች በፊት መሠረታዊው የምርት አቅርቦት ተመጣጣኝ አለመሆን ሲሆን የእዚህ ምክንያት ደግሞ የግብርና ዘርፍ አለማደግ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ግብርና ላይ ነባር ከሆኑ ዋጋዎች በተጨማሪ አርሶ አደሩ ማዳበሪያ፣ ፀረ ተባይ እና ምርጥ ዘር ይገዛል፡፡ የሚያርሰው ሰው ጉልበት ዋጋ አለ፡፡ ይህ ሁሉ ሲደማመር የማምረቻ ወጪ ጨምሯል፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ምክንያት ግብርና በሚፈለገው መጠን ባለማደጉ ፍላጎት እና አቅርቦት ሊጣጣሙ አልቻሉም፡፡

አባባሽ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከአባባሽ ምክንያቶች መካከል መሬት ላይ ያለው ምርት መጠን አነስተኛ ስለሆነ የገበያ ሥርዓታችን ተበላሽቷል፡፡ ገበያው ባለቤት የለውም። የገበያ ሥርዓት አደረጃጀት ደካማ ከመባልም በላይ ቦታው ላይ የለም ማለት ይሻላል፡፡ በየመጋዘኑ ጣራ የነካ ክምችት እያለ፤ ገበያ ላይ ምግብ የለም፡፡ ስለዚህ መሠረታዊ ምክንያቱ በአገር ደረጃ የገበያ ሥርዓታችን ለተፈጠረው የዋጋ ግሽበት አንደኛው ምክንያት ነው፡፡ ሰዎች ያገኙትን ሁሉ መደበቅ ባህል አድርገውታል፡፡ አገራዊ እና ማህበራዊ ሃላፊነት የማይሰማቸው ነጋዴዎች ምርት መደበቃቸው፤ አሁን ላለው የዋጋ ግሽበት ሌላኞቹ ምክንያት ነው፡፡ ምርቱ በበቂ መጠን ሳይኖር፤ ከእርሱም ላይ መደበቁ ግሽት አስከትሏል፡፡

የገንዘብ የመግዛት አቅም እየወረደ መምጣትም ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡ ሰው ገንዘብ ከሚያስቀምጥ ሁለት ኩንታል ጤፍ ቢገዛ ይመርጣል፡፡ ምክንያቱም ዋጋው በየቀኑ ስለሚያድግ ዕህል መያዙ ገንዘብ ከመያዝ ይሻላል ብሎ ያስባል፡፡ ይሔም በራሱ አንድ አባባሽ ምክንያት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በየትም ዓለም የሌለ ተጨባጭ ምክንያት የሌለው የዋጋ ጭማሪ ይደረጋል። ለምሳሌ ግማሽ ሊትር ወተት ከ10 ብር በአንድ ጊዜ ወደ 50 ብር አድጓል። ይሔ እውነት በጥሬ ዕቃ ችግር ነው? ይሔ ያጠያይቃል። መንግሥት የገበያ ሥርዓቱን በደንብ መፈተሽ አለበት፡፡

ሌላኛው የፀጥታ መናጋት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በብዙ መልኩ የሚታይ ነው፡፡ አንዳንዱ ማምረት የሚችል እና ሀገር የሚመግቡ አርሶ አደሮች ማምረት አቁመዋል፡፡ ተመፅዋች ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ምርት ቢመረትም በፀጥታው ችግር ምክንያት ወደሚፈለግበት አካባቢ ማጓጓዝ አይቻልም፡፡ ይህኛው ደግሞ ሌላኛው ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ ወለጋ አካባቢ በቆሎ ሲመረት ነበር፡፡ ወላጋ ላይ አንድ ኩንታል አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር እየተሸጠ አዲስ አበባ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ብር ሲሸጥ ነበር፡፡ ምክንያቱም ትራንስፖርት ላይ ችግር አለ፡፡

የገንዘብ አስተዳደር ጉዳይ ደግሞ ሌላኛው አባባሽ ምክንያት ነው፡፡ ከሚመረተው በላይ ገበያ ላይ ገንዘብ ከተረጨ የዋጋ ግሽበት ያጋጥማል፡፡ በእርግጥ አሁን ገንዘቡ ያዝ እየተደረገ የተወሰኑ ለውጦች እየታዩ ናቸው፡፡ ጠቅለል ሲደረግ ግን በዋናነት ከምርት አቅርቦት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ብዙ ነገር አለ፡፡ የወተት ላም እንክብካቤ ስታገኝ የምትሰጠው ወተት ይጨምራል፡፡ ግብርናም ተመሳሳይ ነው፡፡ በወሬ ብቻ የሚገኝ ነገር የለም፡፡ ዋናው ነገር ግብርና ላይ በስፋት ኢንቨስት ማድረግ እና መሥራት ነው፡፡ ለግብርና የሚሠጠው ትኩረት ከፍ ካላለ ጠብ የሚል ነገር አይኖርም፡፡ ከላይ ከላይ በንግግር ደረጃ ሳይሆን መሬት ላይ የሚወርድ ነገር መሥራት አለበት፡፡

የተገነቡ የመስኖ ሥራዎች ምን ያህል ውጤታማ ሆነዋል? ምን ያህሎቹ ተሠራባቸው የሚለው መታየት አለበት፡፡ የግብርናን ስፋት እና አስፈላጊነትን ያህል ለግብርና ትኩረት መሠጠት አለበት፡፡ የሚሰጠው ትኩረት በቂ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ኩታ ገጠም ላይ መንግሥት ዘር ያቀርባል ማዳበሪያም ይሠጣል፤ ሰፊ ቦታዎች ላይ ትራክተርም ሠጥቷል፡፡ እነርሱ የተሻለ ውጤታማ ሲሆኑ ታይተዋል፡፡ የውጤታማነታቸው ምንጭ የተሠጣቸው ትኩረት ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ሌላው አባባሽ ጉዳይ ለግብርና የተሠጠው ትኩረት አናሳነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በደንብ መታወቅ ያለበት፤ የምግብ ዋጋ ግሽበት የድሃ ድሃውን ይገድለዋል፡፡ ምንም ዓይነት ቋሚ ገቢ የሌላቸው ጡረተኞች በረሃብ እንዳይሞቱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ግጭት ባለባቸው ቦታዎች ያለው የዋጋ ግሽበት በጣም ከባድ ነው፡፡ ነገር ግን በሌሎች ከተሞች ያለው የዋጋ ግሽትም ቀላል አይደለም፡፡ በጣም ከባድ ሁኔታ በመኖሩ የድሃ ድሃዎችን በቅርበት ማየት ይገባል፡፡ ሰው የሚበላውን ዳቦ መግዛት ሲያቅተው ሁኔታው በጣም አስፈሪ ይሆናል፡፡ እኔ የምለው የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር የግድ የንግድ ሥርዓቱን በደንብ መፈተሽ እና በስፋት ግብርና ላይ ኢንቨስት ማድረግ ለይደር መቆየት የሌለባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡



# ጨረታ

## ለንብረቶ ተገቢውን ዋጋ ያግኙ!

### ስካን በማድረግ ይጫረቱ ያሸንፉ!

auction.com.et

# ኦክሽን ኢትዮጵያ

**ጥቅሞቹ**

በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ መጫረት ይችላሉ።
የጊዜ የጉልበት እና የገንዘብ ብክነት ይቀንሳል።
በአንድ ጊዜ በርካታ ጨረታዎችን ያጫርታል።
ለንብረቶ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኙ ያስችላል።

**ለተጨማሪ መረጃ**

+251905115511
info@auction.et
www.auction-ethiopia.com
Bole Atlas, Around EU, kelela Building.
3rd floor, suite 301 Addis Ababa

**መተግበሪያውን ያውርዱ**

Download on the App Store
GET IT ON Google Play

ዜና

# በዞኑ ከ466 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ገብተዋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት ሦስት ወራት 466 ሚሊዮን 300 ሺህ ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ መግባታቸውን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የወላይታ ዞን አስተዳደር ገለጸ፡፡

የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሩብ ዓመቱ አጠቃላይ ካፒታላቸው 466 ሚሊዮን 300 ሺህ ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 11 ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

ወደ ሥራ እንዲገቡ ፈቃድ የተሰጣቸው 11 ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው በአማካኝ ከ80 እስከ 100 ሚሊዮን ብር ካፒታል ማስመዝገባቸውን አስረድተዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የተሠማሩባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች በዋናነት በግብርና ሥራ ሲሆን፣ የግብርና ምርቶችን በማቀነባበር፣ በአገልግሎትና በማዕድን ቁፋሮ ዘርፍ የተሠማሩ አልሚዎች መኖራቸውን አስታውቀዋል።

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በርካታ ባለሀብቶች ለማልማት ጥያቄ ያቀረቡ በሆንም፤ ክልሉ አዲስ እየተዋቀረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጥያቄውን ተቀብሎ በፍጥነት ጉዳዩን ለማስጨረስ ችግር አጋጥሟል ብለዋል።

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ወደ ሥራ ለማስገባት የታቀዱ ከ100 በላይ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን አንስተው፤ ፕሮጀክቶቹ ለክልል ቀርበው እንዲፀድቁ የሚደረግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሂደቱ ላይ መዘግየት መፈጠሩን አመልክተዋል።

ከባለሀብቶቹ የተነሳው የእናልማ ጥያቄ ቀደም ብሎ የቀረበ ቢሆንም፤ የቀድሞ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ለሁለት ተከፍሎ በአዲስ መልክ በመዋቀሩ የተነሳ ፕሮጀክቶቹ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት ቀርበው እንዲፀድቁ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

አዲሱ ክልል ገና እየተደራጀ ከመሆኑም ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቶችን መርምሮ ፈቃድ የሚሰጥ ባለሙያ እጥረት በማጋጠሙና በሌሎች ችግሮች ምክንያት መጓተቶች መከሰቱን ጠቁመው፤ ችግሩን ፈትቶ ብዛት ያላቸውን አልሚዎች ወደ ሥራ ለማስገባት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ከባለሀብቶች የመልካም አስተዳደር ቅሬታ እየቀረበ መሆኑን የተናገሩት አቶ ሳሙኤል፤ ዞኑ ጥያቄዎቹ በፍጥነት ምላሽ እንዲያገኙ ከክልሉ ጋር በመተባበር እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በ2016 በጀት ዓመት በዞኑ ከ200 በላይ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት እቅድ መያዙን አስታውቀው፤ ዞኑ በግብርና በርካታ ፀጋዎች ያሉት በመሆኑ ሰፊ ዕድል እንዳለው ተናግረዋል።

ወደ ወላይታ ዞን በርካታ ቱሪስቶች ለጉብኝት እንደሚመጡ አስታውሰው፤ በአገልግሎት ዘርፉ ሰፊ የሥራ ዕድልና ገቢ መፍጠር የሚቻልበት አማራጭ መኖሩን አስገንዝበዋል።

በአካባቢው በርካታ የማዕድንና የተፈጥሮ ሃብት እንዲሁም ለባለሀብቶች ምቹ ዕድል የሚፈጥሩና ለንግድ የእንቅስቃሴ አማራጭ የሆኑ የተለያዩ መንገዶች በመኖራቸው ወደዞኑ ለማልማት የሚመጡ ባለሃብቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሰፊ ዕድል እንዳለ አመላክተዋል።

# በምክክሩ የራስ ሀሳብን ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ወገን ማድመጥ ያስፈልጋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በሀገራዊ ምክክሩ የራስ ሀሳብን ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን የሌላውን ወገን ሀሳብ ለማድመጥና ለመረዳት መዘጋጀት ያስፈልጋል ሲሉ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የአመራርና አስተዳደር ኮሌጅ ምክትል ዲን መሐመድ አሊ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

መሐመድ አሊ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በእውነተኛ ውይይት ላይ ተመሥርቶ መግባባት ላይ ለመድረስ ሀገራዊ ምክክሩ ወቅቱን የጠበቀና አስፈላጊ ነው። በምክክሩ የራስ ሀሳብን ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ወገን ሀሳብ ለማድመጥና ለመረዳት መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ያስችላል፡፡

በምክክር ሂደቱ ደግሞ አጀንዳ ያላቸውን አካላትን ሁሉ በፍትሐዊነት በማሳተፍ ገንቢ ውይይት እንዲደረግ ማገዝ ይገባል ያሉት ዶክተር መሐመድ፤ ኮሚሽኑ በምክክሩ ያገባኛል የሚሉትን ወገኖች ሁሉ ያሏቸውን ችግሮች በውይይት ለመፍታት ከወገንተኝነት ነፃ ሆኖ መሳተፍ ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

እንደሀገር ያሉት ችግሮች ዛሬ ላይ የተፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ከትናንት ወደ ዛሬ የተሻገሩ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በፖለቲካ ሥርዓቶች፤ በታሪክ፤ በባንዲራና ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ በርካቶች አከራካሪ ሀሳብ እንደሚያነሱና ዕይታው የተለያየ መሆኑን አንስተዋል።



**መሐመድ አሊ (ዶ/ር)**

በሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም አካታች ባደረገ መልኩ ውይይቶችን በማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የምክክር ኮሚሽኑ መድረኮች ሚናቸው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል።

የምክክር ኮሚሽኑ ለውይይት የሚቀርቡ አጀንዳዎችን እየሰበሰበ መሆኑን አሳውቋል ያሉት ዲኑ፤ ተሳታፊ አካላትም ጎራ ከመለየት እሳቤ ወጥተው በፍትሐዊነት በመሳተፍ ውጤታማ ሥራ ለሀገራቸው ለማከናወን መዘጋጀት አለባቸው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እንደ ዶክተር መሐመድ ገለጻ፤ ከሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት አንጻር በሀገር ደረጃ በርካታ የወል እሴቶች አሉ። የተለያዩ ብሔሮች ቢኖሩም በጋብቻ፤ በንግድ፣ በባሕል መተሳሰር ተፈጥሯል፡ በመሆኑም አንድ የጋራ ሀገር አለን በሚል እሳቤ ውይይቱን ማከናወን ይገባል፡፡

የራስ ሀሳብን ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን፤ የሌላውንም ወገን ሀሳብ በማዳመጥና በመረዳት በሰከነ መንገድ መወያየትና፤ ውጤቱም ሁሉንም አካል ተሳታፊ ሊያደርግ ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በየደረጃው ወደሚገኙ የወረዳ መዋቅሮች በመውረድ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ማወያየት እንዲሁም ምሑራንን በተመረጡ ጉዳዮች ላይ በማወያየት በጥናት ላይ የተመረኮዘ መፍትሔ ማበጀት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ሁሉንም አሳታፊ በማድረግ ከየሃይማኖቱ፤ ከሴቶች፤ ከብሔር ብሔረሰቦች ፤ከታሪክ እና ከሌሎች ዘርፎች አንጻር የተመረጡ ሰዎችን በመውሰድ አሳታፊነቱ የተረጋገጠ ምክክር ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚስተዋሉ አለመግባባቶች ለምክክር ኮሚሽኑ ሥራ ተግዳሮት ቢሆንም፤ በተደራጀ መልኩ በቂ የሰው ኃይል በሟሟላት ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ማድረግ እንደሚቻል ጠቁመዋል።

ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ችግር ባይኖርበትም፤ የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል፣ አንዳንድ የፖለቲካ ምሑራንና አመራሮች፤ እንዲሁም የማኅበረሰብ አንቂዎች (አክቲቪስቶች) የራሳቸውን ሀሳብ ወደ ሕዝብ በማንጸባረቅ ችግር ስለሚፈጥሩ፤ በተቻለ አቅም እነዚህን አካላት በሀገራዊ ምክክሩ አቀራርቦ ማወያየት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

# የዋጋ ግሽበቱን ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ ላይ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ገበያ ባለቤት ያለው አይመስልም፡፡ የገበያ ሥርዓት አደረጃጀቱ ደካማና በደላላ የሚመራ ነው፡ ፡ በዓለም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ያለተጨባጭ ምክንያት በአንዳንድ ምርቶች ላይ እጅግ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ሲታይ ተከታትሎ የሚጠይቅ የለም፡፡ ከዚህ አኳያ በዘላቂነት የዋጋ ግሽበቱን ለማርገብ በሀገር ደረጃ ምርታማነትን መሳደግ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የገበያ ሥርዓቱ ፈትሾ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

የገበያ ሥርዓት አደረጃጀት ችግር የዋጋ ግሽበቱን እንዳባባሰው ጠቅሰው፤ በተደጋጋሚ ሲገለፅ እንደነበረው ግብርና ላይ በበቂ መጠን ኢንቨስት አለመደረጉ እና ከአቅርቦቱ በላይ ፍላጎት ፈጥኖ ማደጉ ሀገርን የዋጋ ግሽበት ፈተና ላይ ጥሏታል ብለዋል፡፡

በተለይ ማኅበራዊ ኃላፊነት የማይሰማቸው ነጋዴዎች ምርት መደበቃቸው እና አቆይተው እያወጡ በተጋነነ ዋጋ ማቅረባቸው፤ በዚህ ላይ ተጠያቂነት አለመኖሩ የዋጋ ግሽበቱን እንዳባባሰውም አብራርተዋል፡፡

የዋጋ ግሽበት ላይ ጥናት ማካሔዳቸውን የጠቆሙት የኢኮኖሚ ምሑሩ ታደሰ (ዶ/ር)፤ ግብርና ላይ ነባር ከሆኑ ዋጋዎች በተጨማሪ አርሶ አደሩ ማዳበሪያ፣ ፀረ ተባይ እና ምርጥ ዘር መጠቀሙ እንዲሁም የሚያርሰው ሰው ጉልበት ዋጋ መጨመር በራሱ የዋጋ ልዩነት እንደሚፈጥር ተናግረዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን አሁን ያለው ጭማሪ ከምርት ወጪው በላይ የተጋነነ በገበያ ሥርዓቱ ብልሽት ምክንያት የተባባሰ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ምርት ቢመረትም በሚፈለገው መጠን አለማደጉ ብቻ ሳይሆን፤ የፀጥታ እና የሠላም መደፍረስ ሀገር የሚመግቡ አርሶ አደሮች ማምረት ማቆማቸው እና ተመፅዋቾች መሆናቸውም ሌላኛው ችግር መሆኑን ጠቁመዋል። ምርት በፀጥታው ችግር ምክንያት ወደ የሚፈለግበት አካባቢ ማጓጓዝ አለመቻልም የዋጋ ግሽበት ሌላው ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የገንዘብ አስተዳደር ችግር ማለትም የገንዘብ የመግዛት አቅም እየቀነሰ መምጣት እና ከሚመረተው በላይ ገበያ ላይ ገንዘብ መርጨት የዋጋ ግሽበት አስከትሏል ያሉት ታደሰ (ዶ/ር)፤ አሁን ገንዘብ ያዝ በመደረጉ የተወሰኑ ለውጦች እየታዩ መሆናቸውን ማስተዋል አያዳግትም ብለዋል፡፡

‹‹የምግብ ዋጋ ግሽበት ጉዳቱ ቀላል ሳይሆን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል፡፡ ይህን ጫና ለማቃለል የዋጋ ግሽበትን ለማርገብ የገበያ ሥርዓቱን ችግሮች ፈትሾ ማስተካከል ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን እንደሌለበት አስገንዝበዋል፡፡

ግጭት ባለባቸው ቦታዎች ያለው የዋጋ ግሽበት በጣም ከባድ መሆኑንና በሌሎች ከተሞች ያለው የዋጋ ግሽበት ቀላል እንዳልሆነ አስታውሰው፤ የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር የግድ የንግድ ሥርዓቱን በደንብ መፈተሽ እና በስፋት ግብርና ላይ ኢንቨስት ማድረግ ለይደር መቆየት የሌለባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

# በኢትዮጵያ ከ360 ሚሊዮን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሙሉ ለሙሉ እየተጠቀሙ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል። ከጥራት አንጻር በሀገሪቱ የሚመረተው የድንጋይ ከሰል ኢነርጂ የማቃጠል አቅሙን ለማሳደግና የእርጥበት ሁኔታው ላይ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ ለማምረት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የድንጋይ ከሰል የጥራት ደረጃዎችን በማሟላት የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ጨምሮ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች ምርቱን እንዲጠቀሙ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አቶ ሚሊዮን እንደተናገሩት፤ የተፈለገውን ጥራት ለማምጣት የተለያዩ የማዕድን አውጪ ኩባንያዎች እየሠሩ ይገኛል፡፡

ኢቲ ማይኒግ የተሰኘው ኩባንያ በዳውሮ ዞን አካባቢ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና ኦሮሚያ ክልል በተመሳሳይ የሚንቀሳቀሱ አምራቾች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በድንጋይ ከሰል ምርት ላይ ለመሥራት ግዙፍ ኢንዱስትሪ እያቋቋመ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የድንጋይ ከሰል በሚለማበት ወቅት ከሌላ ነገር ጋር ሳይቀላቀል ጥራቱን ጠብቆ እንዲመረት ለማድረግ የሕንድ ኩባንያ ፕሮጀክቱን ይዞ እየሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ልማት ላይ የሚሠሩ ዘጠኝ ኩባንያዎች የሚገኙ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ በሰላም ችግር ሥራቸውን እያደናቀፈው ይገኛል፡፡

የድንጋይ ከሰልን የሲሚንቶ ፋብሪካዎች፤ የሴራሚክ ኢንዱስትሪዎች፣ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች፣ የመስታወት ፋብሪካዎችና የብረት ኢንዱስትሪዎች ለተለያየ ግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት አስረድተዋል።

የማዕድን ሚኒስቴር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ የታጠበ የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ ለመተካት በ2014 ዓ.ም በተመረጡ ቦታዎች ለስምንት ሀገር በቀል ኩባንያዎች ፈቃድ መስጠቱ ይታወሳል።

በቅርቡ በተካሄደው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ስብሰባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የድንጋይ ከሰል ምርትን በሀገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሸፈን መቻሉ የውጭ ምንዛሪ ማዳን መቻሉን መግለጻቸው የሚታወስ ነው፡፡

# ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደሆነ የገለጹት ሥራ አስፈጻሚው፤ ብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በቅርቡ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል በሰጠው መረጃ መሠረት ሥራው በቅንጅት እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ሥራ አስፈጻሚው እንዳሉት፤ ፀሐያማና ደረቅ በሚሆንበት ወቅት አመራሩን ጨምሮ አርሶ አደሩ አካባቢ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍሎችና የግብርና ባለሙያዎችን በማስተባበር የደረሱ ሰብሎች የመሰብሰብ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት በሰብል ከተሸፈነው 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ሰብል ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ ውስጥም 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል፡፡ የተሰበሰበው የሰብል ምርት በተለይም በቆላማና ፀሐያማ አካባቢዎች ሲሆን፤ አጠቃላይ ሰብል የመሰብሰብ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚሰጠውን ትንበያና የባለሙያዎችን ምክረ ሀሳብ ተከትሎ የሰብል አሰባሰብ ሂደቱ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የደረሱ ሰብሎች እንዳይበላሹ ፀሐይና ደረቅ በሚሆንበት ወቅት አጠቃላይ ኅብረተሰቡን በማስተባበርና የግብርና ሜካናይዜሽንን በመጠቀም ብክነትን ለመከላከል እየተሠራ እንዳለም አመልክተዋል፡፡

መኸር ላይ የተዘራው ሰብል የመድረሻው ወቅት ላይ እንገኛለን ያሉት አቶ ከበደ፤ በቀጣይ ወቅት በመደበኛ መስኖ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚሠሩ የግብርና ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል፡ ፡ በዚህም በበጋ መስኖ ስንዴ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት እየተሠራ እንዳለም ተናግረዋል፡፡

የደረሱ የመኸር ሰብሎችን በመሰብሰብ ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ስንዴን የማልማቱ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

ከበጋ መስኖ ስንዴ ጋር በተያያዘም በባሕላዊና በትራክተር በመታገዝ የማረስና መሬቱን ለዘር ዝግጁ የማድረግ ሥራዎች መሠራታቸውንና አሁን ላይ ከ500 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ በዘር መሸፈኑንም ጠቁመዋል፡፡

አዳዲስ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ምርታማነትን ማሳደግ በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይም ለአርሶ አደሩ ግንዛቤ እየተሰጠ እንዳለም ገልጿል፡፡

በመኸር እርሻ በዘር ከተሸፈነው 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ 513 ሚሊዮን ኩንታል የእህል ምርት ለመሰብሰብ ታስቧል፡፡

## ተናጋሪው ዶሴ

# ቅናትና መዘዙ

**አስመረት ብስራት**

ይወዳታል ከልቡ። በሁለቱ መካከል ያለው የእድሜ ልዩነት ግን ፍቅሩን በአግባቡ እንዳያጣጥም አድርጎታል። አይደለም ወጣ ገባ ብላ ቤት ውስጥም ብትሆን አምሮባት ሲመለከት በቅናት እርር ድብን ይላል። ቅናት በተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ቢሆንም ለእርሱ ግን የሚወደውን ሰው ከማጣት ጋር የተያያዘ የስጋት እና ሽብር ስሜት ፈጥሮበታል፡፡

ይሄ የሽብር ስሜት በተለያዩ ምክንያቶች ቢፈጠርበትም የፍቅሩ መብዛት እያሰበ በቀላሉ ሊያልፈው ሲታገል ሰነባብቷል። አቶ ፍቃዱ ሽፈራው በፍቅሯ የወደቀላትን ሐረገወይንን አሰፋን እጇ ካስገባም በኋላ ምንም ልቡ ሊያረፍለት አልቻለም።

ወዳና ፈቅዳ የትዳር አጋሩም ብትሆን ቅሉ የእርሱ ልብ ግን ትታኝ ትሄዳለች በሚል ስጋት ተወጥሮ ትኩሱን ፍቅሩን እንዳያጣጥም እግር ከወርች አስሮታል። ይህ የቅናት ስሜት በሚፈጠርበት ወቅት ስሜቱን ለመግለፅ ቃላትን ሳይሆን ጉልበትን መጠቀም እንዲጀምር አድርጎታል። በግልፅ ስለጉዳዩ ከመወያየት ይልቅ ባለቤቱ ላይ ለዱላ ሲጋበዝ መታየት የተለመደ ሆነ፡፡

ቤት ውስጥ ተቀምጣ የምትውለው የትዳር አጋሩ ‹‹ምን እያደረገች ይሆን?›› በማለት ቀኑን ሙሉ እየተብሰለሰለ መዋል አልፎ ተርፎም ቀኑን ብቻ ሳይሆን ሌሊትም ኮርኒስ እየቆጠረ ነገር መብላት ሥራው ሆነ።

የሱ የቅናት ስሜት ከፍቅር የመነጨ ሳይሆን እምነት ከማጣት የመጣ እንደሆነ መረዳት ተስኖታል፤ እሷም ለትዳር አጋሯ ውሎዋን ለመናገር ወይም አንተ በሌለህበት ሰዓት የተፈጠሩ ነገሮችን እነዚህ ናቸው ማለት ከብዷታል።

በዚህ በመዘዘኛ ቅናት ምክንያት ባለቤቷ ለምግብ ያለው ፍላጎት ቀንሷል። እሷም በእርሱ ምክንያት ጭንቀት ውስጥ ከገባች ሰነባብታለች። ባለቤቷ ወደቤት ሲገባ እንደ መደሰት ፈንታ በጭንቀት የልብ ምቷ የሚጨምርበት ሁኔታ ተፈጠረ።

እሱን ስታይ በጭንቀት ከልክ በላይ ያልባት ገባ። ጭንቀቱ ነው መስል ቶሎ ቶሎ መድከምም መገለጫዋ ሆነ። በመጨረሻም ቅናት ከትዳር አጋሯ ጋር ያላት ግንኙነት ላይ ክፍተት እየፈጠረ መጣ፡፡

አባወራው ይሄ ቅናት የዕለት ተዕለት ኑሮቸው ጋር እየተጋጨ መሆኑን ቢረዳም የምወደውን ሰው እያሳዘነ እና እየጎዳ እንደሆነ ቢገነዘብም ቅናቱ እርሱ ራሱን ከሚቆጣጠረው በላይ እሱ ተቆጣጥሮት ነበር።

የባልየው ቅናት ባለቤቴ በሥራ ብዙ ሰዓቷን የምታሳልፍ ወይንም ብዙ ጊዜዋን በማንበብ የምታሳልፈው ሆን ብላ ከእኔ ለመራቅ ብላ ነው በማለት በቅናት እርር ድብን ሲል ይታያል፡፡ ቅናቱም የፍቅር ግንኙነቱን እየሻከረ መምጣት ጀመረ።

ሰውየው ‹‹እርር ድብን ማለት አንገሸግሾኛል፤ ጨጓራዬን ልተፋው ነው፤ አንድ በሉኝ›› በማለት ወዳጅ ዘመዱን



ቢያማክርም ምንም ዓይነት መፍትሔ ሊያገኝ አልቻለም። ውስጥ ውስጡን እየበላ ከቁጥጥር ውጭ ያደረገው ቅናትን ፈፅሞ ሊቆጣጠረው አለመቻሉ ከብዶታል። ይህ ቅናቱ ግን እጁን በእጁ ያስቀጥፈኛል ብሎ አስቦ አያውቅም ነበር።

### የፍቅር መጀመሪያ ሰሞን

ወጣቷ ሐረገወይን አሰፋ በአንዲት አነስተኛ ካፍቴሪያ ውስጥ በመስተንግዶ ሥራ ትሰራ ነበር። የአርባ ስድስት ዓመቱ ጎልማሳ ፍቃዱ ሽፈራው ደግሞ ከሥራ መልስ በካፍቴሪያዋ ተቀምጦ ሻይ ቡና ማለት ልማዱ ነበር። ሐረግ ቆንጆ የምትባል ሴት አይደለችም። ይህ ነው የሚባል መልክ ባይኖራትም ዓይነ ግቡ ነበረች። ከልጅነቷ ጋር ተደምሮ ከፊቷ የማይጠፋው ፈገግታ ብዙ ተመልካች እንዲኖራት አድርጓታል።

ብቸኛ ሆና ኑሮዋን ለመርታት የምትታትረው ወጣት በእርጋታ ተቀምጦ ለረጅም ሰዓታት የሚመለከታት ትልቅ ሰውዬ ነገር ልቧን ከንክኖታል። በስህተት ሲቀር ዓይናደጅ ደጁን ማማተር ከጀመረ ሰነባብቷል። ሲመጣም እሷ እንድትታዘዘው የመፈለጉ ነገር ማርኳታል።

እርጋታው ከልክ በላይ የሰውን ስሜት ይገዛል። ከእለታት አንድ ቀን ብዙም ተስተናጋጅ በማይኖርበት ሰዓት ወደ ካፍቴሪያው ጎራ ያለው ጎልማሳ ይችን የደም ገንቦ በነፃነት ለማናገር እድሉን አግኝቷል።

አጠገቡ እንድትቀመጥ ጋብዞ ጨዋታ የጀመረው ሰው ጨዋታ አዋቂ ጥርስ አያሰከድኔ የሚባል ዓይነት ሰው መሆኑ ደግሞ የሐረገን ልብ ይበልጥ አሸፈተው። ስለኑሮዋ በደንብ ከተረዳ በኋላ እሱ ጋር ሆና መማር እንደምትችል አባብሎ በእጅ በእግሯ ገብቶ ቤት ይወስዳታል።

ቤቱ ባስገባት በወራት ጊዜ ውስጥ ትምህርት ቤት ቢያስገባትም መውጣት መግባቷ ግን ጭንቅ ሆኖበታል። እሱ ከልቡ ስለሚወዳት ሁሉም ሰው በእርሱ ዓይን የሚያይበት እየመሰለው ሲጨነቅ ሲጠበበ ነበር የሚውለው።

ለባብሳ ትምህርት ቤት ስትሄድማ ከቁጥጥር ውጭ ይሆንና ስትገባ ስትወጣ በነገር መተክተኩን አላቆም ብሷል። እንደዛ በፍቅሩ ተረታ ቤቱ የገባቸው ወጣት ከዛሬ ነገ ያጠፋኝ ይሆን ወደሚለው ስጋት ውስጥ ለመግባት ሁለት አመታት አልተቆጠሩም ነበር። ትምህርቷን አቋርጣ ቤት ብትቀመጥም ልቡ ሊያረፍለት ያልቻለው አባ ወራ በድብቅ ይሰልላት ጀመር።

### የስለላው መረብ ያጠመደው አሳ

በፊት የምትሰራበት ካፍቴሪያ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ተሰብስበው የሚጥሏት አነስተኛ እቁብ ለሐረገወይን ይደርሳታል። ለሁለት ዓመታት ያልተቋረጠው እቁብ ለሐረግ ስለደረሰ አንድ የሥራ ባልደረባዋ ገንዘቡን ሊሰጣት መኖሪያ ቤቷን አጠያይቆ ይመጣል።

በጥርጣሬ የእለት ከእለት ሥራው ሚስቱን መከታተል የሆነበት አባ ወራ የደጃፋቸውን መዝጊያ የሚቆረቁረው ወጣት ማን እንደሆነ ለመመልከት ጠጋ ከማለቱ ባለቤቱ በር ከፍታ እንግዳውን ሰው በፈገግታ ስትቀበለው ይመለከታል።

ልጁም በር ላይ ቆሞ ከባለቤቱ ጋር ሲያወራ ቆይቶ በፖስታ የያዘውን ነገር ሰጥቷት ሲመለስ ይመለከታል። የቅናት ዛር የጋለበው አባ ወራ በሩጫ ወደ ቤቱ ይገባና መጥቶ የነበረው ሰው ማን እንደሆነ ጠይቆ እንድታስረዳው እንኳን ፋታ ሳይሰጣት ይቀጠቅጣት ጀመር።

በእጁ ደብድቧት አልረካ ያለው አባ ወራ ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል በመግባት የአጥንት መከትከቻ መጥረቢያ በማምጣት የሚወዳት ሚስቱ ላይ የጭካኔ እጁን ያሳረፍባት ጀመረ።

### የማስዳው የጭካኔ ምሳር

ወይዘሮ ሐረገወይን የምወደውን ሰው አገባሁ ብላ በሰላም ከምትኖርበት ቤቷ ውስጥ ፍቅር ይሁን እብደት በቅጡ ያለየ መንፈስ የነበረው ባለቤቷ በአሰቃቂ ሁኔታ በመጥረቢያ እየደጋገመ ይመታታል። ወደ ሥራ መሄዴ ነው ብሎ በጠዋት የወጣው ባለቤቷ በግምት ሶስት ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ ተመልሶ እንደ እብድ ሲጮህ የምትይዘው የምትጨብጠው ነበር የጠፋት።

ለማምለጥም ይሆን ስለጉዳዩ አስረድታ ነገሩን ለማለሳለስ እድል ሳይኖራት በያዘው የሥጋ መከትከቻ አንገቷን፣ ትከሻዋን፣ ዓይኗ ስር፣ ክንዶቿን፣ ጭንቅላቷን በመምታት ሕይወቷ እንዲያልፍ አድርጓል።

ነገን ተስፋ አድርጋ ረጅም የትዳር ሕይወት ይኖረኛል ብላ ያለመችው ህልም ሳይፈታ በአጭሩ ተቀጨ። ልጅ ወልዳ ከብዳ ለወግ ማዕረግ እበቃበታለሁ ያለችው ቤት ውስጥ ሕይወቷን ከፈለች።

የሚስትየው የጣር ድምፅና የባልየው የጭካኔ በትር ጀሯቸውን የሳበው በበር የሚያልፉ መንገደኞች ጉዳዩ ፖሊስ ጆሮ እንዲደርስ ያደርጋሉ። ፖሊስም በፍጥነት በአካባቢው ሲደርስ ገዳይ የገደለበትን መሳሪያ እንደያዘ እጅ ከፍንጅ ይይዙታል።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ በ29/02/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት ሶስት ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ስሙ አርሴማ አደባባይ ከሚባለው አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤት ውስጥ ጩኸት እንደሚሰማ በደረሰው ጥቆማ መሠረት ወደ ቦታው ይሄዳል።

ቦታው ደርሶ የአጥር በር ሲያንኳኳ የሚከፈትለት በማጣቱ በአጥር ዘሎ በመግባት የሆነውን አሰቃቂ ድርጊት ይመለከታል። ይህን ከባድ ሰው የመግደል ወንጀል የፈፀመውን ግለሰብ ሰው ለመግደል ከተጠቀመበት መሳሪያ ጋር እጅ ከፍንጅ በመያዝ ወደ ማረፊያ ቤት ይወስደዋል።

የወንጀል አድራጊውን የእምነት ክህደት ቃል፤ የዓይን ምስክርነትንና ፤ የሕክምና ምርመራውን በማስረጃነት በማቅረብ አቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰርት ይልካል።

### የፌደራል አቃቤ ሕግ

ከሳሽ የፌደራል አቃቤ ሕግ ሲሆን ተከሳሽ ፍቃዱ ሽፈራው አያኖ እድሜ 48 የትምህርት ደረጃ አስራ ሁለተኛ ክፍል የሆነውን ግለሰብ ወንጀሉ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1) (ሀ) ስር የተመለከተውን መተላለፍ ክስ መስርቶበታል።

አድራሻ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር አዲስ ነዋሪ የሆነው ይህ ግለሰብ የትዳር አጋሩ የሆነችው ሟች ሐረገወይን አሰፋ የተባለችውን ከሌላ ወንድ ጋር ማግጠሽብኛል በሚል ምክንያት በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወቷ እንዲያልፍ አድርጓል።

### የወንጀል ዝርዝር

ተከሳሽ ሰው ለመግደል የተጠቀመበት መሳሪያና ዘዴ እና አገዳደሉ ሁኔታ ሲታይ በተለየ ጭካኔና አደገኝነትን በሚያሳይ ሁኔታ 29/02/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት ሶስት ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ስሙ አርሴማ አደባባይ ከሚባለው አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የትዳር አጋሩ የሆነችው ሟች ሐረገወይን አሰፋ የተባለችውን ከሌላ ወንድ ጋር ማግጠሽብኛል በሚል ምክንያት ያለመግባበት መፈጠሩንና ያለመግባበቱ ሲካረር ምግብ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን የአጥንት መከትከቻ መጥረቢያ በማምጣት አንገቷን፤ ትከሻዋን፤ ዓይኗ ስር፤ ክንዶቿን፤ ጭንቅላቷን በመምታት ሕይወቷ እንዲያልፍ አድርጓል።

### ውሳኔ

ከሳሽ የፌዴራል አቃቤ ሕግ ተከሳሽ ፈቃዱ ሽፈራው አያኖ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የነበረው ክርክር በ28/9/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሽ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ እንዲሁም ከሕዝባዊ መብቶቹ ለዘወትር እንዲሻር እንዲሁም በኤግዚቢትነት የተያዘው መጥረቢያ በሚመለከተው አካል እንዲወገድ ውሳኔ ተሰጥቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በመንገዴ ላይ...

**ቃልኪዳን አሳዬ**

እንደለመደብኝ ዘወትር ጠዋት ከእንቅልፌ እየተነሳሁ ወደ መስሪያ ቤቴ እሄዳሁ፡፡ መስሪያ ቤቴ ከመኖሪያዬ ብዙ አይርቅም፡፡ ለዚህም ነው ብዙውን ጊዜ በእግሬ የምመላለሰው፡፡ ይህን የወሰንኩት ከታክሲ ግፍያው ለመሸሽ ስል ነው።

ልማደኛው እግሬ ዛሬም መንገዱን ጀምሯል። ማየትን የማይታክቱ አይኖቼ ዙሪያ ገባውን መቃኘቱን ይዘውታል፡፡ የንጋቱ ማብሰሪያ የአዕዋፋት ዝማሬ ፤ የታክስ ረዳቶች ጩኸት፣ የኮቴ ድምፆች... ሁሌም ለጆሮዬ የእለት ተእለት ዜማ ናቸው ፡፡

እስከ አሁን ከርታታው ዓይኔ ብዙ አስደሳች፣ አሳዛኝ፣ ተስፋ አስቆራጭ ሁነቶችን ያየባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አልፈዋል፡፡ ጆሮዬም ቢሆን ለመስማት የማይጋብዙ ወሬዎችን ሳይወድ በግዱ እየተቀበለ እንዳልሰማ ማለፍ ከጀመረ ሰነባብቷል። በሁሉም ምልከታዬ ግን አይቼ እንዳላየሁ ሰምቼ እንዳልሰማሁ ማለፍ የሌለብኝ አያሌ ጉዳዮች አጋጥመውኛል ፡፡

ከእናታቸው ማህጸን እንደወጡ ጎዳና የተቀበለቻቸው፣ ብርድ፣ ቁርን፣ ረሀብና ስቃይን የጋበዘቻቸው ጨቅላ ህፃናት ዘወትር ከእይታዬ አይርቁም፡፡ ከእነዚህ ነፍሶች መሀል የትምህርት ደጃፍን በመርገጫቸው እጃቸውን ለልመና፣ ራሳቸውን ለተለያዩ ሱሶች ያስገዙ ወጣቶችን ስመለከት ሁሌም አዕምሮዬ በማይመለስ ጥያቄ ይፈተናል ፡፡

በሌላ በኩል ከህፃን እስከ አዋቂ መጠለያ በማጣት በየግንቡ ስርና በየአብያተ ክርስቲያናቱ ጥግ ተከልለው ለእለት ጉርሳቸው አላፊ አግዳሚውን የሚማፀኑት የአብዛኞቻችን ዓይኖች ያስተውላሉ ፡፡

ሁሌም ግርም የሚለኝ ጠዋት ወደ ስራ ስወጣ ዕቃቸውን ቋጥረው፣ ውሃቸውን ይዘው በዘወትር ቦታቸው ላይ የሚሰየሙ ሰዎች ነገር ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ምጽዋት ጠያቂዎች ናቸው፡፡ ባየኋቸው ቁጥር ምናልባት ለምዶባቸው ይሆን? እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ።

ይህ ሁሉ ወገን በየጎዳናው ህይወቱን እንዲመራ የተገደደበት ምክንያት ምን ይሆን? ለዚህስ ችግር ማን ይሆን ተጠያቂው? ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ አለፍ ብዬም የሚሰጣቸው ምጽዋት በቂያቸው ስለ መሆን አለመሆኑ እየመዘንኩ እጨነቃለሁ፡፡

ሁሉንም መለወጥና ወደተሻለ ህይወት መምራት ባይቻል እንኳን ቁጥራቸውን መቀነስ ዋነኛው መፍትሔ እንደሆነ ይሰማኛል ። ነገር ግን አሁንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደጎዳና የሚወጡ ዜጎች ቁጥር እያሻቀበ መምጣቱን ልብ ይሏል።

መልስ በሌለው ሀሳብ ተሳፍሬ እያወጣሁ እያወረድኩ ሳለ የእድል ጮራ ወቶላቸው በወጉ እንዲኖሩ የተፈጠሩ ህፃናት የምሳ እቃቸውን አንጠልጥለው፣ በትካሻቸው የተወጠረ ቦርሳ ተሸክመው ወደ ትምህርታቸው ሲሄዱ አስተውላለሁ፡፡ እርስ በእርሳቸው ከእኩዮቻቸው ጋር የሚያወሩት ወሬ ደግሞ ሌላ ግርምት ያጭርብኛል፡፡

መደማመጥ በሌለው ድምጻታቸው ስለምዕራባዊያን የፊልም ተዋናዮች፣ ስለሚወዷቸው አርቲስቶች ፣ የእግር ኳስ ክለብ ወዘተ... በነጻነት ያወራሉ፡፡ ይባስ ብሎ ስለ ፍቅር አጋር፣ ፆታዊ ግንኙነት እና በእነሱ ዕድሜ ሊወሩ ቀርቶ ለአፍታም መታሰብ ስለማይገባቸው ጉዳዮች እያነሱ በጎላ ድምጽ ይጫወታሉ ።

አሁንም የመንገድ ላይ አስተውሎቴ ቀጥሏል። ርምታዬ ከእኔው ጋር ነው፡፡የአንዳንድ ወጣቶችን የአለባበስ ስርዓት እየቃኘሁ ነው፡፡ አንዳንዶች የሀገራቸውን ባህል እና ወግ ፈጽሞ የዘነጉት ይመስላል፡፡ ሰውነታቸውን ለተለየ ትርዒት ያቀረቡ ያህል አላፍ አግዳሚውን አጀብ የሚያሰኙ ናቸው፡፡ በኔ ግምት ሁሉም የራሱ ጊዜ እና ቦታ አለው፡፡

ይህን እውነት አምነውና ተረድተው በተግባር የሚያሳዩ ሲኖሩ ማንነታቸው መልካም ትርጉም ይኖረዋል ፡፡ አንዳንዶች ግን «ካላያችሁን» በሚመስል ድርጊት በየመንገዱ እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈው ያለአንዳች እፍረት ከንፈር የሚቃመሱ ናቸው፡፡

> « አንዳንዶች የሀገራቸውን ባህል እና ወግ ፈጽሞ የዘነጉት ይመስላል፡፡ ሰውነታቸውን ለተለየ ትርዒት ያቀረቡ ያህል አላፊ አግዳሚውን አጀብ የሚያሰኙ ናቸው፡፡ በኔ ግምት ሁሉም የራሱ ጊዜ እና ቦታ አለው፡፡»

በየጊዜው እንዲህ መሰሎቹ ቁጥራቸው መበራከቱን ስመለከት ውስጤ ከማዘን አልፎ ሲሸማቀቅ ይሰማኛል፡፡ መለስ ብዬ የወላጆችን ኃላፊነት አስባለሁ፡እርግጥ ነው አንዳንዴ «ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ » ሊባል ይችላል፡፡እንዲያም ቢሆን ዋንኛ ትኩረት ከወላጆች መራቅ አይኖርበትም ፡፡ ልጆች ከተወለዱበት ቀን አንስቶ እራሳቸውን እስከሚችሉበት እድሜ ድረስ የወላጆችን ድጋፍና ክትትል ይሻሉ፡፡


ልጆች ነገሮችን ማድመጥ፣ መገንዘብና መናገር ሲጀምሩ የተለያዩ ሃሳቦችን ሊያስተናግዱና የአመለካከት መዛባት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ኋደኛ ማበጀትና ከሌሎች ልጆች ጋር መገናኘት ሲጀምሩ ደግሞ ክፉም ሆነ ደግ ባህሪያትን ሊወርሱ እንደሚችሉ ይገመታል ፡፡

ወደ ጉርምስና እድሜ ሲገቡ የሚስተዋልባቸው ስሜታዊ ድርጊት ለአጉል ልማድና ላልተገቡ ተግባራት የሚያጋልጣቸው ነው፡፡ ይህን በማሰብም በአግባቡ የቅርብ ክትትል ማድረግ የወላጆች ቀዳሚ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ስንቶች ይህን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ይሆን ? የምላሹን ነገር ቤት ይቁጠረው፡፡

በኢትዮጵያ የሚኖር አብዛኛው ዜጋ ሃይማኖት፣ ባህል፣ ወግና እሴት ያለው መሆኑ ይመሰከርለታል። ይህን እውነት እኛም በየአጋጣሚው ስንተርከው እንደመጣለን። አንዳንዴ በመንገዴ ላይ የሚገጥሙኝን ወጣቶች ሳይ ግራ የሚገባኝ ነገር አለ፡፡ ባህል፣ ወግና እሴት ማለት ብጣሽ ልብስ ከሰውነት ጣል አድርጎ መዞር ፤ በየመንገዱ መላላስ ነው እንዴ? በዚህ አይነቱ ገጽታ መታየትስ የኢትዮጵያውያን ባህልና ወግ ያስብል ይሆን ?

ታዲያ ለእነኝህ ግልጽ ጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂው ማን ነው? ወላጆች፣ ትምህርት ቤቶች? ሀይማኖት ተቋማት? መንግስት? ማን ነው? ዋናው ጉዳይ ችግሮቹን ለመፍታት «እከሌ ነው» ጥፋተኛ ብሎ ጣት መቀሳሰር ብቻ አይደለም፡፡ ሁሉም በያለበት ኃላፊነቱን ቢወጣ መልካም ነው እላለሁ፡፡ «አበቃሁ»

# ዓለም አቀፍ



## የኒው ዮርክ ፖሊስ አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተመሳስለው የተሠሩ ምርቶችን ያዘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኒው ዮርክ ባለሥልጣናት አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተመሳስለው የተሠሩ የዲዛይነር ምርቶችን መያዛቸውን አስታወቁ።

ይህን ያህል መጠን ያለው ተመሳስሎ የተሠራ ቁሳቁስ በቁጥጥር ሥር ሲውል በአሜሪካ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ተብሏል።

ባለሥልጣናቱ እንደገለጹት 219 ሺህ የእጅ ቦርሳዎች፣ ጫማዎች እና ሌሎችም ውድ ዕቃዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

ሁለት ግለሰቦች ተመሳስለው የተሠሩ ቁሳቁሶች ማንሃታን ከሚገኝ መጋዘን ውስጥ እያከማቹ ሲሸጡ ነበር ተብለው ክስ ተመስርቶባቸዋል። ሁለቱ ሰዎች ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ እስከ 10 ዓመት እስር ይጠብቃቸዋል።

የኒው ዮርክ ፖሊስ ኮሚሽነር ኤድዋርድ ኤ ካባን በለቀቁት መግለጫ ተመሳስለው የሚሠሩ ምርቶች “ሕጋዊ ሱቆችን፣ መንግሥትን እና ሸማቹን ማሕበረሰብ ይጎዳሉ” ብለዋል።

የዩናይትድ ስቴትስ አቃቤ ሕግ የደቡብ ኒው ዮርክ ቀጣና ቢሮ አዳማ ሶው እና አብዱላይ ጃሎህ የተባሉ ሰዎች ረቡእ ዕለት በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ይፋ አድርጓል።

የዩኤስ አቃቤ ሕግ እንደገለፀው ሁለት ግለሰቦች ካለፈው ዓመት ጥር እስከ ኅዳር ባለው ጊዜ “ትልቅ መጠን ያለው ተመሳስሎ የተሠራ ምርት ሲያጋግዙ ነበር።”

ተመሳስለው የተሠሩት ምርቶች ገበያ ላይ የሚሸጡበት ዋጋ አምራቾች በችርቻሮ እንዲሸጥ ከሚያወጡት ዋጋ እጅግ ያነሰ ነው ብለዋል።

ፖሊስ፤ አዳማ ሶው የተባለው ግለሰብ ከሚቆጣጠረው ግቢ ብቻ 502 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ የሚያወጡ 83 ሺህ ሐሰተኛ ምርቶች በቁጥጥር ሥር አውሏል።

ከአብዱላይ ጃሎህ ግቢ ደግሞ 237 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ 50 ሺህ ገደማ ተመሳሳይ ምርቶች ተይዘዋል።

ባለፈው መስከረም የኒው ዮርክ ፖሊስ 35 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ ያላቸው ተመሳስለው የተሠሩ ምርቶችን ይዞ 18 ሰዎች ማሰሩ ይታወሳል።

ታችኛው ማንሃታን በተለይ ደግሞ ካናል መንገድ ተብሎ የሚጠራው ሥፍራ ተመሳስለው የተሠሩ ምርቶች በሰፊው የሚቸበቸቡበት ሥፍራ ነው።

## ሱዳን ተመድ የፖለቲካ ተልዕኮውን በአስቸኳይ እንዲያቋርጥ ጠየቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ሱዳን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) የፖለቲካ ተልእኮውን በአስቸኳይ እንዲያቋርጥ በይፋ ጠየቀች።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሱዳን ሚሽን የተቀናጀ ድጋፍ (UNITAMS) እ.አ.አ. በ2020 በሱዳን ስራውን የጀመረ ሲሆን 400 ሰራተኞችን ይዞ እየሰራ ይገኛል።

የሱዳን መንግስት በጻፈው ደብዳቤ ተመድ በሀገሪቱ ያለውን የፖለቲካ ተልእኮ በአስቸኳይ እንዲያቋርጥ መጠየቁን ሮይተርስ ዘግቧል።

"የሱዳን መንግስት ተመድ በአስቸኳይ የተመድ ኢንተግሬትድ ትራንዚሽን አሲስታንስ ሚሽንን (ዩኤንአይቲኤሚ) እንዲያቋርጥ ጠይቋል። በዚህ ወቅት የሱዳን መንግስት ከጸጥታው ምክር ቤት ጋር ገንቢ በሆነ መልኩ ለመወያየት እንደሚችል እናረጋግጣለን" ሲሉ የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አሊ ሳድቅ ለጸጥታው ምክር ቤት ተናግረዋል።

ለተመድ ዋና ጸሐፊ የተላከው የሱዳን ደብዳቤ እንዳመለከተው ሚሽኑ የተቋቋመው በ2018 የተከሰተውን አብዮት ተከትሎ ያለውን ሽግግር ለማገዝ ቢሆንም ውጤቱ "ቅር የሚያሰኝ" መሆኑን ጠቅሷል።


የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ቃል አቀባይ ደብዳቤው እንደደረሳቸው እና ለጸጥታው ምክር ቤት መተላለፉንም አረጋግጠዋል።

በሱዳን በጀነራል አል ቡርሃንና በጀነራል ሀምዳን ዳጋሎ መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት ወደ ከፍተኛ ቀውስ አምርቷል። ጦርነቱን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችም ምንም ውጤት አላመጡም።

በሱዳን የሚገኙ የተለያዩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተቋማት ቢሯቸውን ዘግተው ከሀገሪቷ በጊዜያዊነት የወጡ ቢሆንም የተለያዩ ተቋማት አሁን ላይ በሀገሪቷ ይገኛሉ።

# አእምሮን እየጎዱ ያሉ ቀላል ልማዶች

አስናቀ ፀጋዬ



አእምሯችን የሰውነታችን ዋነኛ አንቀሳቃሽ ክፍል ነው፡፡ ያለ አእምሯችን ምንም ማድረግ አንችልም። አእምሯችን ሲጎዳ ሃሳብ ማመንጨት የለም፡፡ እንደልባችን ሰውነታችንን ማዘዝ ይሳነናል። ጤናማ ሕይወት አይኖረንም፡፡ ለዛም ነው የአእምሮ ጤና የሁሉም የሰውነት ክፍል ጤና ነው የሚባለው። ከዚህ አንፃር የአእምሯችንን ጤና መጠበቅ ወሳኝ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን አእምሯችን በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች ጤናው የሚቃወስበት ዕድል ቢኖርም አንዳንዴ ግን ቀላል በሆኑና በራሳችን ቸልተኝነት ምክንያት የሚጎዳበት አጋጣሚ አለ። ይህ ሲባል አእምሯችንን መጠቀም በሚገባን ልክ ካልሰራንበት ምንም ነው፡፡

እነዚህ ቀላል የሆኑ ነገሮች አእምሯችን ከአቅሙ በታች እንዲሰራ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እንድንሰንፍና የተሻለ ሰው እንዳንሆን ያደርጋሉ። ለምሳሌ አንድ ገበሬ ማሳው ላይ ጤፍ ከዘራ ጤፍ ያጭዳል። ስንዴም ከዘራ ስንዴ ያጭዳል። ምንም ባይዘራ ደግሞ ያው አረም ያጭዳል። እኛስ አእምሯችን ላይ ምን እየዘራን ነው? ጥሩ ነገር ከሆነ እንቀጥልበት፡፡ መጥፎ ከሆነ ደግሞ እናስወግደው። ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አእምሯችን እየጎዱ ያሉ ቀላል፣ ነገር ግን መጥፎ የሆኑ ልማዶችን ማስወገድ የግድ ይለናል፡፡

### 1ኛ. ረጅም ሰዓት ስክሪን ላይ መቆየት

አብዛኛዎቻችን በስልክ፣ ኮምፒዩተርና ላፕቶፕ ስክሪኖች ላይ ረጅም ሰዓት እናጠፋለን። አንዳንዴማ ረጅም ሰዓት እንዳጠፋን ሁሉ አይታወቀንም። ዓይኖቻችን በስልክና ላፕቶፕ ስክሪኖች ላይ ረጅም ሰዓት በቆየ ቁጥር white and gray matter የሚባለው የአእምሮ ክፍል ይጎዳል። እንደውም frontal lob የሚባለውና በጣም ከባድና ጠንካራ ሃሳቦችን የምናመነጭበት የአእምሮ ክፍል ይደከማል። በዚህ ምክንያት ጠንካራ ሃሳቦችን ማሰብ፣ በደንብ ማሰላሰል ይሳነናል፡፡ ደካማ እንሆናለን፡፡ ማንበብ እንድንጠላ፣ በጣም ጥሩ ጥሩ የሆኑና የአእምሮ ጡንቻን የሚያጠነክሩ ሥራዎችን እንዳንሰራና እንዳንለወጥ ያደርገናል። ስለዚህ በላፕ ቶፕ፣ የእጅ ስልክና ኮምፒዩተር ላይ በማፍጠጥ የምናጠፋውን ጊዜ መቀነስ አለብን፡፡

### 2ኛ. ዜናና ፊልም ማብዛት

ለምሳሌ እቤታችሁ ውስጥ ምግብ እያበሰላችሁ እያለ አንድ ሰው መጥቶ የምታበስሉት ምግብ ላይ የሆነ ቆሻሻ ቢጨምር ትጣሉታላችሁ፡፡ ዝም ብላችሁ አታልፉትም፡፡ ወይ ትሰድቡታላችሁ፤ ወይ ትደበድቡታላችሁ፤ አልያም ሰው ጠርታችሁም ቢሆን ታስደበድቡታላችሁ፡፡ ብቻ ዝም አትሉትም፡፡ ለምን? ወደ ሰውነታችሁ ውስጥ የሚገባ ምግብ ላይ ነው ቆሻሻ የጨመረው፡፡ ምግቡ ጤናማና ንፁህ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ወደ ሰውነታችን ለሚገባው ነገር እንጨነቃለን ማለት ነው፡፡ ወደ አእምሯችን ለሚገባው ነገርስ ምን ያህል እንጨነቃለን? ዜና ወደ አእምሯችን ሲመጣ ምን ይዞ ነው የሚመጣው? ጥሩ ዜና ነው ወይ የምንሰማው፤ ጥሩ ዘገባ ነው ወይ የምናደምጠው?

በርግጠኝነት አምስት ዜና ብትሰሙ ከአምስቱ በጣም ጥሩ ዜና አንድ ወይ ሁለት ነው፡፡ እንትና አሸነፈ፤ እንትን ደግሞ ተመርቆ ተከፈተ የሚል ሊሆን ይችላል። ከዚህ ውጭ ግን አብዛኛው ዜና ወይ ሽብር ነው ወይ የሆነ ማስጠንቀቂያ አልያም ደግሞ አደጋ ነው። እንዲህ ሲባል ዜና አትስሙ ለማለት አይደለም። ነገር ግን በጣም ደጋግሞ አሰቃቂና አስከፊ ዜናዎችን ደጋግሞ መስማት አእምሮን በእጅጉ ይጎዳል። ቀላል ልማድ ይመስላል ግን ዜናው በሀገራችን ተስፋ እንድንቆርጥ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ በገጠር ያለ ሰው እንዲህ ያለ ዜና ሲሰማ ‹‹አዬ! በቃ ይህች ሀገር እንዲህ ሆና ቀረች፤ መጥፊዋ እየቀረበ ነው›› ይላል፡፡ ለመሥራት ያሰበውን ቢዝነስም ይተዋል፡፡ በውጭ ሀገር ያለውም ‹‹እንደው ሀገሬ ላይ ሰላም የለ፤ ምን ላደርግ ነው ሀገሬ የምገባው›› ይላል ያችን ዜና ሰምቶ፡፡ ኢንቨስት ሊያደርግ ያሰበውን ነገርም ይተዋል፡፡ አያቹህ! መጥፎ ዜናዎች ህልማችሁን ሁሉ ይነጥቃችኋል፡፡

‹‹የአእምሯችንን ጤና መጠበቅ ወሳኝ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን አእምሯችን በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች ጤናው የሚቃወስበት ዕድል ቢኖርም አንዳንዴ ግን ቀላል በሆኑና በራሳችን ቸልተኝነት ምክንያት የሚጎዳበት አጋጣሚ አለ። ይህ ሲባል አእምሯችንን መጠቀም በሚገባን ልክ ካልሠራንበት ምንም ነው፡፡››

ሌላው ቀላል ነገር ግን ደግሞ አእምሮን የሚጎዳው ነገር ፊልም ማየት ነው፡፡ በነገራችን ላይ ፊልም ማየት ካበዛን በጣም መጥፎ ነው፡፡ ለምን መሰላችሁ? አብዛኛዎቹ ፊልም ላይ የሚሰሩ ሰዎች ከእኛ በብዙ የተሻሉ ናቸው፤ ለፊልሙ ሲባል፡፡ ለዛም ነው እየደጋገምን የምናያቸው፡፡ እናም እነሱን ስናይ የበታችነት ስሜት ሊሰማን ይችላል፡፡ እንደውም በአሜሪካን ሀገር በአፍላ የወጣትነት እድሜ ላይ በሚገኙ ወጣቶች ላይ በተደረገ ጥናት 85 ከመቶ ያህሉ አሁን ያላቸውን ሰውነታቸውን እንደማይወዱት ተረጋግጧል፡፡ ሰውነታቸውን መቀየር ይፈልጋሉ። ወይ ቀዶ ሕክምና መሰራት፣ ቦርጭ ካላቸው ማስወገድ፣ ውፍረት ካላቸው መቀነስ፣ ብቻ የሆነ ነገር ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡

ለምንድን ነው? ሲባል ለካ በመዝናኛው ኢንዱስትሪው ላይ በተለይ በፊልም፣ ሙዚቃ ክሊፖችና ሌሎችም የመዝናኛ ዘርፎች ላይ የሚያዩዋቸው ሰዎች በሙሉ በጣም ቀጭን፣ የተስተካከለ የሰውነት ቅርጽ ያላቸው በመሆኑ እነሱን ለመምሰል የሚደረግ ጥረት መሆኑ ነው። ያ ማለት በፊልምና በሙዚቃ ክሊፕ ውስጥ በሚያዩዋቸው ተዋንያን ምክንያት የራሳቸውን ሰውነት እንዲጠሉ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ የበታችነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ እኛም አንዳንድ ጊዜ የምናያቸው ነገሮች በራሳችን ላይ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ አለ፡፡ አእምሯችን ላይ በጣም ከባድ ጉዳት አላቸው፡፡ ስለዚህ ዜና መስማት መቀነስ አለብን፡፡ ፊልም ማየት ማብዛት የለብንም፡፡ ማየት አለብን፤ ግን በልኩ መሆን አለበት፡፡

### 3ኛ. ብዙ ሥራ በአንዴ መሥራት

በአንድ ጊዜ ብዙ ሥራ ስለ ሠራን ጥሩ ነገር ያደረግን ሊመስለን ይችላል፡፡ ለምሳሌ እየበላን ይሆናል አልያም ደግሞ ሥራ እየሠራን ይሆናል፡፡ ዘፈን እንከፍታለን፡፡ ዜና ካለም እንከፍታለን፡፡ ምናልባት ተንቀሳቃሽ ስልካችን ላይ አጭር የጽሑፍ መልዕክት ከገባ እንመልሳለን፤ እንላላካለን፡፡ እያጠናንም ሊሆን ይችላል፡፡ ሥራም እየሠራን ሊሆን ይችላል፡፡ በአንድ ጊዜ የተለያዩ ሥራዎችን እንድንሰራ አድርጎናልና በዚህ ጊዜ አእምሯችን ጥምር ሥራዎችን ወደ መሥራት ውስጥ ይገባል፡፡

ስለዚህ የሆነ ጊዜ ደግሞ አንድ ሥራ ብቻ መሥራት ያለብን ሰዓት አለ፡፡ ለምሳሌ ጸሎት ማድረግ ሊኖርብን ይችላል፡፡ ያኔ አእምሯችን ስንት ቦታ ሊሆን ይችላል? ለምን? አልሰበሰብነውማ፤ ጎድተነዋል፡፡ ብዙ ሥራ እሠራነው፡፡ ስለዚህ አእምሯችን ትኩረት እንዳያጣ፤ ሃሳቡን መሰብሰብ እንዲችል በተቻለ አቅም አንድ ነገር ብቻ መሥራትን ማስለመድ አለብን፡፡ ብዙ ሥራ በአንዴ መሥራት አእምሯችንን ይጎዳዋል፡፡

### 4ኛ. ሁሌም ተመሳሳይ ሥራ መሥራት

አዲስ ነገር አለመሞከርና ሁሌም አንድ ዓይነት ሥራ መሥራት ቀላልና አእምሮን የሚጎዳ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡ ሕይወታችን የተለመደና ተመሳሳይ ነው። ጠዋት ወደ ሥራ ከሥራ ወደ ቤት እንመላለሳለን። ጋደም ብለን ቲቪ እናያለን። ቀኑ ያልፋል፤ ይመሻል፤ ይነጋልም። ቅዳሜና እሁድ ይመጣል፡፡ እቤት እናርፋለን፤ ወይስ ሥራ እንሠራለን። እሱም ያልፋል፡፡ አዲስ ነገር አንሞክርም፡፡ በዚህ ምክንያት አእምሯችን መሰልቸት ውስጥ ይገባል፡፡

ለምን? አእምሯችን አይፈተንማ፤ አዲስ ነገር ሙከራ አያደርግም፣ አዲስ ክሂሎት አይለምድም። ተመሳሳይ ኑሮ ነው የሚኖረው። ስለዚህ አእምሯችንን እንጎዳዋለን፡፡ ታዲያ ምን ይሻላል? የሚሻለው አዲስ ነገር ለማግኘት መሞከር ነው፡፡ አዲስ ነገር በማድረግ ሕይወትን መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ሥራም ከሆነ ትላንት ከሠራነው ዛሬ ጨመር አድርገን መሥራት ነው፡፡ የሚያስደስቱንን ነገር ማድረግ፣ ክሂሎቶችን መልመድ ይገባል። ለምሳሌ ዳንስ የሚወድ ሰው ዳንስ ቢማር፣ የሙዚቃ መሳሪያ መጨዋት የሚወድ ሰው እንዴት እንደሚጫወት ቢማር፣ አዲስ ቋንቋ መልመድ የሚፈልግ ሰው ቋንቋውን ቢማር ብቻ በፊት ከነበርንበት ሁኔታ ሊቀይሩ የሚችሉ ነገሮችን መልመድ ያስፈልጋል፡፡

### 5ኛ. ዝምታ ማብዛት

ማህበራዊ ሕይወታችን ላይ በጣም ሰነፍ ከሆንን ወይም ደግሞ ከሰዎች ጋር መግባባት የማንፈልግ ከሆነ እንደማሽን ነው የምንንቀሳቀሰው። ለምን? ከሰዎች ጋር አናወራም፡፡ ሃሳብ አንለዋወጥም። መረጃ አንወስድም። አይብዛ እንጂ ጓደኛ መያዝ፣ ከቤተሰብ ጋር ጊዜ ማሳለፍ በጣም ወሳኝ ነው። አእምሯችን ይታደሳል፡፡ አንድ ጥግ ብቻ አይቀመጥም፡፡

አእምሯችን እንደጡንቻ ነው፡፡ እንዳሰለጠነው ነው የሚሆነው፡፡ ካጠነከርነውና ብዙ ነገር ካሰራነው በምላሹ የመሥራት አቅሙን ያሳድጋል፡ ከሰዎች ጋር መግባባት በራሱ የሚሰጠን ጥቅም አለ፡፡ ያነቃቃናል። ጉልበት ይሰጠናል፡፡ ይሁንና ጓደኛ ስንይዝ መምረጥ አለብን፡፡ ‹‹አንድ ዓይነት ቀለም ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ›› እንደሚባለው ከእኛ ጋር ህልማችንን የሚጋሩ፣ በዓላማ የሚመሳሰሉ፣ ቁምነገረኛ የሆኑ፣ በጎ ነገርን የሚሰብኩ፣ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸው መሆን አለባቸው። ዝምታ የምናበዛ ከሆነ፣ ብቸኝነት የምናበዛ ከሆነ፣ አእምሯችንን እየጎዳነው ነው፡፡

### 6ኛ. በቂ እረፍት አለማድረግ

ይሄ እንደ ቀላል ልማድ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በተለይ አንዳንድ ሰዎች ሥራቸውን በትጋት ይሰሩና ማታ አምሽተው ፊልም ያያሉ፡፡ በቂ እረፍትና እንቅልፍ ሳያገኙ እንደገና በጠዋት ተነስተው ወደ ሥራ ይሄዳሉ። ወይ ደግሞ በቂ እረፍት ሳያደርጉ አሟቸውም ቢሆን በግድ ሥራቸውን የሚሰሩ ሰዎች አሉ፡፡ እንደውም ሳይንሱ ሰዎች እንቅልፋቸው በተመሳሳይ ሰዓት መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል። ይህም በተመሳሳይ ሰዓት መተኛትና በተመሳሳይ ሰዓት መነሳት እንደማለት ነው። ሁሌም አራት ሰዓት የምትተኙ ከሆነ ሰዓቱን ማዛነፍ የለባችሁም። ከዛ አስራ ሁለት ሰዓት የምትነሱ ከሆነ ሰዓቱን ማዛነፍ አያስፈልግም፡፡

የእረፍት ቀን ቅዳሜና እሑድም ቢሆን፣ የበዓል ቀናትም ቢሆን የእንቅልፍና ከእንቅልፍ የመነሻ ሰዓት ማዛነፍ አይገባም፡፡ ለምን? አእምሯችን የማረፉ ፊድን በተለይ ደግሞ እንቅልፍ የመተኛት ሂደት መልመድ አለበት፡፡ ምክንያቱም ይሄ ከሆነለት አእምሯችን እንደ አዲስ ነው የሚነቃው። ለአእምሯችን እረፍት የማንሰጠው ከሆነ ግን አእምሯችንን እንጎዳዋለን፡፡ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ቀላል መስለው ቢታዩም አእምሯችንን እየጎዱት ነው፡፡ ስለዚህ በፍጥነት ማቆም አለብን፡፡

ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ሀብቶቻቸውን በማቀናጀት በጋራ እየሰሩ ያሉት ዩኒቨርሲቲውና ኮሚሽኑ

መክሲት ወንድወሰን

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ባሉት ስምንት የልህቀት ማዕከላት ብቁ ዜጎችን እና ባለሙያዎችን ለማፍራት ይሰራል፡፡ በዚህም ካሉት የልህቀት ማዕከላት ጋር ተዛማጅ ተግባራትን ከሚከውኑ ትልልቅ ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ተቋማት ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡ ከነዚህም ተቋማት ውስጥ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽንን ለአብነት ማንሳት እንችላለን፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ጋር በመሆን በማዕድን ዘርፉ ላይ በማተኮር ባሳለፍነው ሳምንት የውይይት መድረክ አካሂዷል። በዛሬው እትማችንም ልናስቃኛችሁ የወደድነው በውይይቱ ወቅት ስለተነሱ ሀሳቦችና አስተያየቶች ነው፡፡

በአዲስ አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና በአፍሪካ ህብረት መካከል ያለው አጋርነት በተለያዩ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ አብሮ መስራታቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በሁለቱ ተቋማት መካከል የሚደረገው ትብብር እውቀትን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ እድሎችን ይፈጥራል። ይህ ትብብር የምርምር፣ የፖሊሲ ልማት እና የአቅም ግንባታ ውጥኖችን በጥራት ለመከወንም ያግዛል። በተጨማሪም በሁለቱ ተቋማት መካከል በመተባበር የጋራ ተግዳሮቶችን ለመፍታት እና የጋራ ግቦችን ለማሳካት እና ሀብቶችን መጠቀም እንዲችሉም ያደርጋል።

ዩንቨርሲቲው በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የወደፊት መሪዎችን፣ ባለሙያዎችን እና ተመራማሪዎችን በማስተማር እና በማሰልጠን ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመተባበር ምሩቃን የአህጉሪቱን ተግዳሮቶች በብቃት ለመቅረፍ የሚያስፈልጋቸውን ክህሎት እና እውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ የትምህርት ፕሮግራሞቹን እና የምርምር ተግባራቶቹን ከአፍሪካ አህጉር የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር በማቀናጀትም ይሰራል።



ሚስተር ቺዛ ቻርለስ

ዩኒቨርሲቲው እና የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን በአፍሪካ ዘላቂ ልማት ግቦችን እውን የማድረግ አላማ አላቸው። በአጋርነታቸው እውቀት እና ሀብቶቻቸውን በማቀናጀት የተባበሩት መንግሥታት የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት በጋራ ይሰራሉ።

በእለቱም የተገኙት በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት አብርሃም ደበበ (ዶ/ር)፤ ኮሚሽኑ በእውቀት ግንባታ፣ በፈጠራና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባዋል ብለዋል። የአፍሪካ አዳዲስ ምርምሮችን በማፍለቅ ምርት ከውጭ ማስገባት በማቆም እሴት ጨምሮ ምርትን ወደ ውጭ በመላክ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ እንደሚገባቸውም አስታውቀዋል።

በቴክኖሎጂ ዘርፍ የእውቀት እና የተማረ የሰው ሃይል ማነስ፣ ምርምርና ፈጠራ ላይ በቂ ሀብት መድቦ የምርምርና የፈጠራ ሥራዎች እንዲተገበሩ ያለማድረግ፣ ያሉ ሀብቶችን ማስተሳሰር አለመቻል የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብቶች አውጥቶ እሴት ጨምሮ ለመላክ ተግዳሮት ናቸው፡፡



አብርሃም ደበበ (ዶ/ር)

ዩኒቨርሲቲው ሲመሠረት ሀገርንና አህጉርን በተለያዩ ጉዳዩች እንዲያግዝ የተቋቋመ ነው ያሉት ዶ/ር አብርሃም፤ ምርምርን ከሃሳብ ወደ ምርት ለመቀየር የተመራማሪዎችን አቅም መገንባት፣ የዘርፉን መሠረተ ልማት ማሳደግ፣ ለምርምር ዘርፉ ተገቢ በጀት እንዲመደብ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የማእድን ዘርፉ ለዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል። ለውጤቱም የተለያዩ ተቋማት ተባብረው መሥራት አለባቸው ብለዋል። ኢኖቬሽንና ምርምር ላይ የሚደረጉ ትግበራዎች ከኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል።

ፈጠራና ምርምርን ከመንግሥት የልማት እቅድ ጋር በማገናኘት ለዘላቂ የልማት ግብ መሳካት የራሱን ድርሻ ማበርከት እንደሚገባም ይጠቁማሉ። አፍሪካውያን በሚገባ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብት እሴት ጨምረው መሸጥ ሲችሉ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ምርምር ላይ የሚገባውን ያህል ትኩረት በመስጠት በጀት ሊመደብ ይገባል። "የምርምር ሥራ አሁን ሳይሆን የቀጣዩን ትውልድ የሚጠቅም ነው። ምርምር ላይ ሀብታቸውን የሚያፈሱ ሀገራት በኢኮኖሚ ከፍ ያለ ደረጃ እንዳላቸው ያሳያል።"ብለዋል፡፡

በየአመቱ ደረጃ በማውጣት የሚታወቀው ግሎባል ኢኖቬሽን ኢንዴክስ ደረጃ ሲያወጣ የተለያዩ ግብዓቶችን ወስዶ ነው። መሠረተ ልማት፣ የተማረ የሰው ሃይል በምርምር ሥራ ያለው ድርሻ፣ የፈጠራ ውጤቶችን፣ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ታሳቢ ያደርጋል ብለዋል። በዚህ ያለንበት ደረጃ ዝቅተኛ የሚባል በመሆኑ ያንን ታሪክ መቀየር እንደሚገባም አሳስበዋል።

ሃገራት የተፈጥሮ ሀብትን እሴት ጨምሮ መሸጥ ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው የተናገሩት ዶክተሩ፣ ለትግበራውም ለምርምር ዘርፉ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የተፈጥሮ ሃብቶችን እሴት ጨምሮ ለመላክ በሚደረገው ርብርብ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በምርምርና በሰው ሃይል አቅርቦት ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብቷል። አፍሪካ ህብረት ኮሚሽንም ዩኒቨርቲው ለምርምርና ጥናት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግና ዩኒቨርሲቲውን ከሌላ አጋር ድርጅቶች ጋር በማስተሳሰር አብሮ ለመሥራት ተስማምቷል።

በአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የማዕድን፣ የኢንዱስትሪ የሥራ ፈጠራና የቱሪዝም ዘርፍ ዳይሬክተር ሚስተር ቺዛ ቻርለስ የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች በምርት ላይ አተኩረው እንዲሰሩ፣ ምርትና ምርታማነትን በብዛትም ሆነ በጥራት አምርተው ወደ ገበያ እንዲያወጡ ማስቻል ያስፈልጋልም ብለዋል። የሚደረጉ የምርምር ውጤቶችም ከመደርደርያ ወርደው ሊተገበሩ ይገባል፡፡

አፍሪካ በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች ብትሆንም እሴት ጨምሮ ከመላክ ይልቅ ጥሬ እቃዎችን በመላክ የሚገባትን ያህል እንዳልተጠቀመች ተናግረዋል። እሴት ጨምሮ በመላክ ሀገርንም አህጉርንም ማሳደግ እንደሚገባና የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል።

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

ከኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም


# የከተማ ግብርናን ያሻገሩ የልማት ጀግና

ሸምሱዲን ዩሱፍ

"ምግቤን ከጓሮዬ" ተብሎ የተጀመረው የከተማ ግብርና ዛሬ ወደ ልማት መስክ ተሻግሯል። በዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ ታግዞ አበረታች ውጤት እያስመዘገበም ይገኛል። ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትም የራሱን ድርሻ እየተወጣ ነው።ይህንን እውነታ በተግባር ካረጋገጡት የልማት ጀግኖች መካከል አርሶ አደር ግስላ ዘውዴ አንዱ ናቸው።

አርሶ አደር ግስላ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የሪፌንቲ መንደር ነዋሪ ናቸው። የስድስት ልጆች አባት ሲሆኑ አንድ ቀን የቤተሰባቸውን አባላት ሰብስበው ስለ ወደ ፊት ኑሯቸው በጋራ ተወያዩ፣ ተመካከሩ፤ ወሰኑ። የእርሻ መሬታቸን ለተሻለ ልማት ለማዋል ቆርጠው ተነሱ። ባህላዊ የእርሻ ዘዴን ትተው ዘመናዊ የከተማ ግብርናን ለመተግበር ተስማምተው በታላቁ ልጃቸው እቅድ መሰረት በ2013 ዓ.ም ውስጥ ወደ ስራ ገቡ። ድርጅታቸውንም ሪፌንቲ አግሮ ኢንዱስትሪ ብለው በመንደራቸው ስም ሰየሙ። ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በድርጅታቸው ውጤታማነት ብቻ ሳይሆን የቤተሰብ አባላትን በማስተባበር በአንድ ጥላ ስር ተሰባስበው በአንድ ልብ ከልብ እንዲሰሩ በማድረግ በቤተሰብ ደረጃም ግምባር-ቀደም መሆን ቻሉ።

ሪፌንቲ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተመስርቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ በውጤት ታጅቦ ግንባር ቀደም መሆን የቻለ ድርጅት ነው። ድርጅቱ በቅርብ ጊዜ ወደ ስራ ቢገባም ዛሬ ሁሉንም በአንድ ቦታ በመተግበር ሀገራዊ የሌማት ትሩፋት ፕሮግራምመርሐ ግብርን ውጤታማነት በተግባር አረጋግጠዋል። ድርጅቱ በዘመናዊ መንገድ የእንቁላል ዶሮዎችና የተሻሻሉ የወተት ላሞችን ያረባል፤ በሬዎችን ያደልባል፤





በከተማ ግብርና ስኬታማ መሆን ይቻላል



አርሶ አደር ግስላ ዘውዴ

የተመጣጠነ የእንስሳት መኖን ያመርታል።

ድርጅቱ እንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታውን በ1ሺህ 500 ዶሮዎች ነው የጀመረው። አሁን ላይ ዶሮዎቹ 13 ሺህ 500 የደረሱበት መልካም አጋጣሚ ተፈጥሯል። ድርጅቱ በአንድ ቀን 10 ሺህ እንቁላልም ያመርታል።

የዶሮ እርባታ ጥንቃቄን ይጠይቃል። ውጤታማ ሊሆን የሚችለውም በባለሙያ በትክክል ሲደገፍ ነው።

ዶክተር ስለሺ ወንድምአገኘው በሪፌንቲ አግሮ ኢንዱስትሪ የዶሮ እርባታ ኃላፊ ናቸው። "የዶሮዎቹን ጤንነት በተመለከተ እኛ ባለሙያዎች ስለሆንን በየሰዓቱ እንከታተላቸዋለን። እኔ ከ10 አመት በላይ በዶሮ እርባታ ስራ ላይ ቆይቻለሁ። በቂ እውቀትና የስራ ልምድ አለኝ። ለሰራተኞቻችንም ስልጠና እንሰጣቸዋለን። ለዶሮዎቹ አስፈላጊውን እንክብካቤ ሁሉ እናደርጋለን፤ በየሁለት ወሩም እንከትባቸዋለን" ብለዋል።

ድርጅቱ የወተት ላሞች እርባታን በስድስት ላሞች ነበር የጀመረው። ዛሬ ከነጥጆቹ 70 ደርሰዋል። በባለሙያ የተሻሻለ ጥሩ ዝሪያ በደንብ መርጦ ስለገዛ ምርቱም የተሻለ ነው። በአንድ ቀን (ጥዋትና ማታ) አለባ ከአንድ ላም 28 ሊትር ወተት ያገኛል። በአንድ ቀን 600 ሊትር ወተት ያመርታል። በተጨማሪም በሬዎችን በዘመናዊ መንገድ አደልቦ ለሀገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል፤ ጥሩ ገቢም ያገኛል።

የገበያ ትስስርን በተመለከተ ከወረዳና ክፍለ-ከተማ ሸማቾች ጋር ትስስር ፈጥሮ በቅናሽ ዋጋ ያቀርብላቸዋል። ካለው ወቅታዊ የገበያ ሁኔታ አንፃር ህዝቡን ለመደገፍ ብዙም ሳያተርፍ በቅናሽ ነው የሚሸጥላቸው። ለሸማቾችም ሆነ ለአካባቢው ማህበረሰብ አንዱን እንቁላል እስከ ስምንት ብር ድረስ ይሸጣል፤ አንድ ሊትር ወተት ደግሞ ከ55 እስከ 60 ብር ይሸጣል። በአጠቃላይ ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ ህብረተሰብ የእንስሳት ተዋፅዖ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል።

ድርጅቱ በራሱ ማቀነባበሪያ ማሽን የተመጣጠነ የእንስሳት መኖ ያመርታል። በቆሎ፣ አኩሪ አተር፣ ኖራ ድንጋይ፣ ደም፣ አጥንትና ሌሎችን ወደ 10 ዓይነት ግብዓቶችን በመጠቀም ጥራት ያለውን መኖ ያመርታል። እንስሳት የሰጧቸውን ይሰጣሉና ለወተት ላሞች፣ ለስጋ ከብቶች ለእንቁላል ጣይ ዶሮዎችና ለቄብ ዶሮዎች የሚያዘጋጀውን የተመጣጠነ መኖን ከራሱ አልፎ ለአካባቢው እንስሳት አርቢዎችም ያቀርባል።

የስራ እድልን ከመፍጠር አንፃር ድርጅቱ የራሱን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል። 55 ቋሚና 20 ጊዜዊ ሰራተኞች አሉት። በአጠቃላይ ለ75 ሰራተኞች የስራ ዕድል ፈጥሯል። እንደየስራቸው የተሻለ ደመወዝ ይከፍላቸዋል፤ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅምም ይሰጣቸዋል። ከማደሪያ ጀምሮ ምግብም እዛው ስለሚዘጋጅላቸው የሰራተኞች አያያዝም የተሻለ ነው።

"የኛ ተሞክሮ ወደ አካባቢው እንዲስፋፋ ብዙ ሰርተናል። የአካባቢው አርሶ አደሮች ከኛ ልምድ እንዲቀስሙ እናስጎበኛቸዋለን፤ ስልጠና እንሰጣቸዋለን። የሚጠበቅብንን ድጋፍ እናደርግላቸዋለን። ከትንሽ ጀምረው ዛሬ ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሱ አሉ" ያሉት አቶ ግስላ፣ ለእሳቸው መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንደሚያደርግላቸው ነግረውናል።እኛም ተሞክሯቸው በሌሎች ከተሞች አካባቢ ይስፋ እንላለን።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት


## እየተጠናቀቀ ያለው የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም- የመሠረተ ልማት ግንባታ

ዳግም ከበደ

መንግሥት ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ የዘርፉን መሠረተ ልማቶች በመገንባት ላይ ይገኛል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ታላላቅ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፣ ግንባታቸውም በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተጠናቀቀም ነው፡፡ በአዲስ አበባ በገበታ ለሸገር የተገነቡት የአንድነት ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይና የእንጦጦ ፓርክ ፕሮጀክቶች ከእነዚህ መካከል ይጠቀሳሉ፤ ፕሮጀክቶቹ ግንባታው ተጠናቆ ወደ ሥራ ከገቡ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

መንግሥት በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ደግሞ በጎርጎራ፣ በኮይሻና በወንጪ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችን እየገነባ ይገኛል፡፡ የኮይሻ አካል የሆነው የሀለላ ኬላ ሪዞርት ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት የተደረገ ሲሆን፣ የወንጪና የጎርጎራ ፕሮጀክቶችም ግንባታቸው ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በገበታ ለትውልድ ደግሞ የሌሎች ተመሳሳይ በርካታ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተጀመረ ይገኛል፡፡

አዲስ አበባን ጨምሮ በየክልሎቹ እየተተገበሩ ያሉት እነዚህ የቱሪዝም መሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜና ጥራት መከናወናቸው፣ ፕሮጀክቱን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳና ጥራት መገንባት እንደሚቻል ያመላከቱና በኢንቨስተሮች ፍላጎት ላይ በጎ ተፅእኖ የፈጠሩ ናቸው። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ሃሳብ አፍላቂነት ትግበራ ላይ ከሚገኙት "የገበታ ለሀገር" ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነው "የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም" ግንባታ ሂደትም የዚህ ማሳያ መሆን ይችላል።


የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም- የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከ90 እስከ 95 በመቶ ተጠናቋል

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ማኔጀር አቶ ብርሃኑ ተስፋዬ፣ "የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት ‹‹ወንጪ›› እና "ደንዲ" በመባል የሚታወቁ ሁለት ሃይቆችን ያማከለ የቱሪዝም መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ መሆኑን ይናገራሉ። የመጀመሪያው ዙር የመሠረተ ልማት ግንባታም "ወንጪ" ላይ ልዩ ትኩረቱን አድርጎ ሲተገበር መቆየቱን ጠቅሰዋል። ይህ ፕሮጀክት ሲጀመር በ10 ዓመት ውስጥ በሶስት ዙር እንዲጠናቀቅ ታስቦ ነው፡፡ አሁን ግንባታው መጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሰው "የወንጪ ኢኮ ቱሪዝም" መሠረተ ልማት ግንባታ በመጀመሪያው ዙር ላይ የተያዘ መሆኑን ይገልፃሉ።

የወንጪና ደንዲ አካባቢዎች ምንም ዓይነት መሠረተ ልማት (መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት) የሌለባቸው ቦታዎች እንደነበሩ ያስታወሱት አቶ ብርሃኑ፤ እነዚህን ዋና ዋና ጉዳዮች ማሟላት፣ የቴሌኮም የኔትወርክ ጥራቱን ማሳደግ እንዲሁም ለጎብኚዎች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሎጆችን ለመሥራት በማቀድ ፕሮጀክቱ መጀመሩን ያመለክታሉ። በዚህም ሁሉም የመሠረተ ልማት እቅዶች ተተግብረው ግንባታቸው ከ90 እና 95 በመቶ በላይ መድረሱንና ለምረቃት ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

"በመጀመሪያው ዙር የወንጪ ኢኮ ቱሪዝም ግንባታ ሁሉም እቅዶች ተተግብረው የመጨረሻው ማጠናቀቂያ ደረጃ ላይ ተደርሷል" የሚሉት ማኔጀሩ፤ በመንገድ ግንባታው ከአምቦ ወደ ወንጪ የሚወስደው፣ የወንጪ ዙሪያው፣ ወደ ሐይቁ የሚወስደው፣ ወንጪን ከደንዲ የሚያገናኘው እና የመሮጫ መም (ትራክ) የሚይዘው መንገድ ግንባታ ከ98 በመቶ በላይ መጠናቀቁን ይገልፃሉ። ሌላው ደካማ የነበረው የቴሌኮም አገልግሎትን ለማሻሻል በተከናወነው ተግባርም የአካባቢውን የቴሌኮም አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ወደ 4ጂ ደረጃ ከፍ የማድረግ ሥራ መከናወኑን ይገልፃሉ።

አቶ ብርሃኑ እንደሚገልፁት፣ በመጀመሪያው ዙር የወንጪ ኢኮ ቱሪዝም ግንባታ ከተያዙት ውስጥ የመጠጥ ውሃ ግንባታና ዝርጋታ አንዱ ነው፡፡ በአካባቢው የጉድጓድ ቁፋሮ ተካሂዶ ውሃው ወጥቷል፤ የሥርጭት መስመር ዝርጋታው እየተካሄደ ነው። ይህም ሂደት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ በሚፈለገው መልኩ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰራ ይገኛል፡፡

ሌላው የመሠረተ ልማት ግንባታ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ መሆኑን በማንሳትም፣ በዚህም ረገድ ከወሊሶ ከሚመጣው የኤሌክትሪክ መስመር ኤሌክትሪክ ኃይል በመጥለፍ ለሎጅ፣ ለመንገድ እና ለሁሉም የወንጪ አካባቢ የኃይል ፍላጎቶች ለማድረስ የመጨረሻ ደረጃ የዝርጋታ ሥራ እየተከናወነ ነው ይላሉ።

"በዚህኛው ዙር አንድ ደረጃውን የጠበቀ ኢኮ ሎጅ በወንጪ ፕሮጀክት እየሰራን ነው" የሚሉት የመሠረተ ልማት ፕሮጄክት ማኔጀሩ፤ የዚህ ሎጅ ግንባታም ከ92 በመቶ በላይ መጠናቀቁን ጠቁመዋል። በሂደቱ የቀሩት የማጣሪያ፣ የእቃ ማስገባትና መሰል አነስተኛ ሥራዎች መሆናቸውንም ይገልፃሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ አብዛኛው የኢኮ ቱሪዝም ግንባታው የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ የወንጪ አካባቢ አርሶ አደሮችን ከቦታው ከማንሳት ይልቅ በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚል 13 የሚደርሱ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተውላቸዋል። እነዚህ አርሶ አደሮች ኑሯቸው ከማህበረሰብ አቀፍ ሎጁ ጋር የተሳሰረ እንዲሆንና የዚያም ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይህ ፕሮጀክት የእቅዱ አካል አድርጓቸዋል። በሂደቱም ሁሉም አርሶ አደሮች የወተት ላሞች ተሰጥቷቸዋል። የእርሻ መሬታቸውንም ወደ ኢኮ- ግብርና ቀይረው ለቱሪዝም ፕሮጀክቱ አቅራቢ በሚሆኑበት መንገድ እንዲተሳሰሩ ተደርጓል፡፡ የተገነቡትን ቤቶችም በዚህ ሳምንት ለአርሶ አደሮቹ የማስረከብ ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል፡፡

### የኮንትራክተሮች አፈፃፀም

በመጀመሪያው ዙር እየተተገበረ ባለው የወንጪ ኢኮ ቱሪዝም ግንባታ ላይ በርካታ ኮንትራክተሮችና ንዑስ ኮንትራክተሮች ተሳታፊ ሆነዋል። በመንገድ እና ሌሎች መሰል የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ላይ የተሳተፉት የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋራጮች አፈፃፀም ውጤታማ መሆኑንም አቶ ብርሃኑ ይናገራሉ።

የመንገድ ግንባታው በሀገር ውስጥ ኮንትራክተር 48 ኪሎ ሜትር እንደተሰራ በመግለፅም የቻይና ኮንስትራክሽን ኮሙዩኒኬሽን ኩባንያ ስድስት የሚደርሱ ንዑስ ኮንትራክተሮችን በመቅጠር እንደተሳተፈና ውጤታማ ሥራ እንደተሰራ ይገልፃሉ። የወንጪ አካባቢ ዝናባማና የአፈሩም ሁኔታ ምቹ እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ ግንባታ ጊዜው ሲፈቅድ ብቻ እየተሰራ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡ በሂደቱ ግን ውጤታማ ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው፣ ወደ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ አፈር መቆረጡንና አስቸጋሪ የአየር ንብረትን በመቋቋም እንደተተገበረ ይናገራሉ።

በመንገድ ግንባታው ላይ ከተሳተፉት ኮንትራክተሮች መካከል የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ አንዱ መሆኑን የሚገልፁት አቶ ብርሃኑ፣ ወደ ሎጁ የሚወስደውን 10 ኪሎ ሜትር መንገድ መገንባቱን ይገልፃሉ። የዚህ ግንባታ ሂደትም ተመሳሳይ የአየር ፀባይና የመልከዓ ምድር አስቸጋሪነት ማጋጠሙን ጠቅሰው፣ ቀንና ሌሊት ለ18 ሰዓታት በመሥራት የተሻለ አፈፃፀም እንደታየ ይገልፃሉ።

የሎጅ ግንባታውን የጣሊያን ኮንስትራክሽን ኩባንያ እንደያዘው የሚናገሩት ማኔጀሩ፤ ኩባንያው ወደ ሥራ ከገባ አንድ ዓመት ከስምንት ወር ሆኖታል ብለዋል። ከሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቶች በተለየ ሥራውን የተቀበለው ዘግይቶ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ወደ ማጠናቀቂያው ደረጃ መድረሱን ይናገራሉ። የወንጪ አካባቢ ቀዝቃዛማ የአየር ንብረት ያለው፣ ዝናብ የሚጥልበት እና ከፍተኛ መልከዓ ምድር ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፣ ቀንና ሌሊት በሙሉ ጊዜ ሥራው እየተተገበረ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ግንባታው በአሁኑ ወቅት የመጨረሻው ደረጃ ላይ መድረሱን ጠቁመዋል።

### የንድፍ ሥራ

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም አጠቃላይ ይዘትና ገፅታ ለቱሪዝም መስህብ እንዲመጥን የንድፍ ሥራ ተተግብሯል። ፅንሰ ሃሳቡ በኤም ኤች (MH) ኢንጂነሪንግ ቢሰራም አጠቃላይ የንድፍ ሥራው በጣሊያን ኩባንያው "ሳሊኒ" ድጋፍ በጣሊያን ሀገር በሌላ ኩባንያ መሠራቱን የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ማኔጀሩ ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከመንገድ ግንባታው ጋር በተያያዘም የሀገር ውስጥ የንድፍ ሥራ ኩባንያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የኦሮሚያ ቢፕ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንና፣ ጂኤንድ ዋይ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተሳትፈዋል፡፡ በሎጅ ግንባታው ደግሞ የጣሊያን ኩባንያዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ በአርሶ አደር ቤቶች ግንባታ እንዲሁም በሌሎች የግንባታ ሂደቶች ላይም የሀገር ውስጥ አማካሪዎች በንድፍ (ዲዛይን) ሥራው ላይ ተሳታፊ ሆነዋል። በዚህ ሂደትም ውጤታማ አፈፃፀም መታየቱን ጠቅሰው፣ የአካባቢውን ባህል እና የኑሮ ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ ለመሥራት እድሉ መፈጠሩን ገልጸዋል።

### ሁለተኛና ሶስተኛ ዙር ትግበራ

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም በሶስት ደረጃዎች የሚተገበርና በጥቅሉ አስር ዓመታትን የሚወስድ ፕሮጀክት ነው። አሁን ግንባታው ተጠናቆ ለምረቃ እየተዘጋጀ የሚገኘው "የወንጪ ኢኮ ቱሪዝም" ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር እንዲጠናቀቅ የታቀደ ነው። ቀሪ ሁለት ዙሮች እንደሚኖሩና ግንባታው እንደሚቀጥልም የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ማኔጀሩ አቶ ብርሃኑ ተስፋዬ ይናገራሉ።

"ከስሙ መረዳት እንደምንችለው ፕሮጀክቱ ወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ነው" የሚሉት ማኔጀሩ፤ እየተተገበሩ የቆዩት በወንጪ፣ በደንዲ እና በሁለቱም መካከል ላይ የሚለሙና የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መሆናቸውን በዝርዝር ጠቁመዋል።

በሁለተኛው ዙር የሚከናወኑት በደንዲ የሚሰሩ ልማቶች ሲሆኑ፣ አሁን አንዳንድ ሥራዎች ተጀምረዋል። በዚህም በአካባቢው አንድ ሎጅ እየተሰራ መሆኑን ገልፀው፣ ይህም የፕሮጀክቱ አካል መሆኑን ይገልፃሉ። የሁለተኛው ዙር አካል የሆኑት ሌሎች ሥራዎች ደግሞ በግል ባለሃብቶችና ኢንቨስተሮች የሚሰሩት መሆናቸውን ጠቅሰው፣ እነርሱም በወንጪ የሚሰሩ ሎጆችን እንደሚያካትቱ ጠቁመዋል።

ወንጪንና ደንዲን በሚያገናኘው 13 ኪሎ ሜትር መንገድ መካከል ላይ የተወሰነ ቦታ መኖሩን የሚናገሩት የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ማኔጀሩ፤ በዚያ ስፍራ ላይ ግዙፍ የስብሰባ ማዕከላት (convention center)፤ የአትሌቲክስ መንደር፣ የውሃና የመዝናኛ ፓርኮች፣ የጎልፍ ስፖርት መንደር፣ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴሎች ለመሥራት መታቀዱን አብራርተዋል። የዚህ ዲዛይን እና ዋና ፕላን ተጠናቆ ለባለሃብቶች ጥሪ የማድረግ ሂደት እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

"ሁለቱ ሐይቆች መስህብ ያላቸው ናቸው" የሚሉት የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ማኔጀሩ፤ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ጫና መፍጠርና በግንባታ ማጨናነቅ ተገቢ አለመሆኑ እንደታመነበት ይናገራሉ። በዚህ መሠረትም በወንጪና በደንዲ መካከል ያለውን ቦታ በመለየት ከላይ ለተጠቀሱት ፕሮጀክቶች ግንባታ ለማዋል መታሰቡን ያስረዳሉ። ሥራዎቹም በሁለተኛና ሶስተኛ ዙር በሚሰሩት የልማት ሥራዎች ውስጥ መካተታቸውንም ይገልፃሉ።

### እንደ መውጫ

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም በስፔን ማድሪድ ተካሂዶ በነበረው በ24ኛው የዓለም የቱሪዝም ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የ2021 ምርጥ የቱሪዝም መንደር ሆኖ መመረጡ ይታወሳል።

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም እንደ ሀገር እየተሰሩ ካሉ ትልልቅ የቱሪዝም መዳረሻዎች መካከል አንዱ ነው። በሶስት ምዕራፎች ተከፍሎ እንደሚሰራ የተነገረው ፕሮጀክቱ፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ በሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመጠናቀቅ የቀሩት ጥቂት ጊዜያት መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የአካባቢውን ነዋሪ "ጥያቄ የመለሰ" ፕሮጀክት ስለመሆኑ ማህበረሰብ በተለያየ አጋጣሚ ሲናገር ተደምጧል። የመጀመሪያው ምዕራፍ ሊጠናቀቅ ጫፍ መድረሱና የሁለተኛና ሶስተኛው ሥራ በሂደት ላይ መሆኑንም ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም የቱሪዝም መስህብ ስፍራ ተጨማሪ ሃብት እንደሚሆን ይጠበቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርን የመከላከልና የመቆጣጠሩ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥል!

ሀገራችን በማዕድን ሀብት ከታደሉ ሀገራት አንዷ ናት፡፡ ከከበሩ ማዕድናት ጀምሮ ከፍተኛ የእምነበረድ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የተፈጥሮ ጋዝ ፣ የታንታለም ፣ የጂብሰም፣ የኖራ ድንጋይ... ወዘተ ማዕድናት እምቅ ሀብቶች ባለቤት ነች፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እንደ ሊቲየም ያሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈላጊነታቸው ከፍተኛ የሆኑ ማዕድናት እየተገኙ ነው፡፡

አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ የማዕድን ሀብቶች በጥናት ያልተለዩ ፤ የተለዩትንም ቢሆን አልምቶ ጥቅም ላይ በማዋል በተገቢው መልኩ ተጠቃሚ የመሆናችንም እውነታ ብዙ ክፍተቶች እንዳሉ ይታመናል። በተለይም የማዕድን ልማቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና የአመራረት ሥርዓት አለመታገዙ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን እንዳታገኝ ተግዳሮት ሆኖባታል።

መንግሥት ዘርፉን እየተፈታተኑ የሚገኙ ችግሮችን ለዘለቄታው ለመፍታት ባለፉት አምስት ዓመታት ለሀብቱ የተለየ ትኩረት በመስጠት፤ ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ተግባራዊ እያደረገው ባለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ውስጥም የሀገር ኢኮኖሚ ምሰሶዎች ተደርገው ከተያዙት አምስት ዘርፎች አንዱ መሆኑን አስታውቋል፡፡

የማዕድን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮም ዘርፉን በማነቃቃት ሀገሪቱ ያላትን እምቅ የማዕድን ሀብት በአግባቡ እንድትጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ይታመናል። ዘርፉን በማስተዋወቅ፣ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በማስፋትና በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የገበያ ትስስር ለመፍጠር ተስፋ ሰጪ ሥራዎችን እየሰራ ነው፡፡

በዚህም በተጨባጭ እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች፤ በርግጥም የማዕድን ዘርፉ የሀገሪቱ ዋነኛ የልማት ምሰሶ የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አመላካች ነው። በተለይም ዘርፉን ለማዘመን ሆነ በስፋት ለማስተዋወቅ የሚደረጉ ጥረቶች በሚመለከታቸው አካላት ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያገኙበት ዕድል ከተፈጠረ ዘርፉ የዜጎች የነገ ተስፋ ስንቅ መሆኑ የማይቀር ነው።

ይህም ሆኖ ግን አሁን ላይ ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ እየተፈታተነ ያለው ሕገወጥ የማዕድን ዝውውር የሁሉንም ትኩረት የሚሻ ፤የመላው ሕዝባችንን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ደረጃ ላይ ከደረሰ ውሎ አድሯል። እንደ ሀገርም እያሳጣን ያለው ሀብት በቀላሉ የሚሰላ እንዳልሆነ ሲገለጽ ቆይቷል።

ችግሩ በርግጥ እንደ ሀገር እያሳጣን ካለው ሀብት አንጻር የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርን መቆጣጠር የሚያስችል ብሄራዊ ግብረ ኃይል ባለፈው አመት መቋቋሙ ይታወሳል። በዚህም እየተመዘገበ ያለው ውጤት ዘርፉ የቱን ያህል ለሕገወጦች የተጋለጠ እንደሆነ እያመላከተ ይገኛል።

በቅርቡ የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቴዎስ ችግሩን በማስመልከት እንዳስታወቁት፤ ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርን ለመቆጣጠር የተቋቋመው ግብረ ኃይል በሕገወጥ የማዕድን ዝውውር የተሳተፉ ከ100 በላይ የውጭ ሀገር ዜጎች በሕግ እንዲጠየቁና በአስገዳጅ ሁኔታ ከሀገር እንዲወጡ ተደርጓል ብለዋል።

በሕገወጥ የማዕድን ማውጣትና ንግድ ተሠማርተው የተገኙት ሕገወጦች አብዛኞቹ የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው መሆኑ ፤ትኩረታቸውም በሀገሪቱ የወርቅ ሀብት ላይ የመሆኑ ጉዳይ፤ ችግሩን ለመቆጣጠር የሚደረገው ሀገራዊ ጥረት በጠንካራ ዲሲፕሊን መመራት እንዳለበት የሚያመላክት ሆኗል።

በተለይም ሀብቱ የሚገኝባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የአስተዳደርና የጸጥታ አካላት ፤ሕገወጥ የማዕድን ዝውውር ሀገርና ሕዝብን የቱን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል ፤ ለጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ጥረት ትልቅ ተግዳሮት መሆንን በአግባቡ ተረድተው ፤ ኃላፊነት በሚሰማው መንገድ ሊንቀሳቀሱ እንደሚገባ፤ ችግሩ ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ነዋሪዎችን በስፋት ማስተማር እንደሚያስፈልግ ያመላከተ ነው።

ሀብቱ እንደ ሀገር ዘላቂ ልማት ለማካሄድ ካለው ስትራቴጂካዊ አስተዋጽኦ አንጻር ፤ ከምርት አንስቶ እስከ ገበያ ያለው ትስስር በሕግና ሥርዓት የሚመራበትን አሰራር መፍጠር ፤በዘርፉ ያለውን የተጠያቂነት ሥርዓት ማጠናከር ያስፈልጋል፤ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት ከፍያለ እንደሆነ ይታመናል።

የፌዴራል እና የክልል የፀጥታ መዋቅሮች በጋራ ተቀናጅተው የሚሠሩበትን አሠራር መዘርጋት ፤አሠራሩ በራሱ ሊመራበት የሚገባውን ጠንካራ ዲሲፕሊንና ተጠያቂነት መፍጠር እና ተግባራዊ ማድረግ ፤ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ያስፈልጋል።

በተለይም ሕገወጥ የማዕድን ዝውውር በስፋት በሚስተዋልባቸው የቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች እና በኦሮሚያ ክልል ጉጂ አካባቢዎች የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። በአካባቢዎቹ የሚካሄዱ የማዕድን ማልማት ሥራዎች በዘመናዊ መንገድ የሚከናወኑበት አሰራር እና ሥርዓትም መፍጠር ተገቢ ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስለዘላቂ ሰላም የሃይማኖት ተቋማት እና አባቶች ሚና

ሶሎሞን በየነ

በዓለም ላይ ያሉ ሕዝቦች 75 በመቶዎቹ በሃይማኖት ተጽዕኖ ሥር እንደ ሆኑ እና በከፍተኛ ሁኔታ ከሃይማኖት ጋር ቁርኝት እንዳላቸው ጥናቶች ያመላክታሉ። በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ ከጠቅላላው ሕዝብ 99 በመቶ የሚሆነው አማኝ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሃይማኖቱን አክባሪ፣ ፈጣሪውን የሚፈራ፣ ለእምነቱ ቀናዒና ተገዥ መሆኑን ከኛ አልፎ ዓለም ይመሰክርለታል።

ይህ ሃይማኖተኛና ፈርያ እግዚአብሔር ያለው ሰፊው የሀገሪቱ ህዝብ በአንድም ሆነ በሌላ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው በሚከተለው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ተጽዕኖ ሥር ያለ ነው። የሃይማኖት ተቋማትና አባቶቹ የሚሉትን የሚሰማ፣ ሰምቶም የሚፈጽም ነው። ይህ ደግሞ በራሱ ለማኅበራዊ አንድነት እና ለሰላም ግንባታ የሚኖረው አስተዋጽኦ መተኪያ የማይኖረው ነው፡፡

በተለይም የሃይማኖት አባቶች ልዩነቶችን በንግግርና በውይይት የመፍታት ባህል እንዲዳብር የሚኖራቸው ጠቀሜታ በቃላት የሚገለጽ አይደለም። በሃይማኖታዊ አባታዊ ተግሳጽና ምክራቸውም በዳይ እንዲክስ፣ ተበዳይ ደግሞ እንባው እንዲታበስ በማድረግ ይቅር በመባባል ሰላምን ለማጽናት የሚኖራቸው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

ዛሬ በሀገራችን በተዛቡ ንዑስ ትርክቶች፣ በጽንፈኛ እና አክራሪ አስተሳሰቦች እየተፈጠሩ ያሉ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ፤ ከዚህም ባለፈ ሀገራዊ ሰለምና አንድነትን በጸና መሰረት ላይ ለማዋቀር በሚደረገው አሁነኛ ጥረት ውስጥ የሃይማኖት ተቋማት ያላቸው ድርሻ በእጅጉ ሊታሰብበት የሚገባ ነው፡፡

በቀደሙት ዘመናት የሃይማኖት ተቋማትና አባቶች በትንሹም በትልቁም ሰላም እና ዕርቅ እንዲጸና መሰረት ነበሩ፡፡ በሀገራት ደረጃም የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ከዲፕሎማሲው ጎን ለጎን የሃይማኖት አባቶች ሰላምን በማውረድ ረገድ የነበራቸው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር፡፡

እንደ ሀገራችን ሃይማኖት፣ ባህልና ወግ ደግሞ ባል ከሚስት፣ ጎረቤት ከጎረቤት፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ በጥቅሉ አንድ ሰው ከሌላው በተለያየ ምክንያት ቢቃያየም የዕርቀ ሰላሙን ሥራ የሚከውኑት የሃይማኖት አባቶች ናቸው፡፡ “በእርቅ ደም እንዲደርቅ” ቄሱ ታቦትን ከዙፋኑ ይዞ ወጥቶ ይገዝታል፣ ሼህ በዱዋው ያስማማል፤ ያስታርቃል።

> “በእርቅ ደም እንዲደርቅ” ቄሱ ታቦትን ከዙፋኑ ይዞ ወጥቶ ይገዝታል፣ ሼህ በዱዋው ያስማማል፤ ያስታርቃል

በሀገራችን ትናንትም ሆነ ዛሬ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ጠብ እና ጦርነቶች ሲካሄዱ ኖረዋል። ሀገሪቱ ከገባችበት የግጭት አዙሪት ለመውጣት ደግሞ፤ የሃይማኖት ተቋማትና አባቶች ምዕመናቸውን ስለ ሰላም ከማስተማር ባለፈ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ በድርድርና በውይይት እንዲፈቱ ማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡

በመሆኑም በሀገሪቱ በተለያዩ ወቅቶች የተፈጠሩ ግጭቶች እንደ ሀገር በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ያደረሱት ኪሳራና ውድመት ዛሬ ላይ እንዳይደገም የሃይማኖት ተቋማትና አባቶች የሚጠበቅባቸውን መንፈሳዊና ሞራላዊ ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል። ለዚህም እራሳቸውን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

የተለያዩ ሃይማኖቶች አስተምህሮና ዶግማ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ስለ ሰላም ያላቸው አስተምህሮ ተመሳሳይ በመሆኑ በሀገሪቱ ዘላቂ ሰለም እንዲሰፍን በጋራ ሊመክሩና ሊሠሩ ይገባል። ግጭት ውስጥ ያሉ አካላትን ወደ ሰላም ጎዳና እንዲመጡ ሳይታክቱ ማስተማር ለአስተምህሮው ተፈጻሚነትም በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

ተቋማቱ በማህበረሰቡ ዘንድ ካላቸው ከፍተኛ ተቀባይነት አኳያ፤ በሰላማዊ መንገድ በድርድርና በውይይት አለመግባባቶች በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲፈቱ የአንበሳውን ድርሻ መወጣት ይችላሉ። በአንጻሩ ሰላማዊ መንገድን አልቀበልም ያለን አካል በማውገዝ እና ምዕመኑ ከሰላም ውጪ ያሉ ሃሳቦችን እንዳይገዛና እንዳይከተል በማስተማርና በመስበክ የጦርነት ነጋዴዎችንና በሰው ሕይወት የሚቆምሩ ነፍሰ በላዎችን እራቁታቸውን ማስቀረት ይችላሉ።

የሃይማኖት ተቋማትና አባቶች ዘላቂነት ካለው የሰላም አስተምሮ ባለፈም ፤ግጭት ውስጥ ያሉ አካላት ወደ ሰላም መንገድ እንዲመጡ ሊጮኹ፣ ሊመክሩ፣ ሊያስተምሩ፣ ሊዘክሩ፣ ሊገስጹ ... ይገባል። ይህም ሀገርን ከትርምስና ከውድመት፤ ንጹሃንን ከሰቀቅንና ከሞት ይታደጋል። እነሱም ከወቀሳና ከታሪካዊ ተጠያቂነት ይድናሉ። ለሰላም ዘብ በመቆምም ለሰላም የሚሰጡትን ዋጋ በተጨባጭ ያመላክታሉ።

ስለ ሰላም መምከር፣ አብዝቶ መሥራት፣ የሰላም መታጣት የሚያመጣውን ችግር በግልጽ ማስረዳት፣ ከደረሱብን የሰላም እጦት ሰው እንዲማርና ከሰላም ጎን አጥብቆ እንዲቆም ማድረግ ፤የጥላቻን ዘር በመዝራት የሚፈጸመውን አክራሪነት ለሀገር ሰላምና ደኅንነት ጠንቅ መሆኑን ማስገንዘብ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የሰላም ሐዋሪያ ስለመሆናቸው ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ሰላም ማኅበራዊ ዕሴት ነው። ሚዛናዊ የሆነ መስተጋብርን ይፈልጋል፡፡ የደካሞች ሰላም ሲከበር በማኅበረሰቡ ውስጥ የኃያላኑም ሰላም እንደሚከበር ለሰፊው ምዕምን ማስተማር ያስፈልጋል። በማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ የተለያዩ አንዳንዴም የተቃረኑ የፖለቲካ አስተሳሰቦች እና ያልተጣጣሙ ፍላጎቶች የተነሣ የፖለቲካ ትግል ይፈጠራል፡፡ ትግሉ ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ፤ከማህበረሰቡ ባሕል፣ እምነትና ግብረ-ገብነትን ተከትሎ ሊሆን እንደሚገባም ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ ውጪ ያሉ አካሄዶችን በግልጽ በማውገዝ፣ የተበደለ እንዲካስ፣ የበደለ ይቅር እንዲልና ሁሉም ወደ ሰላም ጎዳና እንዲመጣ በማድረግ ዘላቂ ሰላም በሀገሪቱ እንዲሰፍን የማይተካ ሚናቸውን ከመቸውም በላይ ዛሬ ላይ በቁርጠኝነት ሊወጡ ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ የጦርነትን አስከፊነትና አውዳሚነት ለኢትዮጵያ ህዝብ መናገር “ለቀባሪ” እንደማርዳት ይቆጠራል።

ስለዚህ ምዕመኑ የሃይማኖት አባቶችን የሰላም ጥሪ ጆሮ ሰጥቶ ሊያደምጥና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። የሚከተለውንም እምነት ለይስሙላ ሳይሆን በተግባር ሊኖረው ይገባል። ወንድምን ከወንድሙ ለማስተራረድ የጦርነት ነጋሪት የሚጎስሙ የጦርነት ነጋዴዎችን “ጆሮ ዳባ” በማለት እጅ ለእጅ ተያይዞ ለሰላሙ ዘብ ሊቆም ይገባል እላለሁ። ሰላም ለሀገራችን ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የኮርፖሬሽኑ የስኬት መስመር

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጥሩ ስም የለውም፤ ፕሮጀክት የሚጓተትበት፣ ጥራት ጥያቄ ውስጥ ያለበት፣ ሙስና ስር የሰደደበት፣ በአጠቃላይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት ችግር የተተበተበ መሆኑ ይገለጻል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፋይናንስ፣ የግብዓት፣ የአቅም፣ ወዘተ... ክፍተቶች እንዳሉበትም በተለያዩ መድረኮች ይጠቆማል። ይህን ሀቅ መንግሥትም፣ የዘርፉ ተዋንያንም በሚገባ ያውቁታል፡፡

በዛሬው የስኬት ዓምዳችን የምንዳስሰው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽንም ይህን የዘርፉን ችግር ያውቀዋል፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከዓመታት በፊት በፕሮጀክት ማኔጅመንት፣ በአመለካከት፣ በአቅም ውስንነትና በመሳሰሉት ችግሮች በእጅጉ ተፈትኗል። በአሁኑ ወቅት ግን በሀገሪቱ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በመገንባት የሚታወቅ ሲሆን፣ 55 ነጥብ ሰባት ቢሊየን ብር ኮንትራት ያላቸውን ፕሮጀክቶች እየገነባ ይገኛል፡፡

ድርጅቱ ቀደም ሲል ፕሮጀክት ከአምስት እስከ አስር ዓመት በእጁ ላይ የሚቆይበት፣ ሠራተኛውም ሆነ አመራሩ ለፕሮጀክት ያለው አመለካከት በእጅጉ የተዛባበት ነበር፤ በሠራተኛውና በአመራሩ መካከል ያለው የግንኙነት ክፍተትና የሀብት ብክነት እንዲሁም በደንበኞች ዘንድ እስከ አለመታመን የደረሰ ችግሮች ነበሩበት፡፡

በ2011 ዓ.ም ሂሳብ ሲዘጋ ከ500 ሚሊየን ብር በላይ ኪሳራ ነበረበት፤ በ2010 ዓ.ም ላይም እንዲሁ ከ600 ሚሊየን ብር በላይ ኪሳራ ታይቶበታል፡፡ ኪሳራው ደግሞ በዓለም አቀፍ ሁኔታም የኮንስትራክሽን ዘርፉ ችግር ባልነበረበት ወቅት የተፈጠረ ኪሳራ ነበር፡፡

ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው የሪፎርም ሥራዎች ግን በጥቂት ዓመታት ውስጥ እነዚህን ችግሮች በመፍታት ወደ አትራፊነት መመለስ መቻሉን የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ዮናስ አያሌው ይጠቅሳሉ። ለውጡ ከተተገበረ በኋላ በ2012 ማትረፍ መጀመሩን ያስታውሳሉ፡፡

ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ለሀገሪቱ ኢንዱስትሪያላይዜሽን የሚጠቅም ተግባር እያከናወነ እንደሚገኝም ይገልጻሉ፡፡ ኮርፖሬሽኑ መድረስ ያለበት ቦታ ለመድረስ ባከናወናቸው ተግባራት ብዙ ለውጦች ማስመዝገቡን ጠቅሰው፣ ለውጦቹ ግን ጅምር ናቸው ብሎ ኮርፖሬሽኑ እንደሚያምን ተናግረዋል፡፡

‹‹ወደ ለውጥ ሥራዎች ለመግባት መነሻዎቻችን አጠቃላይ የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ችግሮች ናቸው›› ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ እንደዚህ ዓይነት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ችግሮችን ለመፍታት ለሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለውጥ መሠረት መሆን የሚያስችል ተቋም መገንባት ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡

‹‹ሌላው የሪፎርሙ መነሻ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፕሮጀክቶች ናቸው፤ ፕሮጀክቶቹን እሳቸው እየመሩ እኛ መሥራታችን እሳቸው የሚመሩበትን ሥርዓት ወደ ተቋሙ ለማምጣት አስችሏል›› ይላሉ፡፡ እሳቸው ፕሮጀክቶች በሚመሩበት መንገድ ሌሎች ፕሮጀክቶችን መምራትና ማስተዳደር ቢቻል ትልቅ ስኬት ማስመዝገብ እንደሚቻል መረዳታቸውን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል፡፡

‹‹ከለውጡ በፊት ተቋሙ እንደ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም መሠረታዊ ችግሮች ነበሩበት›› ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ኮርፖሬሽኑ ሰው ሳይቀየር፣ ተቋም ሳይቀየር ሪፎርምን ማስተግበር አይቻልም ብሎ የመጀመሪያ ሥራ ያደረገው ተቋማዊ ሪፎርም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

‹‹የሰው ኃይሉ አመለካከት፣ የተቋሙ ችግሮች ሳይፈቱ ወደ ሌላ መሄድ አይቻልም ብሎ ተቋምና የሰው አመለካከት መለወጥ ላይ ሠራ፡፡ ለሠራተኛ ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር፣ በሠራተኛውና አመራሩ መካከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ላይም መሥራት ተጀመረ። ተልእኮዎችን መፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣ ሀብት እንዳይባክን ማድረግ፣ ገቢ ማግኛ ሥራዎችን መሥራት፣ ተቋሙ እምነት የሚጣልበት እንዲሆን ማድረግ ላይ ተሰራ፤ በዚህ ሁሉ መቶ በመቶ ስኬት ተመዘገበ›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ቀጣዩ ሥራ በፕሮጀክት አስተዳደር ላይ መሥራት ሆነ፡፡ ተቋሙ ፕሮጀክት በባህላዊ መንገድ የሚመራበት ነበር፡፡ ይሄ የሀገሪቱም ችግር ነው፡፡ ‹‹ዓለም አቀፍ ተቋም ለመሆን ይህን ችግር መፍታት አለብን ብለን ተነሳን፡፡


የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ዮናስ አያሌው

ለእዚህም ዓለም አቀፍ ከሆነው የፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ጋር በጥምረት ሠራን፤ ከዚያም የኛን የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሪፎርም ሎጎ አዘጋጅተንለት በ2013 ተገበርነው›› ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ቀደም ሲል የአንድ ቢሊየን ብር ፕሮጀክት ሲመጣ መሥሪያ ቤቱ አንድ ቢሊየን ብር የሚያገኝ የሚመስለው ብዙ ነበር፡፡ ፕሮጀክት ጨርሼ ይህን ያህል አትርፌ... ወጪውን ሸፍኜ አስረክባለሁ የሚል አስተሳሰብ ውስን ነበር፤ ፕሮጀክቶች አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ አስር ዓመት ይዘገዩ ነበር ሲሉም ይገልጻሉ፡፡

በሪፎርሙ እነዚህን ፕሮጀክቶች መምራት ይገባል በሚል ለማጠናቀቅ ጥረት ማድረግ ተጀመረ፡፡ በዚህም የተቋሙ ሪፎርም እንዲቀጥል ተደረገ፡፡ በዚህ ሥራም የኮርፖሬሽኑ የፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅም ከ80 በመቶ በላይ ደረሰ፡፡ ይህን ሥራ የሚመራ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንትና ዴቨሎፕመንት ማዕከል በማቋቋም ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉንም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፣ በዚህም ፕሮጀክት በየቀኑ የሚገመገምበት ሥርዓት እንደተፈጠረም ይገልጻሉ፡፡

ከፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅሙ 20 በመቶው ክፍተት ከግብዓት አቅርቦት ጋር የተያያዘ መሆኑን በመለየት ይህን ችግር የሚፈታ የዲጂታላይዜሽንና ኢንደስትሪያላይዜሽን ሪፎርም ማድረግ ውስጥ ተገባ፡፡ ‹‹ይህንንም ከምን እንጀምር ብለን ተነሳን፤ የተገጣጣሚ ፕሮጀክት መምሪያችንን ማሽኖች ከተጣሉት አንስተን መሥራት ጀመርን፤ አንድ ምርት ለማውጣት ብዙ ጊዜ ይወስድበት የነበረውን ይህን ተቋም በቀናትና በወራት ሥራዎች የሚጨርስበትን መንገድ ፈጠርን›› ሲሉም የዚህ ሪፎርም ስኬት መጀመሩን ገለጹልን፡፡ በዚህም ራሳችን አልሙኒየም እየቆራረጥን መገጣጠም ውስጥ ገባን፤ ቀን ከሌት የሚሰሩ ሠራተኞችና ወርክሾፖች አሉን፤ ይህንንም በአምስት ሺ ፕሮጀክት ላይ ተገበርን፤ በአንድ ቀን ብዙ በርና መስኮት መሥራትና መግጠም ቻልን›› ብለዋል፡፡

ከግብዓትና ከውጭ ምንዛሬ እጥረት ጋር በተያያዘ በፕሮጀክቶች ላይ የሚደርሰውን መጓተት ለመቀነስ ደግሞ እንደ አልሙኒየምም፣ እምነበረድ፣ ሴራሚክ የመሳሰሉትን ከውጭ ሀገር የሚመጡ የማጠናቀቂያ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ማምረት አለብኝ፤ ብሎ እየሰራ ነው፤ የጂብሰም ፋብሪካ ተክሏል፤ የማርብል ፋብሪካ እየገነባ ነው። በሲሚንቶ ኢንቨስትመንት ለመሰማራትም ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር እየሰራ ይገኛል፤ ለተገጣጣሚ ቤቶች አካላት ሥራ በራሱ ባለሙያዎች ሞልዶችን በማምረትና ከውጭ የሚመጣውን በማስቀረት በአንድ ቀን የአንድ ጂ+4 ህንጻ ተገጣጣሚ አካላት ማምረት ችሏል፡፡

ሥራዎቹን ዲጂታላይዝ ማድረግ አለብኝ ብሎም በመነሳት ለሥራው የሚያስፈልገውን ሶፍትዌር ከውጭ ከማስመጣት ይልቅ በራስ አቅም ማልማት ውስጥ ገባ። ይህንንም እውን አድርጎ ፕሮጀክቶቹን ከቢሮ ሆኖ መከታተል፣ ሀብትን በሚገባ ማስተዳደር የሚቻልበትን ሁኔታ ፈጠረ፡፡

‹‹በዚህም የነዳጅ ብክነትን በግማሽ ቀነስ፡፡ ከ2012 ጋር ሲነጻጸር በ2015 በጣም ብዙ ሚሊየን ብር መቆጠብ ቻለ፤ 12 ሚሊየን ሊትር ይጠቀም የነበረውን ነዳጅ ወደ 6 ሚሊየን አወረደ፡፡ የሥራ አፈጻጸሙም በአራትና አምስት እጅ አደገ›› ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰዋል፡፡

ይህን ሲጨርስ ደግሞ ሌላ ክፍተት ማየቱን ገለጸ፤ እንደ ሀገር የፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ቢኖርም፤ ኮርፖሬሽኑም የራሱ የማኔጅመንት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ያስፈልገኛል ብሎ ተነሳ፡፡ ለእዚህም የስልጠና ማዕከል ከፍቷል፡፡

በፕሮጀክቶች የሚደረግ ክትትል ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰዋል፡፡ እኛ የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክቶችን ብንሰራ እንመርጣለን ሲሉም ገልጸው፣ አዲስ አበባ ላይ ከንቲባዋ የጠቅላይ ሚኒስትሩን መንገድ ተከትለው ፕሮጀክት እየተከታተሉ ናቸው፤ የክልል መንግሥታትም ይህን ማድረግ ጀምረዋል፡፡ ሌሎች ተቋማትም ይህን ማድረግ አለባቸው ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከኢትዮጵያ ወጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ በማመንም ወደ ሥራ መግባቱን ጠቅሰዋል፡፡ ለእዚህና የተቋሙን የኢንዱስትሪ ሪፎርም ለመሥራት በጣም ብዙ የውጭ ምንዛሬ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ ሀገር ቅድሚያ የምትሰጠው ለሌላ ጉዳይ ነው›› ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ‹‹እኛ መሥራት እየቻልን ዶላር ሰርተን ማግኘት የሚያስችለን አቅም እያለን ለምን ዶላር እንጠይቃለን ብለን በአፍሪካ ጅቡቲ ላይ ቅርንጫፍ ከፍተናል፤ ከዚህ በምናገኘው ዶላር ኢንዱስትሪያችንን ማስፋፋት ጀምረናል፤ ለእዚህም ከመንግሥት የውጭ ምንዛሬ አልጠየቅንም፤ ላለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት ከመንግሥት ምንም የውጭ ምንዛሬ አልወሰድንም›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በጅቡቲ የጀመረውን ቅርንጫፍ የመክፈት ሥራ በኬንያ፣ በደቡብ ሱዳን፣ መቀጠል አለብኝ ብሎ እየሰራ ነው፤ ደቡብ አፍሪካና ሌሎችም ጥያቄ እያቀረቡለት መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ኮርፖሬሽኑ የውጭ ምንዛሬ የሚያገኝበትን መንገድ ለመጨመር መሥራቱን ቀጥሏል፤ በኦሞ ኩራዝ ፕሮጀክት እያካሄደ ያለውን የግብርና ሥራ ትራክተርና የመሳሰሉትን በመግዛት ባለሙያዎች ቀጥሮ በሌላ በ600 ሄክታር ማሳ ላይ ሩዝ እያለማ ይገኛል፤ ምርቱንም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ለውጭ ገበያ ወደሚሆን ምርት ለመቀየር እየሰራ ይገኛል፡፡

ለእነዚህ ሁሉ ስኬቶቹ የመጀመሪያው መሠረት የአመራሩና የሠራተኛው ቁርጠኝነት ነው ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ይጠቅሳሉ፤ በርካታ የተቋሙ ሠራተኞች በቁጭት ውስጥ ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ፤ አዳዲስ አመራሮችን ከውስጥም ከውጭም ማምጣቱ፣ የመንግሥት ቅንነት የተሞላበት ድጋፍ ሌሎች መሠረቶች ናቸው፡፡

ተቋሙ ይህን ሁሉ ውጤት አሳይቶም ‹‹እኛ ተሳክቶልናል ብለን አንናገርም፤ መስመር ውስጥ ገብተናል ነው የምንለው፡፡ ስኬት የሚባለውን ነገር ገና አልቀመስነውም›› ሲሉ ነው ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚናገሩት፡፡ ‹‹ስኬት የሚባለው እንደ ሀገርም እንደ ዓለምም እኛ ከውጭ ተቋም በተሻለ መፈጸም ከሚያስችለን እንዲሁም መንግሥት እና ሕዝብ ዛሬ የሚፈልጉትን ዛሬ መፈጸም ደረጃ ስንደርስ ስኬታማ ሆነናል እንላለን›› ብለዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ማህበራዊ ኃላፊነትን እየተወጣም ነው፡፡ ይህንን ሥራ ብሎ የጀመረው በተቋሙ ውስጥ ነው፡፡ ‹‹የኛ ሠራተኞች ደመወዝ ዝቅተኛ ነው፡፡ ሠራተኞቹን ለማነቃቃት ተቋሙ ምን ማድረግ አለበት፤ ከደመወዝ ውጭ ምን ልንደግፋቸው እንችላለን ብለን እንደ ማኔጅመንት ተወያይተናል›› ይላሉ፡፡ ‹‹ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሠራተኞቻችን መካከል አንዳንዶቹ ምሳ አይበሉም ነበር፤ ምሳ ይዞ የሚመጣውም ቢሆን ምግቡ ለመሥራትና ሰውነቱን ለመገንባት አቅም የሚፈጥርለት ዓይነት አልነበረም፡፡ ልጆቹን ሳያበላ ቢሮ ለማጽዳትና ለማስተካከል ሌሊት ቢሮ የሚገባ ነበር›› ሲሉ ያስታውሳሉ።

ይህን ሁኔታ በመቀየር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው 400 ሠራተኞች ላለፉት ሶስት ዓመታት ምሳ በነጻ እንዲመገቡ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ሠራተኛው ቢሮ ይዞ የሚመጣውን ምግብ ለልጁ መተው ይችላል፡፡ ከፈለጉም ምሳ በምሳ እቃ ስለሚሰጣቸው ይህንንም ወደ ቤታቸው መውሰድ ይችላሉ፡፡ ሌላው ሠራተኛም በካፍቴሪያ ትንሽ ከፍሎ የሚደገፍበት ሥርዓት ተፈጥሯል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ከዚያም ወደ አካባቢው ወጣ፡፡ ወደ ግቢው የሚወስደውን መንገድ አሳመረ፡፡ በአቅራቢያው ያለውን የወረዳ አስተዳደር ህንጻ አደሰ፤ የወረዳውን አመራር በጥራት ሽልማት ድርጅት እንዲሰለጥን አደረገ፤ በዚህም ጥራት ያለው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

ሌሎች በአካባቢው የሚገኙ የተቸገሩ ሰዎችን ማገዝ አለብን የሚል አቋም በመያዝ የምገባ ማዕከል አቋቁሟል፤ በዚህም አመራሩና ሠራተኛው ገንዘብ እያዋጣ በየቀኑ ወደ ሁለት መቶ አካባቢ የሚሆኑ ችግረኞች ምገባ እየተካሄደ፣ ቡና እንዲጠጡ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በፕሮጀክቶቹ አካባቢዎችም እንዲሁ ለማህበረሰቡ መሠረተ ልማቶችን ይገነባል፡፡ በቅርቡ መገጭ ግድብ አካባቢ ከሃያ ሚሊዮን ብር በላይ በማውጣት ከ20 ኪሎ ሜትር በላይ መንገድ ሰርቶ የሕብረተሰቡን የመንገድ ጥያቄ መልሷል ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰዋል። ላለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ተመሳሳይ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት ሕዝብን ተጠቃሚ አድርጓል ብለዋል፡፡

ሁሉም የማህበራዊ ኃላፊነት ሥራ በእቅድ እንደሚመራም አመልክተው፣ ከገቢያችን ከትርፋችን የተወሰነውን መቶኛ ለእዚህ አላማ በመመደብ ብዙ የተቸገሩ ሰዎችን ቤቶች ሰርተናል፤ የከተማ አስተዳደሮችና ክልሎችን ደግፈናል ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚያስተዳድረውን የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከል ብዙ ሚሊየን ብር በማውጣት በነጻ ሙሉ ጥገና ማድረጉንና አንዳንድ ግንባታዎችን ማካሄዱን፣ የፌዴራል ፖሊስ የጀግኖች ማዕከል ግንባታንም እንዲሁ ሙሉ ወጪ ሸፍኖ መገንባቱን ጠቅሰዋል፡፡

ተቋሙ አቅሙን እያሳደገ አስፈላጊ በሆኑት አካባቢዎች ላይ አተኩሮ መሥራት ይፈልጋል፤ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች በሚገቡበት ላይ እያተኮረ፣ ከኢትዮጵያ ውጭ መሥራት አለብኝ ብሎ እየሰራ ይገኛል፡፡ አብዛኞቹ ሥራዎቹ ከኢትዮጵያ ውጭ መሆን አለባቸው የሚል አቋምም አለው፡፡ በአብዛኛው በኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማምረት ሥራ መሳተፉን ጀማምሮታል፡፡

‹‹በጥራት፣ በዋጋ መወዳደር፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዋጋ ማረጋጋት የሚችል ተቋም ለመገንባት ትልቅ ሥራ እንሰራለን›› ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ይገልጻሉ፡፡ ይሄን ተቋም አፍሪካዊ ማድረግ መቻሉን፤ ቀጥሎ ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ለማድረግ እንደሚሰራም ተናግረዋል፡፡ ደረጃችን ወርቅም ይሁን መዳብ አፍሪካ ላይ ተቋማችንን ለማሳየት ያደረግነው ሙከራ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ይላሉ፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን የተሰጠንን እድል ተጠቅመን ከሠራን ከዚህም በላይ መሥራት እንችላለን፡፡ ብዙ መሥራት የሚችል አእምሮ ያላቸው ባለሙያዎች፣ ይህን ማስፈጸም የሚችሉ አመራሮች እየተፈጠሩ ናቸው፤ መንግሥታችን በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ያለው እይታ እና እየተፈጠረ ያለው ንቅናቄ ቀላል አይደለም፤ ይህን ሁሉ ምቹ ሁኔታ ልንጠቀምበት ይገባል›› ሲሉም ያስረዳሉ፡፡

# ማህደረ ጤና

# ትኩረት ያልተሰጠው የጋማ እንስሳት ጤና

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ የጋማ እንስሳትና ህብረተሰቡ በልዩ ልዩ መልኩ ጥብቅ ቁርኝት አላቸው፡፡ በተለይ ለገጠሩ የህብረተሰብ ክፍል የጋማ እንስሳት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዋጽኦዋቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል። የገጠሩ ማህበረሰብ በጋማ እንስሳት ከማሳ እህል ጭኖ ወደ አውድማ ያመጣባቸዋል፡፡ እህል ይወቃባቸዋል። የወቃውን እህል ደግሞ ጭኖባቸው ጎተራ ይሞላል፡፡ በእነዚህ እንስሳት የኢትዮጵያ ገበሬ እህሉን ጭኖና ወደ ከተሞች አጓጉዞ ይሸጣል። በሸጠው እህል ሌላ ሸቀጥ ገዝቶ ጭኖባቸው ዳግም ወደ አካባቢው ይመለሳል፡፡ ይህም የጋማ እንስሳት ለገጠሩ ማህበረሰብ በተለይ ደግሞ ለገበሬው ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሩቅ ሰው ለቅሶ የሚደርሰው በፈረስና በአህያ ተጉዞ ነው፡፡ ሰርግም እንደዛው። ዘመድም ሆነ የታመመ ሰው የሚጠያየቀው በጋማ እንስሳት በመጓዝ ነው፡፡ ይህም የጋማ እንስሳት ጭነት በማጓጓዝ ለገጠሩ ማህበረሰብ ከሚኖራቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ለሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠትና ማህበራዊ ኑሮዋቸውን በማሳለጥ ረገድ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ ይጠቁማል፡፡

የገጠሩ ተነሳ እንጂ በከተሞችም አካባቢ ቢሆን ውሃ በጀሪካን፣ ሸቀጣ ሸቀጦችን፣ አሸዋ፣ ጠጠርና ሲሚንቶ ሳይቀር በጀርባቸው ተሸክመው በማጓጓዝ የሰዎችን ኑሮ የሚደጉሙ በርካታ አህዮች አሉ፡፡ የዛኑ ያህል ደግሞ ጋሪ እየጎተቱ ከቦታ ቦታ ሰዎችን በማመላለስ የትራንስፖርት ድጋፍ የሚሰጡና የባለጋሪዎችን ኑሮ የሚደጉሙ ፈረሶች በርካቶች ናቸው፡፡

በቀደመው የኢትዮጵያ ታሪክም ቢሆን የጋማ እንስሳት ከነዚሁ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦዋቸው ባሻገር ሀገሪቷ በገጠሟት የውጭ ወረራዎች ወቅት ትጥቅና ስንቅ በማጓጓዝ ብሎም በጦር ግንባሮች ጀግኖች አርበኞችን ጭነው ከፊት ሆነው እንዲፋለሙ በማድረግ ትልቅ ታሪካዊና ሀገራዊ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ የእነሱን አስተዋጽኦ ልብ በማለትም ጀግኖች አርበኞች በፈረስ ስሞቻቸው እስከመጠራት ደርሰዋል፡፡

እንግዲህ የጋማ እንስሳት በኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ትልቅ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ አሁን ባለው መረጃም በኢትዮጵያ 13 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚጠጉ የጋማ እንስሳት እንዳሉ ይነገራል፡፡ ይሁንና የአበርክቷቸውን ያህል ለደህንነታቸውና ለጤናቸው የሚደረገው ጥበቃና እንክብካቤ ዝቅተኛ ነው፡፡ በህብረተሰቡ በኩል ለጋማ እንስሳት ያለው አመለካከትም እጅግ ደካማና ኋላ ቀር ነው፡፡

በጋማ እንስሳት ጤናና ደህንነት አጠባበቅ ዙሪያ የሚሰራው ሥራ እጅግ ደካማና ከናካቴውም የለም በሚባል ደረጃ የሚገለፅ ቢሆንም ችግሩን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ጥናት አልያም ደግሞ የተጠናቀረ የቁጥር መረጃ የለም፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ረገድ የተሰራ ጥናትና የተጠናቀረ የቁጥር መረጃ ባይኖርም ቢያንስ ሀገሪቱ በጋማ እንስሳት ደህንነትና ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ፖሊሲ የሌላት መሆኑ ብቻ በዚህ ዘርፍ የሚሰራው ሥራ ችላ የተባለ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ትኩረት ተደርጎበት እየተሰራ እንዳልሆነም ያሳያል፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን የእነዚህ እንስሳት ደህንነትና ጤና የሚያሳስበው አንድ ምግባረ ሰናይ ድርጅት ይበል የሚያሰኝ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ እያከናወነ ይገኛል፡፡ አቶ ዮሐንስ ቃሲም «ብሩክ ኢትዮጵያ» የተሰኘውና በጋማ እንስሳት ደህንነትና ጤና ጉዳዮች ላይ የሚሰራው ድርጅት ካንትሪ ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው እንደሚናገሩት ድርጅቱ ዶሮቲ ብሩክ በተሰኘች እንግሊዛዊት በቀደመው ጊዜ በነበረ ጦርነት የእንግሊዝ ወታደሮች ግብፅ፣ ካይሮ ውስጥ ጥለዋቸው የሄዱና የተጎሳቆሉ 20ሺህ የሚጠጉ ፈረሶችን ለመርዳት ታላሚ በማድረግ «The Brooke Hospital for Animals in Cairo» በሚል ስያሜ እ.ኤ.አ በ1934 የተመሰረተ ነው፡፡ በሂደት ድርጅቱ በተለያዩ ሀገራት ሥራውን አስፍቷል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአስራ አንድ ሀገራት ላይ ይሰራል፡፡ በእስያ፣ በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና በሰሜን አሜሪካ ከጋማ እንስሳት ደህንነትና ጤና ጥበቃ ጋር በተያያዘ ሥራዎችን ያከናውናል።



«በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ በየመንገዱ ቆሳስለው የቆሙ ፈረሶችን ማየት የተለመደ ነው፡፡ እነዚህ ፈረሶች ሊድን በማይችልና/episodic fangaits/ በተሰኘ በሽታ የተጠቁ ናቸው። ቀድሞ መከላከል ቢቻል እዚህ ደረጃ ላይ ሳይደርስ መከላከል ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን ለነዚህ የጋማ እንስሳት ጤና የሚሰጠው ትኩረት በእጅጉ ያነሰ በመሆኑ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ፈረሶች ለረጅም ጊዜ የጋሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ለእንዲህ ዓይነቱ በሽታ ከመጋለጣቸው በፊት አስፈላጊው ሕክምና አገልግሎት ስለማያገኙ እጣ ፈንታቸው አስፓልት ላይ በቁማቸው መሞት ነው፡፡»

በኢትዮጵያም «Brooke Ethiopia» በሚል ስያሜ በ2006 ዓ.ም ተመስርቶ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። በአሁኑ ጊዜም በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች (በቀድሞው አጠራር) ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

"ብሩክ ኢትዮጵያ" በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በማተኮር በጋማ እንስሳት ደህንነት ጥበቃ ዙሪያ ይሰራል። አንደኛው የእንስሳት ደህንነት፣ ጥበቃና አያያዙ ዙሪያ ለማህረሰቡ አጠቃላይ ግንዛቤ መስጠት ነው። በማህበረሰቡ በኩል የጋማ እንስሳት አያያዝ ችግሮች ይታያሉ፡፡ ይህን ለማስተካከል የእንስሳቱን ደህንነትና ጤና እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ድርጅቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሰራል፡፡

ሁለተኛው የጋማ እንስሳት ባለቤቶች የገቢ አቅማቸውን እንዲያሳድጉና ከሚያገኙት ገቢ ተጠቅመው የጋማ እንስሳቱን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ ድርጅቱ ይሰራል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ አጠቃላይ የጋማ እንስሳት የጤና ሥርዓቱን ለማሻሻል ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ ለዚህም የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን አቅም በስልጠና ያጎለብታል፡፡ ይህም በተለይ በገጠር አካባቢ ያሉ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን ያካትታል፡፡ ለእነዚህ ባለሙያዎች ተከታታይ የሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ያደርጋል፡፡

ከወሎ፣ ጅማ እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን በዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ የሚገኙ የእንስሳት ሕክምና ተማሪዎች ተገቢው የክሂሎትና አቅም ኖሯቸው ትምህርታቸውን አጠናቀው እንዲመረቁ ጥራቱን የጠበቀ ሕክምና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ስልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የእንስሳት ጤና አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተደራሽነቱ ደካማ እንደመሆኑ ተደራሽነቱን ለማሻሻል የእንስሳት ጤና ኬላዎችን ድርጅቱ ይገነባል፡፡ ከገነባ በኋላም ለጤና ኬላዎቹ የሚያስፈልጉትን የሕክምና ግብዓቶች በማሟላት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል። በተመሳሳይ የጋማ እንስሳት መድኃኒት አቅርቦት ችግር ያለ በመሆኑ ችግሩን ለማሻሻል በስልጠና፣ በገንዘብ፣ በማማከርና በመሳሰሉት፤ በተለይ በተዘዋዋሪ መድኃኒት አቅርቦት ፈንድ የእንስሳት መድኃኒት በዘላቂነት እንዲቀርብ የማድረግ ሥራዎችን ይሰራል፡፡ በዚሁ አሰራር መሠረት ለጋማ እንስሳት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ በመድኃኒቶች በዘላቂነት እንዲቀርቡ ከማድረግ አኳያ ድርጅቱ እየሰራ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የጋማ እንስሳትን ጤንነት ይበልጥ ለመጠበቅ ድርጅቱ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የውሃ ተቋማትን ይገነባል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ለሰዎችም የንፁህ ውሃ ተቋማትን ገንብቶ ያስረክባል፡፡ ሌሎች የጋማ እንስሳት ደህንነትና ጤናን ሊያረጋግጡና ሊያስጠብቁ የሚችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ በየመንገዱ ቆሳስለው የቆሙ ፈረሶችን ማየት የተለመደ ነው፡፡ እነዚህ ፈረሶች ሊድን በማይችልና /episodic fangaits/ በተሰኘ በሽታ የተጠቁ ናቸው፡፡ ቀድሞ መከላከል ቢቻል እዚህ ደረጃ ላይ ሳይደርስ መከላከል ይቻል ነበር። ነገር ግን ለነዚህ የጋማ እንስሳት ጤና የሚሰጠው ትኩረት በእጅጉ ያነሰ በመሆኑ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ፈረሶች ለረጅም ጊዜ የጋሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ለእንዲህ ዓይነቱ በሽታ ከመጋለጣቸው በፊት አስፈላጊው ሕክምና አገልግሎት ስለማያገኙ እጣ ፈንታቸው አስፓልት ላይ በቁማቸው መሞት ነው፡፡

እነዚህ ፈረሶች የገጠማቸውን በሽታ ህመም በመቀነስ የማስወገድ ሥራ ብሩክ ኢትዮጵያ ይሰራል። ይህንንም የሚያደርገው ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ለመከላከልና የፈረሶቹን ስቃይ ለመቀነስ ነው፡፡ ከከተማ ፅዳትና ውበት አኳያም የቆሳሰሉ ፈረሶችን ማየት ተገቢ ባለመሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚመለከታቸው የመንግሥት አጋር አካላት ጋር ድርጅቱ በትብብር እየሰራ ይገኛል፡፡

እነዚህንና መሰል ሥራዎች ብሩክ ኢትዮጵያ እየሰራ የሚገኝ ቢሆንም በዋናነት በጋማ እንስሳት ደህንነት፣ አያያዝና ጤና ዙሪያ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ የውትወታ ሥራ ይሰራል። እንስሳትን የተመለከቱ አዋጆች፣ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ሲወጡ የጋማ እንስሳትን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ሥራዎችን ይሰራል፡፡

በብሩክ ኢትዮጵያ የፐርፎርማንስና ካፓሲቲ ዴቨሎፕመንት ሲኒየር ማናጀር ዶክተር ቴዎድሮስ ተስፋዬ በበኩላቸው እንደሚሉት በጋማ ከብቶች አጠቃቀምና አያያዝ ዙሪያ የሚያስፈልጉ ፖሊሲዎች ኢትዮጵያ ቢኖራት ኖሮ በዘርፉ የሚታየውን ችግር በሚገባ መቅረፍ ይቻላል። ይሁንና ሀገሪቷ በዚህ ዙሪያ የተዘጋጀ ፖሊሲ የላትም፡፡ ድርጅቱ በሶስት ክልሎች ውስጥ በሚገኙ አስራ አምስት ወረዳዎች ላይ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ሥራዎቹ ፕሮጀክት ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በዚህም ሥራው በጊዜና በሀብት የተወሰነ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ የተጎዱ የጋማ እንስሳት በተለይ ደግሞ ፈረሶች አሉ፡፡ ይህም ድርጅቱ ተደራሽ ሆኖ ከሚሰራበት አካባቢ ውጭ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን ድርጅቱ በሁለት ዓይነት መንገድ የጋማ እንስሳት ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ ይሰራል፡፡ አንደኛው የእንስሳት ጤና አገልግሎቱን ማሻሻል ሲሆን የጋማ እንስሳትን ያካተተ ሆኖ ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው በተለይ በመንግሥት የእንስሳት ጤና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች ተከታታይ የሆነ ስልጠናና ድጋፍ በመስጠት በክሂሎታቸው የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡ ይህም ለጋማ እንስሳት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የቤት እንስሳቶች የጤና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለእነዚህ የጋማ እንስሳት አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒትን ጨምሮ ሌሎች የሕክምና ግብዓት እጥረት ችግሮች ይታያሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ድርጅቱ በመድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ አማካኝነት በክልል ያሉ ክሊኒኮች የመድኃኒት አቅርቦት እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል። በተመሳሳይ መሠረታዊ የእንስሳት መድኃኒቶች ለኢትዮጵያ እንስሳት ጤና አገልግሎት ከሌሎች አጋር አካላት፣ ማለትም ከግብርና ሚኒስቴር፣ የግብርና ባለስልጣንና ከኢትዮጵያ እንስሳት ሐኪሞች ማህበር ጋር በመሆን የእንስሳት መሠረታዊ መድኃኒቶች ዝርዝር ተዘጋጅቷል፡፡

ይህም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፤ ከተለያዩ ልምድና እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በመሆን የተዘጋጀ ብሔራዊ ሰነድ ነው፡፡ ከዚህ በኋላም እነዚህን መድኃኒቶች ለኢትዮጵያ ሊኖራቸው የሚችለውን ገቢ የማምጣትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥራ ይጠበቃል፡፡ ይህም በብሩክ ኢትዮጵያ በእንስሳት ጤና ዘርፍ የሚያከናውነው ሥራ ሆኖ ማህበረሰቡ በጋማ እንስሳት ዙሪያ ያሉበትን የግንዛቤና የአያያዝ ክፍተቶች ለመሙላት በሁለት ዓይነት መንገድ፣ በተለይ በገጠራማውና በከተማው የሀገሪቱ ክፍሎች ይሰራል፡፡

አንደኛው በአዲስ አበባ ከተማ በቅርቡ ይፋ የሚያደርገው ተንቀሳቃሽ የጋማ እንስሳት ሕክምና አገልግሎት ነው፡፡ ይህ አገልግሎት የሚሰጠው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ግብርና ቢሮና ከኤልም ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ነው። በዚህም በከተማዋ ውስጥ በሥራ ላይ የሚገኙ ፈረሶች የማከም ሥራ ይሰራል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ታመው መዳን የማይችሉ ፈረሶችን ህመም ሳይሰማቸው በርህራሄ /Euthanasia/ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

ሀገሪቱ ወደ ሌላ ዓይነት ቴክኖሎጂ እስካልተሸጋገረች ድረስ የጋማ እንስሳት ከሚሰጡት አገልግሎት ውጭ መሆን አይቻልም፡፡ ይህም ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ ታዳጊ ሀገራት ላይ የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ህብረተሰቡ የሚመገበው ምግብ በእነዚህ የጋማ እንስሳት ተጭኖ የሚመጣውን ነው፡፡ አይደለም የገጠሩ ማህበረሰብ በከተማም የሚኖረው የእነዚህ እንስሳት አስተዋጽኦ ተጠቃሚ ነው፡፡ ይሁንና እንስሳቱ ይህን ያህል ጥቅም እየሰጡ ቢሆንም ደህንነታቸውና ጤናቸው በበቂ ሁኔታ እየተጠበቀ ባለመሆኑ የሁሉንም ትኩረት ይሻሉ፡፡

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)

gechoseni@gmail.com

**የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።**

# የነገይቱ ኢትዮጵያ መልክ

**"ከዛሬ ጋር ሙግት!?"፤**

ከዛሬ ይልቅ ስለ ነገ ማሰብ የሰው ልጆች ሁሉ ባህርይ መሆኑን የበርካታ የጥናት መስክ ምሁራን እውነታውን ያረጋግጡልናል። ለእኛ ለኢትዮጵያ ልጆችም እንዲሁ፡፡ ትናንት ለየትኛውም የአዳምና የሄዋን ዘር የትዝታ፣ የቁጭትና የነበር ወግ ማህደር ነው፡፡ "ትናንትን እንዴት ነበርክ?" በማለት ከታሪኩ ለመማርና ለመተራረም ተፈልጎ ካልሆነ በስተቀር "እንዴት ነህ?" ወይንም "እንዴት ትሆን ይሆን?" በማለት በዛሬና በነገ ወንጠፍት ለመፈተሽ እንሞክር ብንል ከኃላፊ ዘመን ጋር ለመኳረፍ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ፋይዳ አይኖረውም፡፡

"ጊዜ በረርክ በረርክ፣
ጊዜ በረርክ በረርክ፣
ግና ምን አተረፍክ፣
ግና ምን አጎደልክ?
ሞትን አላሸነፍክ፣
ሕይወትን አልገደልክ፡፡"

ብለን ብንፎትተውም ሆነ ብንገረምበት አለያም ብንፈላሰፍበት ምንም ጠብ የሚያደርግለን ነገር ስለሌ ድካማችን ከጉንጭ አልፋነት አያልፍም።

ነፍሰ ሄሩ የሀገራችን ብዕረኛ ከበደ ሚካኤል "አዝማሪና የውሃ ሙላት" በሚለው ዘመን ተሻጋሪ ግጥማቸው ስለ አንድ ማሲንቆ ገዝጋዥ አዝማሪ ድንቅ ቅኔ ተቀኝተዋል። የዋሁ አዝማሪ ከአፍ እስከ ገደፉ የሞላ ፈረሰኛ ወንዝ ራርቶለት ጎድሎ እንዲያሻግረው ለመለማመጥ ዳር ላይ ቆሞ አንጀት በሚያራራ ዜማ ወንዙን ሲያሞጋግሰው ያስተዋለ አንድ መንገደኛ ምስኪኑን መሲንቆኛ የመከረው እንዲህ በማለት ነበር፡፡

"እስኪ ተመለከተው ይህ አወራረድ፣
ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ፤
ድምጡን እያውካካ መገስገሱን ትቶ፣
ማን ይሰማኝ ብለህ ትደከማለህ ከቶ፡፡"

ገጣሚው "ልብ ያለው ልብ ይበል" ብለው ሊመክሩን የፈለጉት "ጊዜንም" በአግባቡ ተጠቅመን ለውጤትና ለፍሬ ካላስገበርነው በስተቀር የነበር ወግ እያላመጥን ወይንም የነገን እለት እየጎመጀን ብቻ "ወይ ጊዜ! አይ ጊዜ!" እያልን በአራራይ ዜማ ብናሞጋግሰውም ሆነ በትዝታ ቅኝት ብናደናንቀው አለያም ብናማርረው ትርጉም አይኖረውም፡፡ ይልቅስ ጊዜን በጊዜ አሸንፈን ካልረታነው በስተቀር በጊዜያት ውስጥ ያከማቸነውን በጎ ትሩፋቶች ሁሉ አስረግፎንና ባዶ እጃችንን አስቀርቶ "ምርኮኛ" በማድረግ ለነገ ፍርድ እንዳያሺጋግረን አጥብቆ ማሰቡ ብልህነት ነው፡፡

"የግድግዳ ሰዓቴ የሴኮንድ ቆጣሪ ያለ እረፍት ቲክ! ቲክ! እያለ የመዳዙን ድምጽ የሚያሰማኝ ዛሬህ በከንቱ እንዳያመልጥህ እኩል በመራመድ በእጁ የያዘውን ዕንቁ አስጥለው እያለ ሊመክረኝ ፈልጎ ይመስለኛል።" እንዳለው ጠቢብ፤ ገስጋሹን ጊዜ በአግባቡ ጨምቀን አምቆ የታቀፈውን "ጣዝማ ማር" ከእጁ ካላስጣልነው በስተቀር (ጣዝማ ማር አንድም ለጥፍጥና አንድም ለመድኃኒትነት መዋሉን ልብ ይሏል) እኛን ወደ ኋላ እያስቀረ የያዘውን ሀብት ይዞ እንደ ወንዙ አወራረድ እያውካካና እየሳቀብን መገስገሱን አያቆምም፡፡ ሀገራዊ ብሂላችንስ ቢሆን፡ - "ጊዜ ወርቅ ነው፤ ግና ኃላፊም ነው፡፡" በማለት የሚያስተምረን ስለዚሁም አይደል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን "ጊዜ በረርክ በረርክ" ስንኞች ያዋቀረው ብዕረኛው ደበበ ሰይፉ በሌላ ግጥሙ ጊዜን በአግባቡ ተጠቅመን እንዴት ፍሬ እንደምናዘምርበት በ1967 ዓ.ም በጻፈውና "የምኞት ሱስ ለሌለባቸው ለሀገር ልማትና ዕድገት የትም መቼም ቀና ደፋ ለሚሉ" በሚል የግርጌ ማስታወሻ አስደግፎ "በትን ያሻራህን ዘር" በሚለው ግጥሙ የመከረን እንዲህ በማለት ነው፡፡

"በጓጥ በስርጓጉጡ፤ በማጥ በድጡ፤
እንደ ተንጋለልክ እንደ ዘመምክ፣
ትንፋሽህን እንደቋጠርክ፣
ልል ቀበቶህን እንዳጠበክ፣
የተልዕኮህን አባዜ፣
የሕይወትህን ቃለ-ኑዛዜ፣
ወርውር!
የእጅህን ዘገር፡፡
በትን! ያሻራህን ዘር፡፡
ይዘኸው እንዳትቀበር፡፡

ጊዜን ማሸነፍ የሚቻለው በሥራና በውጤት ብቻ እንጂ "ሀሳብ ሹሩሩ" በማለት ከንጋት እስከ ፀሐይ ግባት ብናንጎራጉሩ ትርፋችን ምንም፤ ድካማችንም ከንቱ መሆኑን ልብ ማለቱን ከቶውንም ልንዘነጋው አይገባም። ከሰማይ በታች ለሚከናወን ለማንኛውም ነገር ጊዜ አለው" እንዳለው የቅዱስ መጽሐፉ ጠቢብ፤ ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ከማዋል ይልቅ "እንደ ኦሪታዊው ኢያሱ ፀሐይን ካላቆምን ብለን ግብ ግብ ብንፈጥር" የጊዜን መብረር ለአፍታም ቢሆን ልንገታ ስለማንችል ጠቡ ከራስ ጋር፤ ኩሪፊያውም ከማንነት ጋር ይሆን ካልሆነ በስተቀር አንዳች ጠብ የሚል ፋይዳ አይኖረውም፡፡

**"የአራት ሴናሪዮዎች" ግምገማ፤**

ከሦስት ዓመታት በፊት ዴስቲኒ ኢትዮጵያ በተባለ ሀገር በቀል ተቋም አማካይነት ከመላው ሀገሪቱ የተውጣጡ 50 ያህል በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፖለቲከኞች፣ መሪዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎችና በጎ ፈጣሪ እንደሆኑ የታመነባቸው ግለሰቦች ለሦስት ያህል ጊዜያት ተገናኝተው የነገይቱ ተናፋቂ ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ምን ሆኖ ለማየት እንደሚጓጉ የጋራ አግባቢ ሃሳብ ላይ ደርሰው ነበር፡፡

በተከታታይ መርሃ ግብሮችም በኢትዮጵያ የሃይማኖት ጉባዔና በሰላም ሚኒስቴር ጥምረት ከሀገሪቱ ቤተ እምነቶች የተውጣጡ መምህራንና ምሁራን ቀደሚዎቹ 50 ተሳታፊያን በነደፏቸው አራት ሴናሪዮዎች ላይ ጥልቅ ውይይቶችን በማድረግ የነገይቱን ኢትዮጵያ መልክና ውበት ላይ ምክክሮች አድርገው ነበር፡፡ የዚህን ምክክር ክራሞት በተመለከተ ይህ ጸሐፊ ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በዚሁ ገጽ ላይ ምልከታውን በዝርዝር ማጋራቱ አይዘነጋም፡፡

በተወያዮቹ የቀረቡት ሴናሪዮዎች በቁጥር አራት ሲሆኑ ኢትዮጵያን በ2032 ዓ.ም ሊገጥሟት ይችላሉ ብለው የገመቷቸው አማራጮች የተንጸባረቁባቸው ነበሩ። የመጀመሪያው በሠባራ ወንበር (Broken Cahir) የተወከለ ሴናሪዮ ሲሆን ዋነኛ ይዘቱም የሀገሪቱ ዜጎች በመነጋገር፣ በመመካከርና በመግባባት ችግሮችን እየፈቱ ካልሄዱ በስተቀር ሊያጋጥም የሚችለው የሥርዓት አደጋ የከፋ ሊሆን ይችላል የሚል መደምደሚያ የተደረሰበት ነበር፡፡

የዚህ አደጋ ምክንያቱ ደግሞ በሰነዱ ውስጥ የተገለጸው እንዲህ ተብሎ ነበር። "በሰባራ ወንበር ሴናሪዮ ጠንካራ በሚመስል፣ ነገር ግን ገና ሲነኩት እንደሚሽመደመድ፣ ቀላል ክብደትን እንኳን የማይሸከም ወንበር የተመሰለ ነው፡፡ የአቅም ማጣቱ በማሕበረሰቡ ውስጥ በየደረጃው ለሚነሱ የልማት ፍላጎቶች ተግባራዊ ድጋፍ ለመስጠት እንዳይቻል ያደርጋል...፡፡" ይላል፡፡

ሁለተኛው ሴናሪዮ የተወከለው አፄ በጉልበቱ (Hegemony) በሚል ስያሜ ሲሆን ሴናሪዮው የተብራራውም፤ "ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የኢኮኖሚውን አካሄድ፣ የአካባቢ መጎሳቆልንና የሕዝብ እድገት ጫናዎችን ለመመከት ቁጥጥር ተኮር ሥርዓትን መከተል ወሳኝ መሆኑን ያምናል...።" በሚል ትንተና ነበር፡፡

ሦስተኛው ሴናሪዮ የፉክክር ቤት (Divided House) የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ በሰነዱ ውስጥ የተብራራውም እንደሚከተለው ነበር። "የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል እንደሚባለው የተለያዩ ቡድኖች እና ክልሎች ያገኙትን አዲስ ነፃነት እነርሱ እንደፈለጉትና እንደመሰላቸው መጠቀማቸውን የሚያሳይ ሲሆን ከመንግሥት አንስቶ እስከ ቤተሰብ ደረጃ በሁሉም የማሕበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚስተዋሉ ክፍተቶችንና ክፍፍሎችን የሚያሳይ ነው..." የሚል ነበር፡፡

አራተኛው ሴናሪዮ ንጋት (Dawn) በሚል ስያሜ የተለየ ሲሆን ማብራሪያውም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡ "የንጋት ሴናሪዮ የኢትዮጵያ እድገት ደረጃ በደረጃ ዕውን የሚሆንበትን ተስፋ ያዘለ ነው፡፡ የሙሉ ቀን ብርሃን አልሆነም፡፡ ነገር ግን የአዲሱ ቀን ወገግታ ጀምሯል፡፡ ኢትዮጵያዊያን ሕጋዊና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን እና የዕርቅ ሂደቶችን አጠናክረው በመተባበር የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውን እያስቀጠሉ ነው፡፡

በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ሥር የሰደዱ ማሕበራዊ ቅራኔዎች በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች እልባት ማግኘት ጀምረዋል። ከቅራኔና ከጥላቻ ይልቅ የይቅርታና እርቅ አስተሳሰቦች በማሕበረሰቡ ዘንድ እንዲሁም በመደበኛ እና ማሕበራዊ መገናኛዎች በየዕለቱ ተቀባይነታቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡ የዴሞክራሲ ተቋማትና ኢኮኖሚው ደረጃ በደረጃ እየተገነቡ፣ በጋራ ርእይ ላይ የተመሠረተ አንድነት በመፍጠር ላይ ይገኛል።" የሚል ነበር፡፡ በማጠቃለያው ላይም "ኢትዮጵያ ውስብስብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ተግዳሮቶች ከፊቷ ተደቅነዋል፡፡ ምላሾቻችን ምን ይሆናሉ?" የሚል ጥያቄ ለተሳታፊያኑ ተሰንዝሮ ነበር፡፡

ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም የመጀመሪያውን ምክክር ያከናወኑ የቤተ እምነት መሪዎችና ምሁራን እንደገና ተሰባስበው የሦስቱን ዓመት ጉዞ ለመገምገም ዕድል አግኝተው ነበር፡፡ በዚሁ የምክክር መርሃ ግብር ላይ በርካታ ሃሳቦች የተንሸራሸሩ ሲሆን፣ በአጠቃላይ የተደረሰበት የጋራ መግባቢያ ድምዳሜ ዛሬም ኢትዮጵያ ወደምንመኘው ንጋት እንዳትቃረብ በበርካታ ተግዳሮቶች መከበቧን የሚጠቁሙ ነበሩ፡፡

ኢትዮጵያ በቀዳሚዎቹ ሥርዓተ መንግሥታት ያልተፈተነችባቸው ችግሮች ነበሩ ለማለት ያዳግታል። ችግሮቹም ብዙ ሀገራዊ ቀውስ አስተናግደው አልፈዋል። አንዳንዶችም "በደረታቸው እየተሳቡ" በመምጣት ዛሬም ድረስ ብሔራዊ ፈተናዎቻችን በመሆን እየተገዳደሩን ይገኛሉ፡፡

የብሔራዊ ችግሮቻችን መልኮችም ሆኑ ቅርጾች የተለያዩ ቢሆኑም "በንጋት" የሚመሰለውን የነገ ተስፋችንን ያዘገዩ ካልሆነ በስተቀር የውጋጋኑን በረከትና ትሩፋት ግን ማየታችን የሚቀር አይደልም። የከበቡን ተግዳሮቶች የበዙ ቢመስልም በንግግርና በምክክር፣ በውይይትና በስክነት፣ በመደማመጥና ተቀራርቦ በመተያየት የማይፈታ ምንም ችግር ሊኖር እንደማይችል ዜጎች በሙሉ ከልብ ልንቀበለው እንደሚገባ ወቅቱ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጉጉት እየጠበቀን ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያን ንጋት የሚያደበዝዙ፣ ተስፋዋንም የሚፈታተኑ እጅግ በርካታ የፈተና ጋሬጣዎች ከውስጥም ሆነ ከውጭ ከፊታችን ቢጋረጡም ዜጎች በአንድ ልብና ሃሳብ ምህዋር ውስጥ የሚሰለፉ ከሆነ የነገይቱ ሀገራችን ተውባና ደምቃ በዓለም ፊት እንደምትታይ ጅምር ሀገራዊ ትሩፋቶቿ ምስክሮች ናቸው፡፡

በተለየ ሁኔታና በተደራጀ ዝግጅት ተልዕኮውን ለማካሄድ እየተንቀሳቀሰ ያለው የምክክር ኮሚሽን በሙሉ ኃይሉ ሥራውን ጀምሮ ሲፈጽም የምንመኘው የነጋችን የንጋት ተስፋ እውን እንደሚሆን መጠራጠር አይቻልም፡፡ ስለዚህም የነገይቱ ኢትዮጵያ መልክ ዛሬ እንደሚስተዋለው በጥልፍልፍ ፈተናዎች ወይቦ ብቻ አይቀርም፡፡

የተስፋዋ ወጋጋን ደምቆ የሚወጣበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ ዜጎቿም ከቁዘማ ወጥተው በደስታ ዜማ አድማሳችን መድመቁ አይቀርም፡፡ ይህቺን ኢትዮጵያ ነው ነገ ማየት የምንፈልገው፡፡ ዛሬንና ነገን ከማስዋብ ይልቅ በትናንት ቁጭት መብከንከኑ ወይንም "ለምን ሊሆን አልቻለም ነበር" በማለት ከታሪክ ጋር ግብግብ ለመፍጠር እልህ መያያዙ እጅግም ለዛሬያችን መፍትሔ ስለማይሆን የሚበጀው የነገ ተስፋችን ንጋት ደምቆ እንዲፈካ፣ ገጣሚው እንደመከረን፤ የእጃችንን መልካም ዘር በመዝራት የድርሻን መወጣት ብቻ ነው፡፡ ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ፡፡

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆእስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ያልጠለቀች ጀንበር…

መልካምሥራ አፈወርቅ

ዕትብቷ የተቀበረው ከአባ ጅፋር ሀገር ከጅማ ምድር ነው፡፡ ተወልዳ ባደገችበት ከተማ ተምራ፣ ትዳር ይዛ ወግ ማዕረግ ማየት አልታደለችም። ድንገት ከቤተሰብ ጋር የተነሳ ግጭት ሰላሟን ነሳት፡፡ ይህ እውነት ለቀጣይ ሕይወቷ ዕንቅፋት መስሎ ቢታያት ቆም ብላ አሰበች፡፡

የሃሳቧ ዳር በዝምታ አልተቋጨም፡፡ ከ‹‹ነገሩ ጦም እደሩ››ን መረጠች፡፡ ውስጧ ርቆ መሄድን ቢያልም ሩቁን መንገድ አሳያት፡፡ ውላ ማደር አልፈለገችም፡፡ ጓዟን ሸክፋ ተነሳች፡፡ ዘመዶቿን ትታ ጅማን ተሰናብታ አዲስ አበባ ገባች፡፡

ዘቢደር ኩራባቸው የአዲስ አበባ ሕይወት በሥራ ተቀበላት፡፡ ጉልበቷን ሳትሰስት፣ አቅሟን ሳትደብቅ ከሚተጉት ጋር ዋለች፡፡ የላቧን ዋጋ አላጣችም። በሰራችው ልክ እያገኘች ራሷን አቋቋመች፡፡ ዘቢደር መልካም ባለሙያ ነች፡፡ የድግስ ዝግጅት ባለ ጊዜ እጇን የሚሹ ፈልገው ያገኟታል፡፡ ዝናዋን የሰሙ ሌሎች አድራሻዋን አያጡትም ፡፡ ስትፈለግ ትገኛለች። ስትጠራ ትመጣለች፡፡

ለዘቢደር አሁን ጅማና ቤተሰቦቿ ትዝታዎች ናቸው፡፡ የአቅሟን ቤት ተከራይታ መኖር ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ዘቢደር ሥራ ባገኘች ጊዜ እረፍት ይሉትን አታውቅም፡፡ የተሰጣትን ኃላፊነት በወጉ ልትወጣ ሌት ተቀን ትደክማለች፡፡

ሁሌም እሳትና ሙቀት የማያጣው ውሎዋ አንዳንዴ በድካም ያልፋል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ጤናዋ ከስጋት መውደቁ አይቀርም፡፡ አዲስ አበባ ሥራውን ከጀመረች ወዲህ የስኳር ህመም አግኝቷታል። ለመፍትሔው የምትወስደውን የኢንሱሊን መርፌ የምትወጋው በራሷ እጅ ነው፡፡

ዘቢደር የስኳር ህመሟና አድካሚ ሥራዋ እየታገሏት ነው፡፡ ኑሮን አሸንፎ ለመቆም አትሆነው የለም፡፡ አንድ ቀን ግን ይህ ዓይነቱ ትግል ካላሰበችው አጋጣሚ አደረሳት፡፡ እየተራመደች ሳለ ህመሟ ከመንገድ ጣላት፡፡ በዚህ መነሻ ችግሯ እየከፋ፣ ድካሟ እየባሰ ሄደ፡፡ ሕክምና ጀምራ፣ መድኃኒቷን ተከታትላ ወደሥራዋ ተመለሰች፡፡

### በሌላ ቀን…

ከቀናት በአንዱ ዘቢደር እንደ ልማዷ ከቤት ወጣች፡፡ ክረምቱ ሊገባ ‹‹መጣሁ›› ማለት ይዟል። ዕለቱ ካለፉት ቀናት የተለየ አይደለም፡፡ ድካም ቢጤ ቢሰማትም መንገዷን አላቆመችም፡፡ ባልዘገየ፣ ባልፈጠነ ርምጃዋ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ ድንገት በእሷ ላይ የሆነው አጋጣሚ ግን ሁኔታዎችን እንዳልነበሩ ቀየራቸው፡፡

ዘቢደር ዓይኗ ላይ የሆነ ነገር አጭበረበራት፡፡ ፊቷን በእጇ ከልላ ልትከላከለው ሞከረች፡፡ ማጭበርበሩ እንዳሰበችው አልተዋትም፡፡ እንደምንም መሬቱን ፈልጋ በዝግታ አረፍ አለች፡፡ ሰውነቷ ቦታ ከመያዙ አንዳች ነገር ዓይኖቿን ሲከልላት ታወቃት። አሁንም በእጇ ፊቷን እየሞዠቀች ሁኔታውን ታገለችው፡፡ ማጭበርበሩን ተከትሎ በድንገቴ ጨለማ ተጋረደች ፡፡

ራሷን አላመነችውም፡፡ ብርሃን ፍለጋ ወደሰማይ አንጋጠጠች፡፡ ከጸሐይዋ ሙቀት በቀር የደረሳት የለም። ዓይኖቿን እየገለጠች፣ እየጨፈነች ጭላንጭል ፍለጋ ዋተተች፡፡ አዲስ ነገር አልተገኘም፡፡ በአፍታ ቆይታ ዓይኗ ከብርሃን ተራርቆ መሄጃዋ ጠፋት፡፡

እንደምንም ከቤት ደርሳ የሆነባትን ለጎረቤት አዋየች፡፡ የሰሟት ሁሉ የምትለውን አላመኑም፡፡ የፈጠጡ ዓይኖቿን እያዩ ደህንነቷን አረጋገጡላት። በወቅቱ በአቅሟ ለመታከም ሞከረች፡፡ የዓይኗ ችግር ሞራ መሆኑ ተነገራት፡፡ እንደ ጅማሬው በርትታ አልቀጠለችም፡፡ ወጪው ሲከብዳት ቸልተኝነት አበዛች፡፡

ዘቢደር ግራ ዓይኗን እንደጋረዳት በቀኙ ብቻ ስትመራ ከረመች፡፡ ይህ እውነት ግን ብዙ አልቀጠለም። በሌላ ቀን በድንገት የቀኝ ዓይኗም ተስፋ ተጋረደ። ሁለቱም ዓይኖቿ ከብርሃን ተጣልተው ከጨለማ ተዋደዱ፡፡ ዘቢደር በድንገት የጀመራት ችግር ከእይታ አራርቆ ዓይነ ስውርነትን አስተዋወቃት፡፡

ትናንት በሩጫ የሚተጉ እግሮች ዛሬ ከቤት ውለዋል፡፡ ሰርተው የሚያበሉ እጆች አሁን በችግር ተይዘው የሰው ፈላጊ ሆነዋል፡፡ ከምንም በላይ ንቁና ፈጣን የነበሩ ውብ ዓይኖች በጠዋቱ በጨለማ ተጋርደዋል፡፡

ዘቢደር ሁለት ዓይኖቿ ከታወሩ ጀምሮ የሕይወት አቅጣጫዋ ተቀየረ፡፡ ከመሥራት ወደመቀመጥ፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የቀየራት ክፉ አጋጣሚ ካልታሰበ መንገድ አዋላት፡፡ ትናንት የሚያውቋት በርካቶች ሊረዷት ተረባረቡ፡፡ ዝቅ ያለው ጉልበቷ፣ የታዘዘው ማንነቷ ጥሎ አልጣላትም፡፡ ቀን ቆጥሮ ዋጋዋን በመልካም መለሰ፡፡ ጎረቤቶቿ፣ ባልንጀሮቿ ታሪኳን የሰሙ ሁሉ ጎዶሎዋን ሊሞሉላት ፈቀዱ፡፡

### ጉዞ በነጭ በትር …

አሁንም የሕይወት ትግሉ ቀጠለ፡፡ ዘቢደር ከስኳር ህመሟ እየታገለች ራሷን ልታሸንፍ ቆመች። የሚንከባለሉ ንጹህ ዓይኖቿ ዛሬም አስተውለው የሚያዩ ይመስላሉ፡፡ አሁንም በነጭ በትሯ እየተመራች የጎደለ ኑሮዋን ልትሞላ ተንቀሳቀሰች፡፡

ትናንት ትሮጥበት የነበረ ሜዳ ዛሬ ዙሪያው ገደል ሆነባት፡፡ የምታውቀው ሁሉ ባዕድ መስሎ ተሰማት። ዘቢደር ከትናንት ማንነቷ ብዙ የሕይወት ሰበዞች ጎደሉባት፡፡ ሳታስበው የሌሎች ጥገኛ ያደረጋት ዓይነ ስውርነት ቀላል የማይባል ዋጋ ያስከፍላት ያዘ፡፡ በብዙ ክፉ አጋጣሚዎችም አመላለሳት፡፡

### ‹‹ከንፍር መሀል ጥሬ››

በአንድ ምሽት በነዘቢደር መንደር ድንገቴ የእሳት አደጋ ተነሳ፡፡ ይህን ተከትሎም ጩኸት ግርግሩ በረከተ። ነገሩ ባስ ባለ ጊዜም ብዙዎች ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን ለማዳን ሩጫ ጀመሩ፡፡ ሰፈሩ ሰባ ደረጃ ከሚባለው አካባቢ ነው፡፡ አብዛኛው ኑሮው በወንዝ ዳርቻ በመሆኑ አቅጣጫውን ወደ ውሃው አድርጓል፡፡

እሳቱ እየባሰ ችግሩ ስር መስደድ ሲጀምር አብዛኛው እየተጠራራ ‹‹እግሬ አውጭኝ›› ሲል ከአካባቢው ራቀ። ይህ ሁሉ ሲሆን ብቸኛዋን ዓይነ ስውር ያስታወሳት አልነበረም፡፡ ዘቢደር እሳቱ ተቀጣጥሎ ከእሷ ጥግ እስኪደርስ በፍርሃትና በመቁነጥነጥ ቆየች፡፡ ተደግፋው ከቆመችበት ግንብ በቀር የጠበቃት አላገኘችም፡፡


እሳቱ አራት ቤቶችን አቃጥሎ፣ ብዙ ንብረቶች አወደመ፡፡ ዘቢደር ጭሱና ወላፈኑ ወደእሷ ሲቀርብ ይሰማታል፡፡ አሁንም ግን የትነሽ ሲል የሚፈልጋት አልተገኘም፡፡ ደጋግማ እየጮኸችና እየጸለየች ፈጣሪዋን ‹‹እየኝ፣ ተመልከተኝ ›› ብላ ተማጸነች። ልመናዋ ከመሬት አልወደቀም፡፡ ‹‹ከንፍር መሀል ጥሬ›› እንዲሉ ያን የጨለማ ክፉ አጋጣሚ በተአምር አሸንፋ ከቀጣዩ ቀን ቆመች፡፡

ዘቢደር ይህን ጨምሮ ሌሎች ክፉ ጊዚያትን በሚያስገርሙ አጋጣሚዎች አልፋለች፡፡ ነጭ በትሯን ይዛ ስትራመድ መኪና በጥሶ የጣለውን የኤሌክትሪክ ገመድ ከመርገጥ የዳነችበትን ቀን ዛሬም ድረስ አትዘነጋውም፡፡

ዘቢደር ሁሌም የሚያግዟት ‹‹አይዞሽ›› የሚሏትን አታጣም፡፡ እንዲያም ሆኖ የብቸኝነት ሕይወት ይፈትናታል፡፡ በድንገት ቀኑ በጨለመባት ጊዜ ራሷን ከሁኔታዎች ማስማማት ይጠበቅባት ነበር፡፡

ለእሷ ከድንገቴው የዓይነ ስውርነት ውጣ ውረድ ጋር መታገል ቀላል አልሆነም፡፡ ውላ አድራ ግን ችግር መከራውን ከራሷ አግባባችው፡፡ ለቅሶ፣ ትካዜን ትታ ውስጧን አበረታች፣ ጠነከረች፡፡ አንድ ሁለት ሲል መቁጠር የጀመረው ጊዜ እንደዋዛ ሰባት ዓመታትን ቆጠረ፡፡

አንዳንዴ በሰዎች፣ ሌላ ጊዜ በነጭ በትሯ



ፎቶ ፡- ገባቦ ገብሬ፤

ዘቢደር ኩራባቸው

እየተመራች አሁንም ራሷን ፈለገች፡፡ ብርቱዋ ዘቢደር ቀኗን በትካዜ ማሳለፍ ምርጫዋ አልሆነም። የሆነባትን ስታስብ ብታዝንም ውሎዋ በዚህ ስሜት እንዲታሰር አትሻም፡፡

ልበ መልካሞች በሚያደርጉላት ድጋፍ እየታገዘች አስቸጋሪውን ኑሮ ቀጠለች፡፡ ውስጧ ተስፋ አላጣም። ከዓይነ ስውራን ትምህርት ቤት ገብታ የብሬን ትምህርት ቀሰመች፡፡ ለእርምጃዋ እንዲበጅ የመንገድ አቅጣጫ ተሞክሮን ወሰደች፡፡

### ሰባ ደረጃን ከውሾች ጋር …

ዘቢደር የምትኖርበት የሰባ ደረጃ አካባቢ ለልማት ተፈልጓል፡፡ ነዋሪው ሰፈሩን ለመልቀቅ ጓዙን ከሸከፈ ሰንብቷል፡፡ እሷ ተከራይ ነች፡፡ ለእኔ የምትለው መጠጊያ የላትም፡፡ ቤቶች እየፈረሱ ሰዎች መውጣት ሲጀምሩ በእጅጉ ጨነቃት፡፡

ቀስ በቀስ በዙሪያዋ የነበሩ ቤቶች ተነስተው ስፍራው ባዶ ሆነ፡፡ አከራዮቿ ቤታቸውን አፍርሰው ዕቃቸውን ይዘው ወጡ፡፡ ጣራው በተነሳ የግድግዳ ጥግ እሷና ውሾቿ ብቻ ቀሩ፡፡ ቀኑ አልፎ ምሽት ተተካ፡፡ ጨለማ የዋጠው አካባቢ በጭርታ ሲዋጥ ውስጧ ፍርሃት ነገሰ፡፡

ሰፈሩን አቋርጦ የሚያልፍ ወንዝን ይዞ ብቅ የሚሉ ጅቦች ሁሌም ስጋት ናቸው፡፡ ይህን የሚያውቁ አንዳንዶች ዘቢደርን እያሰቡ የሚሆነውን ገመቱ። ዙሪያዋን ያሉት ታማኝ ውሾች ግን ‹‹አለንሽ›› ሲሉ ጠበቋት፡፡ ዘቢደር ከፈጣሪዋ በታች እነሱን አመነች። ብርድና ውርጩን ችላ የቀን ሌሊቱን ጨለማ አለፈች፡፡

ዘቢደር በወንዝ ዳርቻ ሰው አልባ ሕይወት ከጀመረች ከአንድ ወር በላይ ሆኗል፡፡ ቀኑን እንደምንም አልፋ ምሽቱ ሲደርስ ይጨንቃታል፡፡ አሁንም ከፈጣሪ በታች ከሚጠብቋት ታማኝ ውሾች በቀር የደረሰላት የለም፡፡

ዘቢደር አንድ ቀን በድንገት ታመመች፡፡ ውሾችና ወንዝ በከበባት ስፍራ ራሷን ማስታመም አልቻለችም። ይሄኔ የዓይኖቿ መጥፋት ያጎደለባትን ሕይወት አስባ ከልብ አዘነች፡፡ ውሃ ቀድቶ የሚሰጣት ወገን ማጣቷ ልቧን ነካው፡፡

ከቀናት በአንዱ ግን መልካም ዓይኖች ወደ እሷ ተመለከቱ፡፡ አንዲት ባልንጀራዋና የቀበሌው አመራሮች ደርሰው ከስፍራው አወጧት፡፡

ዘቢደር ጓዝ ንብረቴን አላለችም፡፡ ሙሉ የቤት ዕቃዋንና ልብሷቿን እዛው ትታ ተከተለቻቸው፡፡ ሁኔታዋን ያየችው ሴት ልቧ ራራላት፡፡ ቀን እስኪያልፍ ብላ በቤቷ አስጠጋቻት፡፡ ዘቢደር ስጋትና ህመም ሲፈራረቅበት የቆየው አካሏ ለጊዜው አረፍ አለ። እንዲያም ሆኖ ውስጧ ጤና የለውም፡፡ ህመም እያዳከማት ነው፡፡ ሆስፒታል ገብታ ታክማ ተመለሰች፡፡

ዘቢደር አሁን በጽኑ ታማለች፡፡ ሕይወቷን ለማዳን ህክምና ያሻታል፡፡ ስለጤናዋ ግድ ያላቸው ስለእሷ ዝም አላሉም፡፡ በአስቸኳይ ከሆስፒታል አደረሷት። አሁን በቀላሉ ታክማ የምትወጣ አልሆነም፡፡ የስኳር ህመሟ ለወራት አልጋ አስይዞ አስተኛት፡፡

ዘቢደርን ያዩ የሕክምና ባለሙያዎች ከልባቸው አዘኑ፡፡ ድና ብትወጣ የምትሄድበት፣ እንደሌለ ባወቁ ጊዜ ሊረዷት ተባበሩ፡፡ አራት ወራትን ከሆስፒታሉ ግቢ ሳትወጣ ቆየች፡፡ ይህ በመሆኑ ዘቢደር አፏ ለምስጋና ተከፈተ፡፡ በዓይነ ስውር አቅሟ በወንዝ ዳር ያሳለፈችውን የብቸኝነትና የጨለማ ጊዜ አስባ ስለነገው ተስፋ ጣለች፡፡

### የሰኔው በረከት…

ከቀናት በአንዱ ዘቢደርን ያሉ ሰዎች ቀርበው አወሯት፡፡ ንግግራቸው፡፡ ስለዓይኗ ደህንነት ነበር። ሰዎቹ ‹‹የወደቁትን አንሱ የነዳያን ማህበር›› ከተሰኘ ድርጅት የመጡ ናቸው፡፡ ዘቢደር ዓይኗን ሊያሳክሟት እንደሚፈልጉ ስትሰማ ሳታቅማማ ተስማማች፡፡ ድርጅቱ እንደ እሷ ጊዜና ዕድሜ ዘንበል ያለባቸውን ወገኖች በመደገፍ ይታወቃል፡፡

ከሆስፒታሉ ወጥታ ወደ ድርጅቱ ገባች፡፡ አሁን ሰኔ ግም ማለት ጀምሯል፡፡ ከጥቂት ጊዚያት በኋላ ዓይኗ እንደሚታከም ቃል ተገብቶላታል፡፡ ዘቢደር እነዚህን ቀናት እስኪደርሱ በጉጉት ጠበቀች፡፡ ተስፋዋ ለመለመ፡፡ አንድ ቀን የተያዘለት ጊዜ ቀጠሮው ደረሰ። ሕክምናውን ወደምታገኝበት ሐኪም ቤት ተጓዘች፡፡

የሐኪሞቹ የመጀመሪያ ሥራ የቀኝ ዓይኗን ቀዶ ሕክምና መሥራት ነበር፡፡ እንደታሰበው ሆኖ በስኬት ተጠናቀቀ፡፡ ዓይኗ ለቀናት ታሽጎ መቆየት ነበረበት፡፡

### ድንገቴው ብርሃን

እነሆ የታሸገው ዓይን ሊፈታ ቀኑ ደርሷል፡፡ ዘቢደር በቀጠሮው ዕለት ከሐኪም ዘንድ ቀርባለች። እሽጉን በጥንቃቄ መፈታት ተጀምሯል፡፡ እይታዋን ለማረጋገጥ ጥያቄ ቀረበላት፡፡ የሰጠችው ምላሽ አስደንጋጭም፣ አስደሳችም ነበር፡፡ በጨለማ ውስጥ የኖረው ዓይኗ በትክክል ደማቁን ብርሃን ማየት ጀምሯል፡፡

ዘቢደር ውስጧ ሲመላለስ የኖረው ግማሽ ተስፋ ዕውን ሆኗል፡፡ ሰባት ዓመታትን ከጨለማ የተዛመደ ማንነቷ አሁን በከፊል ከብርሃን ተዋዷል፡፡ ይህ ለእሷ ከሙሉ በላይ ነበር፡፡ እውነታውን የሰሙ ደስታዋን በእኩል ተጋሩ፡፡ የቀረቧትን እያየች በስም መጥራት ያዘች፡፡ አዲስ ዓለም፣ አዲስ ሕይወትን ተቀበለች፡፡

ሁኔታው በዚህ ብቻ አልቆመም፡፡ ሁለተኛውን ዓይን ለመሥራት ሌላ ቀጠሮ ተይዟል፡፡ ከአንድ ወር በኋላ ዘቢደር ሐኪም ፊት ቀረበች፡፡ ልክ እንደቀድሞው ዓይነት ሕክምና መካሄድ ጀመረ፡፡ ግራ ዓይኗ ዳግመኛ ሕክምናውን አገኘ፡፡ የዘቢደር ውጤት ተመሳሳይ ነበር፡፡ ሁለቱም ዓይኖቿ በብርሃን ከለላ ተገናኙ

### ያልጠለቀች ጀንበር …

እነሆ! የሰባት ዓመታት የጨለማ ምዕራፍ በ‹‹ነበር›› ተዘጋ፡፡ ይህ ልብ ውለድ መሰል ታሪክ በዚህች ሴት ዕውን መሆኑ የበርካቶች እጅን በአፍ አስጭኗል፡፡

ልበ ቀናዋ ዘቢደር ዛሬ ብድር ከፋይ ሆናለች። በምትገኝበት ድርጅት ደካሞችን ደጋፊ፣ የወደቁትን አቃፊ ነች፡፡ ትናንት ከብርሃን፣ ወደጨለማ፣ መልሶም ወደ ብርሃን ላመጣት ፈጣሪዋ ምስጋናዋ የላቀ ነው። ከእሷ ጎን ለነበሩ ወዳጆቿ ሁሉ የተለየ አክብሮት አላት።

አሁን የስኳር ህመሟ ጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ዘቢደር ድቅድቅ ጨለማዋ ተገፏል፡፡ ጀንበሯ አልጠለቀችም፡፡ ዛሬም በብርሃን መንገድ ልትመለላስ ውስጧ የበረታ መንፈሷ የጠነከረ ነው።

# ስፖርት





## ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በታላላቅ ተጋባዦች ደምቆ ነገ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ በመላው ዓለም ስሟ በመልካም የሚጠራበት፣ የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ የምትደምቅበት፣ በሯጮቹ ሃገር አትሌቲክስ ባህላዊ ስፖርት መሆኑ የሚመሰከርበት፣ ኢትዮጵያዊያንና የሌሎች ሃገራት አትሌቶች ለማሸነፍ የሚፋለሙበት፣ በርካቶች ተሳታፊ ለመሆን የሚጓጉለት ተናፋቂው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ነገ ለ23ኛ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ስፖርት፣ ቱሪዝም፣ ኢትዮጵያዊ ባህልና እሴት፣ ዲፕሎማሲ ወዘተ በአንድ በሚታዩበት በዚህ መድረክ 45ሺ ሯጮች ይሳተፉበታል፡፡

ዛሬ ደግሞ 3ሺ500 ህጻናት የሚካፈሉበትና ‹‹ክትባት ለሁሉም›› የሚል መሪ ሃሳብ ያለው የህጻናት ሩጫ ይካሄዳል፡፡ በዘንድሮ ሩጫ ዓለም አቀፍ የ10 ኪሎ ሜትር ሩጫ ተሳታፊ ለመሆን ከተመዘገቡት ውስጥም ከ130 በላይ የሚሆኑት ከ15 ሃገራት የተወጣጡ ተወዳዳሪዎች ናቸው፡፡ 500 (200ሴት እና 300 ወንድ) የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በሚካፈሉበት በዚህ ውድድር ላይም እጅግ በርካታ ዝነኛ አትሌቶችን ባፈራው ግሎባል ስፖርት ኮሚዩኒኬሽን ስር የሚሰለጥኑ ዩጋንዳዊያን እንዲሁም ከሌሎች የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት የተወጣጡ አትሌቶች ተካፋይ ይሆኑበታል፡፡

ባለፉት ዓመታት ታዋቂ ከሆኑ አትሌቶችና የአትሌቲክስ ባለሙያዎች ባሻገር የጥበብ ሰዎች በመድረኩ ላይ ተገኝተው ውድድሮችን አስጀምረዋል። እነዚህ የክብር እንግዶችም የጎረቤት ሃገር ኬንያን ጨምሮ የእንግሊዝና ሌሎች ሃገራት ድንቅ ብቃታቸውን ያስመሰከሩና ከኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ጋርም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ፉክክር በማድረግ የሚታወቁ ጭምር ናቸው፡፡



በነገው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከ45ሺ በላይ ተሳታፊዎች ስመርጥ ተዘጋጅተዋል፣

በዚህ ዓመት ደግሞ በክብር እንግድነት ደቡብ አፍሪካዊቷ አንጋፋ አትሌት ኤለና ሜየር እንዲሁም ታዋቂው የአትሌቲክስ ውድድር ኮሜንታተር ቲም ሃቺንግስ በምስራቅ አፍሪካዊቷ የአትሌቶች ሃገር ተገኝተዋል፡፡ አንጋፋዋ አትሌት ባለፉት ዓመታት ቀንደኛ ተፎካካሪዎቿን ስታገኝ፤ የቀድሞው አትሌትና ለ33 ዓመታት የአትሌቲክስ ጋዜጠኛ የሆነው ቲም ድላቸውን የተረከላቸውን አትሌቶች እንዲሁም ልምምድ የሚያደርጉባቸውን ስፍራዎች የመመልከት እድል አግኝተዋል፡፡

ከኢትዮጵያዊያን ባለፈ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተሳትፎ በእርግጥም ውድድሩን አሁን ካለበት እንዲደርስ ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረጉ ይታመናል፡፡ በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የማርኬቲንግ ዳይሬክተር ህሊና ንጉሴ፤ በየዓመቱ ጥሪ ከሚደረግላቸው እንግዶች ባለፈ እነሱን ተከትለውየሚመጡበርካታአካላትእንደመኖራቸውዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ለውድድሩ ሽፋን እንደሚሰጠው ትገልጻለች፡፡ ይኸውም የውድድሩን ደረጃ የሚጨምር ሲሆን በተጋባዥ እንግዶች አማካይነትም ውድድሩ ምን ይመስላል የሚለው ለዓለም ይታያል። እንግዶቹ ምንም እንኳን በሙያቸው ታላላቅ ስራን የሰሩና በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቢሆኑም ግብዣው ሲቀርብላቸው ሌላ መርሃ ግብር ከሌላቸው በቀር ምላሻቸው አወንታዊ ነው፡፡ በተለይ ጥሪው የሚቀርብላቸው በጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ በኩል መሆኑ እሱን ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች ምላሻቸው ቀና ነው፡፡

እንግዶቹ ሩጫውን ከተመለከቱና ተሳታፊ ከሆኑ በኋላም ወደሃገራቸው ሲመለሱ በቀጣይ ሌሎች ከመጋበዝ አኳያ ያላቸው ሚና ከፍ ያለ ነው። ከዚህ ባለፈ ስለ ኢትዮጵያ የታዘቡትን ለሌሎች በመናገርም መልካም ገጽታን ይገነባሉ፡፡ ለዚህ መንገድ የሚከፍተውም የውድድሩ አዘጋጅ የሆነው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከውድድሩ ባለፈ የሚያዘጋጅላቸው የጉብኝት እንዲሁም ባህላዊ እሴቶችን የሚመለከቱበት መርሃ ግብር እንደሆነ ዳይሬክተሯ ታስረዳለች፡፡ ከተለያዩ ሃገራት ኤምባሲዎችንና አምሳደሮችንም በመጋበዝ በጋራ ይሰራል። ይኸውም የስፖርት ዲፕሎማሲ እንዲሁም የስፖርት ቱሪዝምን የሚያሰፋ ነው፡፡ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ላለፉት 23 ዓመታት ሳቆራረጥ በተመሳሳይ የመወዳደሪያ ወቅት እየተካሄደና እያደገ የመጣ ውድድር መሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም በሩጫው ላይ ከሚሳተፈው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ባለፈ በመገናኛ ብዙሃን ሽፋን ማግኘቱ ለዲፕሎማሲው ሰፊ ሚናን ይጫወታል፡፡

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በሌሎች ዓለማት ከሚካሄዱ ህዝባዊ ሩጫዎች የተለየና የራሱ የሆነ መልክ ያለው ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊ ቃና ያለው የስፖርታዊና የመዝናኛ መድረክ ነው፡፡ ይኸውም በየጊዜው በሃገር ውስጥና በውጪ ያለውን ተሳታፊ በይበልጥ በመሳብ ላይ ይገኛል፡ ፡ በመሆኑም ነገ አዲስ አበባ ላይ ከሚደረገው ሩጫ ባለፈ 200 የሚሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን የሚያሳትፍ የሩጫ ውድድር በተመሳሳይ ሰዓት ለንደን ላይም ይካሄዳል፡፡ ይህ ሁኔታ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ተከትሎ የ‹‹ቨርቹዋል ሩጫ›› በሚል መተግበሪያ የተጀመረ መሆኑ የምታስታውሰው ዳሬክተሯ በሂደት እያደገ ሊመጣ ችሏል፡፡ ለንደን ላይ ከሚደረገው ሩጫ ባለፈም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚሮጡና የተለያየ ዜግነት ያላቸው 130 የሚሆኑ ሯጮችም በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ መተግበሪያ አማካይነት 10ኪሎ ሜትር ይሮጣሉ፡፡

ብርሃን Berhan Bank

የማህበሩ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ 3,357,946,000

የምዝገባ ቁጥር 06/1/28428/01

ለብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች የተላለፈ የጉባኤ ጥሪ

የብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 14ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሐሙስ ኅዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ፤ ቦሌ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሔዳል፡፡ ስለሆነም የባንኩ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በተጠቀሰው ቀንና ቦታ ማንነታችሁን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪ ያቀርባል፡፡

**የጉባኤው አጀንዳዎች**

1. አጀንዳውን ማጽደቅ
2. የተከናወኑ የአክስዮን ዝውውሮችን ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል
3. በተጓደሉ የቦርድ አባል ምትክ የተተኩትን ዳይሬክተር ሹመት ማጽደቅ
4. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ
5. የውጭ ኦዲተሮችን እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማዳመጥ
6. ከዚህ በላይ በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴን ሪፖርት መስማትና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ
8. እ.ኤ.አ. በ2022/23 በጀት ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ወርኃዊ አበልና ዓመታዊ ክፍያ መወሰን እና
10. የጉባዔውን ቃለጉባዔ ማጽደቅ

**ማሳሰቢያ**

በጉባኤው ላይ ለመገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች

- ጉባኤው ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሞ ባሉት ቀናት ውስጥ የባንኩ ዋና መ/ቤት አድራሻ በሆነው በአዲስ አበባ ከተማ፤ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 2185 በሆነውና ቦሌ ድልድይ ፊት ለፊት በሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የአክስዮን አስተዳደር ክፍል በመገኘት የውክልና ፎርም/ቅጽ በመሙላት ተወካይ በመወከል ወይም
- በስብሰባው ለመገኘትና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ማስረጃ ያለው ተወካይ ዋናውን እና አንድ ፎቶ ኮፒ በጉባኤው ዕለት ይዞ እንዲቀርብ በማድረግ በወኪሎቻቸው አማካይነት መሳተፍ ይችላሉ፡፡

**የብርሃን ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

Tel +251 116 18 57 22 / +251 116 18 57 32 / +251 116 63 20 83
Fax +251 11 662 3431 Swift BERHETAA
E-mail info@berhanbanksc.com www.berhanbanksc.com
P.O.Box 387 Code 1110, Addis Ababa,Ethiopia

Follow us